# የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሙስሊሞች ማካፈል

- ለክርስቲያኖች ጠቃሚ መመሪያ

በቢል ዴነት

# የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሙስሊሞች ማካፈል

# ለክርስቲያኖች ጠቃሚ መመሪያ

## መግቢያ


ክፍል 1. ለወንጌል ስርጭት መነሣሣት

ምዕ. 1. ሙስሊሞች ወደ ክርስትና ሊለወጡ ይችላሉን? ........1
ምዕ. 2. በእግዚአብሔር ቃል መታመን ........3
ምዕ. 3. የዚህ መጽሐፍ ዋና አሳብ ........5
ምዕ. 4. እግዚአብሔር ለሙስሊሞች ያለው ርኅራኄ ........8
ምዕ. 5. እስልምና የበላይነትን በያዘበት አካባቢ የክርስቲያን ምስክርነት ........11
ምዕ. 6. ሙስሊሞችን ለመረዳት የሚጠቅም መሠረታዊ መረጃ ........14

ክፍል 2. ለሙስሊሞች መመስከር

ምዕ. 7. ድንገት ለሚያጋጥሙን መመስከር ........21
ምዕ. 8. ፍቅር - የሙስሊሞችን ልብ የመግረኪያ መንገድ ........27
ምዕ. 9. ክቡር ስለሆነው ወንጌል ለሙስሊሞች ንገራቸው ........31
ምዕ. 10. በወንጌል ላይ ሙስሊም ያለውን ጥላቻ መረዳት ........34
ምዕ. 11. ለተለመዱ የሙስሊሞች ተቃውሞዎች ምላሽ መስጠት ........38
ምዕ. 12. ጸሎት - የአገልግሎት መሠረት ........52
ምዕ. 13. መንፈሳዊ ውጊያ ........56
ምዕ. 14. አዲስ አማኞችን ደቀ መዛሙርት ማድረግ ........66

ክፍል 3. ሙስሊሞችን የመድረስ ስልት(መንገድ)

ምዕ. 15. የእርስ በርስ ግንኙነት ማድረግ ........71
ምዕ. 16. መገናኛ ብዙኃንን መጠቀም ........77
ምዕ. 17. ሥነ-ጽሑፍን መጠቀም ........79
የመሠረተ - አሳቦች ማጠቃለያ ........84
መደምደሚያ ........85

አባሪዎች:-

አባሪ ሀ. መነበብ የሚገባቸው መጻሕፍት ........88
አባሪ ለ. ለሙስሊሞች ለንባብ የሚያገለግሉ ጽሑፎች ምንጭ ........89
አባሪ ሐ. ሥቃይ እና ስደት ........91
አባሪ መ. «ለአነጋገርህ ጥንቃቄ ይኑርህ» ........96
አባሪ ሠ. ወንጌል በደብዳቤ........102

# መግቢያ

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ እስልምና ወንጌልን በኃይል በሚቋቋምባቸው አካባቢዎች፥ ክርስቲያኖች የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለሙስሊሞች እንዲያካፍሉ ማበረታታትና ማነሳሳት ነው።

«የምሥራቹን ቃል ለሙስሊሞች ማካፈል» የተሰኘችው የመጀመሪያዋ መጽሐፌ፥ በምዕራባዊው ዓለም በዘለቄታነት ኑሮአቸውን ለመሠረቱ ሙስሊሞች፥ ክርስቲያኖች ወንጌልን የሚያደርሱባቸውን ቀለል ያሉ መመሪያዎችን አስፍራለች። ለሌሎች የዓለም አካባቢዎች ተተርጉማ እንድትቀርብ አስተያየት በተሰጠኝ ጊዜ አዲስ እትም ሆና መውጣት እንደሚገባት ተገነዘብሁ። ይህችን መጽሐፍ የጻፍሁት ከብዙ ጸሎት እና በተለያዩ አገሮች ስላለው ሁኔታ መረዳት ያላቸውን ታዋቂ መሪዎች ምክር ካገኘሁ በኋላ ነው።

ምንም እንኳ ደራሲነቱ በስሜ ቢሆንም መጽሐፏ ከብልኋ አፍቃሪ ባለቤቴ ልምድ የተገኙ ጥልቅ አሳቦችንም ይዛለች። እውነቱን ለመናገር የሁለታችን ጥምር ውጤት ነች። ይህን በመሰለ አንገብጋቢ ጉዳይ ላይ ለመጻፍ ጌታ ቅድመ ሁኔታዎችን እንዴት እንዳዘጋጀልን ስናስበው በእጅጉ እንገረማለን።

ጆ አን በሕክምና ትምህርት ቤት ሆና ጌታን ካገኘች በኋላ በሙስሊም አገር በሙያዋ ለአሥራ ሁለት ዓመታት አገልግላለች። ብቻውን በበረሃ ውስጥ ለተቋቋመ አንድ የሚስዮን ሆስፒታል ኃላፊ ሆና ትሠራ ነበር። ከእግዚአብሔር ብርታትና ጽናት ባይሰጣት ኖሮ፥ ሴት ሐኪም ሆና እነዚህን ኩሩና ኃይለኛ ሙስሊሞች ማገልገል የሚቻላት ባልሆነም ነበር። ይሁንና ለሥጋዊ ችግሮቻቸው መፍትሔ በመስጠት በምትረዳበት ወቅት እስልምና ሊያረካላቸው ያልቻለውን የምንጊዜም የልብ ጥማታቸውን መረዳት ቻለች። የአገሬው ክርስቲያኖች በጣት የሚቆጠሩ ስለነበሩ ጆ አን የወንጌላዊነትና አዲስ አማኞችን ደቀ መዛሙርት የማድረጉን ሥራ፥ እንደዚሁም የሕክምና አገልግሎቷን በአንድነት ተያይዛው ነበር።

የእኔ ልምምድ ግን ከዚህ ለየት ያለ ነው። እኔ የኬሚካል መሐንዲስ ስሆን፥ በአውስትራሊያ ለሃያ አምስት ዓመታት የግል ድርጅቴን ሳካሂድ ነበርሁ። ጌታን የተቀበልኩት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሆኜ ሲሆን፥ ከማነበው ቅዱስ ቃል ለጌታ የመመስከር ትእዛዝ እንዳለብኝ ብዙም ውሎ ሳያድር ተረዳሁ። በሚቻልበት ቦታ ሁሉ እየተንቀሳቀሰ ወንጌልን በማዳረስ ላይ በሚገኝ አንድ የወንድሞች ቡድን ውስጥ አባል እንድሆን መራኝ። በመናፈሻ ቦታዎችና በባሕር ዳርቻዎች ለልጆች የሰንበት ትምህርት ከመስጠታችንም ባሻገር፥ ሰዎች በተሰበሰቡበት መንገድ ላይ ጭምር እንሰብክ ነበር። በዚህ በየሳምንቱ መጨረሻ ይደረግ በነበረው የወንጌል ስርጭት ላይ በመሳተፍ ሰላሣ አምስት የእርካታ ዓመታትን አሳልፌአለሁ። ወደ አገሬ የሚመጡ የውጪ ሰዎች በተለይም የሙስሊሞች ቁጥር እየጨመረ በመጣ መጠን እኔም በፍላጐቶቻቸው ላይ የነበረኝ አትኩሮት እየጨመረ ሄደ።

በገዛ አገሬ በወንጌል ስርጭት ሥራ ከመጠመዴም ሌላ፥ በዓለም ሁሉ ወንጌል እንዲዳረስ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በጸሎትና በገንዘብ ለመደገፍ ውሳኔ አድርጌ ነበር። ወደ በርካታ አገሮች የመጓዝና በክርስቶስ ወንድሞችና እህቶች ከሆኑ ከየአገሩ አማኞች ጋር ኅብረት የማድረግ ልዩ ዕድል ገጥሞኝም ነበር።

ሁለታችንም ሙስሊሞች ወደሚገኙበት አካባቢ በመሄድና በመሥራት የመመስከር ጥበብን ተማርን። ለአንተም ቢሆን፥ ለሙስሊሞች ስለጌታ ኢየሱስ ለመንገር፥ ስለ እስልምና ብዙ ማወቅ እንደማያስፈልግ ልንመሰክርልህ እንችላለን። ይህች መጽሐፍ የተጻፈችበት ዓላማ አንተም እንደዚሁ እንድትመሰክር ለመርዳት ነው። በእስልምና ላይ የተጻፈ ምሑራዊ ሥራ አድርጋ ራሷን አታቀርብም፤ ይልቁኑ ማስተዋወቂያ ናት ማለቱ ይመረጣል። ክርስቲያኖች ለሙስሊሞች መመስከር እንዲጀምሩ ለመርዳት የተጻፈች ነች። ሙስሊሞች ስለሚያምኑባቸው ነገሮች በቂ መረጃ ስለምትሰጥ ስለ አስተሳሰባቸውና ስሜቶቻቸው አንዳንድ ግንዛቤዎችን ታስጨብጥሃለች። በምትመሰክርበት ወቅት መከላከያቸውን ጥሰህ ለመዝለቅ የምትችልባቸውን ቀላል ዘዴዎች ታሳይሃለች። ደግሞ የተቃውሞዎቻቸውን ምሳሌዎች ታቀርብና ምላሽ የመስጫ ዘዴዎችንም ትጠቁምሃለች። መጽሐፏ የአዲስ ኪዳን መልእክቶችን ፈለግ በመከተል በቅድሚያ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮትን ካቀረበች በኋላ፥ በማከታተልም መወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ታብራራለች።

በዚህች መጽሐፍ ያካፈልናችሁ አሳቦችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች ከእግዚአብሔር በታች በመሆን በምትኖሩበት አካባቢ ለሚገኙት ሙስሊሞች በፍቅር ወንጌልን ለማዳረስ ብርታት ይሰጡአችሁ ዘንድ ጸሎታችን ነው።

ቢል ዴነት

ሲዲኒ፥ አወስትራሊያ

# ክፍል 1

## ለወንጌል ስርጭት መነሣሣት

### ምዕ. 1 ሙስሊሞች ወደ ክርስትና ሊለወጡ ይችላሉን?

ሰውዬው ክርስቲያኖች አልፎ አልፎ እየተሰባሰቡ በዓረብኛ ቋንቋ ወደሚነጋገሩበት ማዕከል ሲገባ ማንአለብኝነትን በተላበሰ ልበሙሉነት እንደተወጠረ ነበር። የመጣውም ክርስቲያኖች ማዕከሉን መዝጋት እንዳለባቸውና ሐሰተኛ ትምህርታቸውን ከመንዛት መቆጠብ እንዳለባቸው ለማስጠንቀቅ ነበር። ይህ ሰው እስልምናን ያጠና፥ ቁርዓንን በቃሉ ያወቀ እና በዓለም ብቸኛው እውነተኛ ሃይማኖት የእርሱ እንደሆነ የሚያምን ነበር። በእርግጥም ሰዎችን በማሳመንና በማስገደድ ሙስሊሞች ማድረግና የእስልምናን ወሰን የማስፋት ኃላፊነት ነበረበት።

ሕዝቡን በክርስቲያናዊ ፕሮፓጋንዳ አስታችሁታል በማለት የማዕከሉ ኃላፊ ከሆነው ሰው ጋር ክፉኛ ተከራከረ። ከብዙዎቹ መሰል ገጠመኞች ይህ የመጀመሪያው መሆኑ ነበር። ይህ ሰው የታክሲ ነጂ ሲሆን ብዙ ጊዜ ወደ ማዕከሉ ጐራ እያለ የማያወላውል አቋሙን ከመግለፅ የተገታበት ወቅት አልነበረም። ሆኖም የማዕከሉ ሥራ አስኪያጅ ክርስቶስ ሰውየውንም ጭምር የእርሱ ሊያደርገው እንደሚፈልግ ለሁለት ተከታታይ ወራት ያህል በታማኝነትና በትዕግሥት ካስረዳው በኋላ፥ ሰውዬው ከመከራከር ይልቅ ቀስ በቀስ ራሱን ለውይይት ማዘጋጀት ጀመረ። ተከታታዮቹም የውይይት ሳምንታት ጠበኛና ተከራካሪ የነበረውን ሰው ልዝብና በተመስጦ የሚያዳምጥ ሰው አደረጉት። ሥራ አስኪያጁም አንዳንድ ክርስቲያናዊ ሥነ-ጽሑፎችን ሊሰጠውና «ለምን ይህንን ወስደህ በማንበብ ምን እንደሚል አታስላስልም?» ብሎ አሳብ ሊያካፍለውም በቃ። ሰውዬው ትክክለኛ እውነትን ፈላጊ መሆኑ ሥራ አስኪያጁ ተሰማው። የሚያነባቸው መጻሕፍት ልቡን ያበሩለት ዘንድ ክርስቲያን ወዳጆቹን እንዲጸልዩለት ጠየቃቸው።

ሆኖም የሚቀጥሉት አራት ወራት ሰውየው የት እንደገባ ሳይታወቅ አለፉ። ክርስቲያኑም ሰው ስላስቀየመው የሸሸው መስሎት ተሰማው። ከዚያ በኋላ በአንድ የገበያ አዳራሽ አገኘውና «ምን ነው ጠፋህብን?» አለው። ሙስሊሙም «አንድ ቀን እመጣለሁ። ያን እንዳነበው የሰጠኸኝን ጽሑፍ አንብቤ እያሰብሁበት ነኝ» ብሎ መለሰለት።

ከበርካታ ወራት በኋላ ሰውዬው በደስታ እየተምነሸነሸ ወደ ማዕከሉ ገባና ሥራ አስኪያጁን «ዛሬ ለምን እንደመጣሁ ታውቃለህ?» በማለት ከጠየቀው በኋላ፥ «የመጣሁበት ምክንያት የዛሬው ዕለት ለእኔ በጣም ልዩ ቀን ስለሆነ ነው» ሲል እራሱ መለሰ። ከዚያም «ዳግመኛ ልትወለድ ይገባሃል» የሚል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የያዘውን የቀን መቁጠሪያ አንዱን ቅጠል ለሥራ አስኪያጁ አሳየው።

ቀጠለና «እኔም ይህንኑ ለማድረግ እሻለሁ! ዳግመኛ መወለድ እፈልጋለሁ» ሲል ተናገረ።

«ምን እያልክ ነው?» በማለት ክርስቲያኑ በመገረም ጠየቀው። በመቀጠልም «ዳግም መወለድ ማለት ምን እንደሆነ ይገባሃል? ይህ ያለጥርጥር በሕይወትህ ላይ ስደት እና መከራ እንደሚያስከትልብህ ታውቃለህ? የሚያጋጥምህን ተቃውሞስ ለመቋቋም ዝግጁ ነህ?» ሲል ሥራ አስኪያጁ ሊያስጠነቅቀው ሞከረ።

ሰውዬው ግን በምክሩ መሠረት አቅጣጫውን ለመቀየር አሻፈረኝ አለ! እንዲያውም እንዴት ንስሐ እንደሚገባና ክርስቶስን አዳኙ አድርጎ መቀበል እንደሚችል እንዲያሳየው ሥራ አስኪያጁን ተማጸነው። ፊቱም በደስታ እንደተጥለቀለቀ ጸሎት ማድረስ ጀመረ። ከዚያም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሰጠው ጠየቀው።

ከማዕከሉም ከወጣ በኋላ ባብዛኛው በሱቅ ንግድ የሚተዳደሩ ዓረቦች ወደሚኖሩበት አካባቢ በመሄድ «ዳግም ተወልጃለሁ! አሁን እኔ ክርስቲያን ነኝ» በማለት ጮክ ባለ ድምፅ ለሁሉም ተናገረ። ሥራ አስኪያጁ ተከትሎት በመሄድ እንዲህ ጥበብ በጎደለው መንገድ እራሱን ለአደጋ ማጋለጥ እንደማይገባው አሳሰበው። ሰውዬው ግን «ዝም ለማለት ጊዜ የለኝም። ሙስሊሞቹ የእምነት አቋሜን እከማስተባብል ግፋ ቢል ለሦስት ቀናት ብቻ ቢታገሱኝ ነው፥ ከዚያም ሊገድሉኝ ይሞክራሉ» ብሎ መለሰለት።

እንደተፈራውም ከጥቂት ጊዜ በኋላ የመስጊዱ መሪ በግንባር አግኝቶት ወደ እስልምና ካልተመለሰ በሕይወቱና በክርስቲያኖቹ የመሰብሰቢያ ማዕከል ላይ አስከፊ ሁኔታ እንደሚከሰት ዛተበት። ዳሩ ግን በዛቻው ባለመፍረክረክ ወደ ጌታ ከመጣው ክርስቲያን ጋር አብሮ እየሆነ ዓረቦች በኅብረት በሚገኙበት በተቋቋሙ ስብሰባዎች ላይ መካፈል ጀምሮ ነበር። ሆኖም ብዙ ሳይቆይ አካባቢውን ለቆ ሄደ። ያም ሆኖ ግን በእምነቱ እያደገ ስለመሆኑ ለማዕከሉ ሥራ አስኪያጅ በየጊዜው መልእክት መላኩን አላቋረጠም ነበር።

ለአንድ ሙስሊም ወደ ክርስትና መለወጥ ሌላው ምሳሌ በመካከለኛው ምሥራቅ ሙስሊም ሆኖ ያደገው የገዛ ጓደኛዬ ነው። ይህ ወጣት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሰማ ቢሆንም ምን ዓይነት መጽሐፍ ስለመሆኑ የማየት ዕድል አልገጠመውም ነበር። በከተማው መጽሐፍ ቅዱስ ያለው አንድ ባለሱቅ መሆኑን ከደረሰበት በኋላ ከዚህ ሰው ተዋሰ።

መጽሐፉን ለብዙ ተከታታይ ዓመታት በታላቅ ጉጉት ደጋግሞ አነበበው። መላውን መጽሐፍ ቅዱስ አሥራ አራት ጊዜ፥ አዲስ ኪዳንን ደግሞ ለብቻው አሥራ ሦስት ጊዜ በተጨማሪ ማንበቡን ነገረኝ። በመጨረሻም ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተጻፈውን እውነት በመረዳት አዳኙና ጌታው አድርጎ ተቀበለው። ይህ

እምነት ለብዙ ጊዜ ሲመኘው የነበረውን ታላቅ የልብ ሰላምና የደኅንነት ዋስትና ሰጠው።

ይሁን እንጂ ታላቅ መከራም አስከትሎበታል። ይህን ይቅርታ የማይደረግለት ክህደት በእስልምና ላይ ስለፈጸመ፥ ቤተሰቡ ከመካከላቸው እርሱን የሚገድለውን ሰው ለመለየት ዕጣ ይጣጣሉ ነበር። አጐቱ ሊገድለው ሞክሮ ባይሳካለትም ያቆሰለው ጠባሳ ግን እስከዛሬ በአንገቱ ላይ አለ። ይህ ጓደኛዬና ባለቤቱ አሁን በመካከለኛው ምሥራቅ ላሉ ሙስሊሞች ወንጌልን በማድረስ ውጤታማ አገልግሎት እየሰጡ ናቸው።

አዎን ሙስሊሞች ክርስቶስን ወደ ማመን ይመጣሉ። ብዙውን ጊዜ ግን ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድባቸው ይችላል። ቅዱሳት መጻሕፍትን ማጥናታቸው ግን፥ መንፈሳዊ ብርሃን ወደ ልባቸውና አእምሮአቸው እንዲገባ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። የሙስሊሞች የመለወጥ ምስክርነት የሚያሳየው የመጽሐፍ ቅዱስን ሐቀኛ ያላቋረጠና እረጅም ተጋድሎ ነው። የሙስሊሞች ሃይማኖታዊ ጉዞ አንዳንድ ጊዜ የሚጀምረው የሕልም ወይም የራእይ ያህል ሆኖ ይሆናል። ዳሩ ግን ሁልጊዜም ቢሆን የሚያሳርገው መጽሐፍ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን የሚገልጽበትን እውነት በመቀበልና መሥዋዕትነት በመክፈል ነው።

በጥልቀት የሚታሰብ፡-

*** ወደ ክርስትና የተለወጠ ሙስሊም ታውቃለህን? ከሆነ በክርስቶስ እንዲያምን /እንድታምን የገፋፋው/ፋት ምንድን ነው?

*** ራስህ ለሙስሊሞች ስትመሰክር የሚሰማህ ምንድን ነው?

## ምዕ. 2. በእግዚአብሔር ቃል መታመን

ወንጌልን ለሙስሊሞች የማድረሱ ዕድል ምናልባት ተስፋ-ቢስ መስሎ ይታይ ይሆን? አንተንስ ስታስበው እንድትፈራና እንድትርድ ያደርግሃል? (1ኛ ቆሮ. 2፡3)። ተስፋ የሚያስቆርጥና የድፍረት መሟጠጥ ስሜት ይሰማሃል? (ኤፌ. 6፡19)። ለእንደዚህ ዓይነቱ ሥራ እራስህን እንደማትመጥን በመቁጠር ደካማነት ይሰማሃል? (2ኛ ቆሮ. 12፡9፥ 10)። እነዚህ የአንተ ስሜቶች ቢሆኑም፥ ዳሩ ግን ብቸኛ ላለመሆንህ ላረጋግጥልህ እወዳለሁ። ከላይ በተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንደሚታየው፥ ሐዋርያው ጳውሎስም የዚህ ዓይነት ስሜት እንደ ነበረው ያመለክታል። በእርግጥም ይህ የጠፉትን ለማዳን በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ለመሳተፍ በሚደፍሩት ሰዎች ሁሉ ላይ የሚከሰት የጋራ ገጠመኝ ነው።

ወንጌልን ለሙስሊሞች ለማድረስ መሠረቱ ምን እንደሆነ መርምር። በእርግጥም መሠረቱ መቼውንም የማይለወጠው ኃያሉ የእግዚአብሔር ቃል

መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ትደርስበታለህ። ቅዱሳት መጻሕፍት ሕያው፥ ዘልቀው የሚገቡና የሚሠሩ ናቸው (ዕብ. 4:12)። እውነት ናቸው (ዮሐ. 17:17)። አሁን በሚሠራው በሕያው ቃሉ፥ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ (ዮሐ. 1:1-3) እና በተጻፈው ቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስ (1ኛ ጴጥ. 1:23) መካከል ምስጢራዊ በሆነ መንገድ አንድነት ይታያል። ይህም ሕያው ቃሉ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በኃይል የተሞላ ነው (1ኛ ዮሐ. 5:6)። ወንጌል ማለት ዘላለማዊ የሆነው የእግዚአብሔር ኃይል በደኅንነት ሥራ ውስጥ መገለጥ ማለት ነው (ሮሜ 1:16)። ወንጌል ስለ ራሱ የራሱ ማረጋገጫ አለው። ይኸውም በተቀበሉት ዘንድ የሚታየው የተለወጠ ሕይወት ነው። እኛም ይህንን ጌታ ኢየሱስ ያደረገልንን እውነት ለሌሎች በማካፈል ታማኝነታችንን እናረጋግጣለን።

ምንጊዜም ቢሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሙሉ መተማመን ይኑርህ። የእኛ ኃላፊነት መልእክቱን ማወጅ ነው። በጥንት ዘመን ነቢያት ያደረጉት ይህንኑ ነበር። አዋጃቸው «ጌታ እንዲህ ይላል» የሚል ሲሆን፥ ዛሬም እኛ ይህንኑ ማድረግ ይገባናል (2ኛ ጴጥ. 1:20፥ 21)። የነቢይ ሚና ቀላል አልነበረም። ነቢዩ ኤርምያስ «... ወዮ ጌታ እግዚአብሔር፥ እነሆ፥ ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም ...» ብሏል (ኤር. 1:6)። እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል የሰጠው ትእዛዝ «እነርሱ ዓመፀኛ ቤት ናቸውና ቢሰሙ ወይም ባይሰሙ ... አትፍራቸው፥ ቃላቸውንም አትፍራ ...» (ሕዝ. 2:5፥ 6) በማለት ነበር። የእግዚአብሔር ቃል «...፥ ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል፤ የምሻውን ያደርጋል። የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም» (ኢሳ. 55:11) የተባለለት ነው። በእርሱ አማካኝነት «... የጌታን ፍርሃት አውቀን ሰዎችን እናስረዳለን» (2ኛ ቆሮ. 5:11)፤ መውቀስ የሚችለው ቃሉ መሆኑን እያስተዋልን ለአእምሮአቸውና ለልባቸው እንናገራለን። እርሱን ለመጠቀም ድፍረት ይኑርህ፤ ምክንያቱም ሕይወት እና ኃይል ያለው በ«ዘሩ» እንጂ በዘሪው አይደለምና።

ለመመስከር ብቃት የጎደለህ መስሎ ቢሰማህ ለእያንዳንዳችን ከተዘረጋው የእግዚአብሔር ጸጋ ብርታትንና ልበ ሙሉነትን ተቀበል። በሐዋርያት ሥራ 3 ላይ የተጠቀሰውንና መልካም በሚሉት ቤተ መቅደስ ደጅ የነበረውን አንካሳ ለመፈወስ እንዴት እግዚአብሔር በጴጥሮስና በዮሐንስ እንደ ተጠቀመ ተገንዘብ። የእስራኤል መሪዎችም የኃያሉ እግዚአብሔር ክንድ በሐዋርያት አማካይነት መገለጡን ተቀብለውታል። «ጴጥሮስ እና ዮሐንስም በግልጥ እንደተናገሩ ባዩ ጊዜ፥ መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደ ሆኑ አስተውለው አደነቁ፥ ከኢየሱስም ጋር እንደነበሩ አወቁአቸው ...» (ሐዋ. 4:13)።

ለሙስሊሞች ለመመስከር ራስህን «ያልተማረና ተራ ሰው» አድርገህ በመመልከት አለመብቃት ይሰማህ ይሆናል፤ ነገር ግን ተስፋ አትቁረጥ። ኃይል የሚመነጨው በውስጥህ ካለው መንፈስ ቅዱስ እንጂ ከአንተ አለመሆኑን

አስተውል። «... ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው» (ሐዋ. 5:32)። ዕለት በዕለት «በመንፈስ ስትመላለስ» (ገላ. 5:16) አንተም «ከኢየሱስ ጋር ስለምትሆን» ለክብሩ ይጠቀምብሃል።

ከቶውንም ለቃሉ ጥብቅና የመቆም ግዴታ እንዳለብህ አድርገህ አታስብ። አንድ አንበሳ እየተጠቃ መሆኑን በማየት ለማገዝ ሲል በትሩን የሚያነሣ ሞኝ ሰው ይኖር ይሆን? የሚኖር አይመስለኝ። አንበሳው ራሱን መከላከል ስለማይሳነው የሚሻለው ፈትቶ መልቀቅ ብቻ ነው። ገናናው የእግዚአብሔር ቃልም ልክ እንደዚሁ ነው።

ወንጌል ልዩ መሆኑን ምንጊዜም ልንስተው ወይም ልንዘነጋው አይገባም። እስልምናን ጨምሮ ሁሉም ሌሎች ሃይማኖቶች የሚጋሩት አንድ ዓይነት ማዕከላዊ ነጥብ አለ። ይኸውም ሰው እግዚአብሔርን ይፈልጋል የሚል ነው። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ግን ማዕከላዊው ነጥብ እግዚአብሔር ሰውን መፈለጉ ነው።

## በጥልቀት የሚታሰብ

*** ሐዋርያው ጳውሎስ ስለምስክርነት የተሰማው እንዴት ነበር?

የአንተ ዓይነት ስሜት እንደነበረውና ዳሩ ግን እግዚአብሔር አብዝቶ እንደተጠቀመበት ተገንዝበህ ራስህን አበርታ።

***መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነና የሰዎችን ሕይወት መለወጥ እንደሚችል ከቅዱስ ቃሉ ልታረጋግጥ ትችላለህን? (2ኛ ጢሞ. 3:16፡17እና ዕብ. 4:12 አንብበህ በቃልህ ያዘው።)

# ምዕ.3 የዚህች መጽሐፍ ዐቢይ አሳብ

የዚህች መጽሐፍ ዐቢይ ዓላማ፥ ወንጌልን ለሙስሊሞች ለማድረስ ውጤታማው መንገድ የሙስሊሞችን አንገብጋቢ መንፈሳዊ ፍላጐቶች በዋና መነሻነት መጠቀም መሆኑን ለክርስቲያኖች ማሳየት ነው። እነዚህ አንገብጋቢ መንፈሳዊ ፍላጐቶች ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ሥራ ለማስረዳት መሪ መንገዶች በመሆን ሊጠቅሙ ይችላሉ።

«አንገብጋቢ መንፈሳዊ ፍላጐቶች» ስል ምን ማለቴ እንደሆነ ላብራራ። ይህን ፅንሰ አሳብ ወንጌልን በማዳረስ ረገድ ቁልፍ አሳብ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ይህ ፅንሰ አሳብ በየትኛውም ስፍራ ያሉትን ሰዎች የሚያገናኝ የጋራ ነጥብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ «(እግዚአብሔር)... ዘላለምነትን በልቡ ሰጠው» (መክ. 3:11) ይላል። ይህ የሰው የዘላለማዊነት ባሕርይ፥ በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ የጉጉት ስሜት

በመፍጠሩ ሊታወቅ ይችላል። የእያንዳንዱም ሰው ጉጉት ራሱን በተለያየ መንገድ ይገልጣል።

መንፈሳዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በሙስሊሞች ዘንድ ተመሳሳይ የሆነ የንቃት ደረጃ ይታያል። የእግዚአብሔር ሕልውናና ኃይል በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት አለው። ይሁን እንጂ እስልምና ሊያረካው የማይችለው ውስጣዊ ጥማት አለ። እነዚህም አንገብጋቢ ፍላጐቶች የሚገለጹባቸው አንዳንድ ምሳሌዎች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

. የእግዚአብሔርን ምሕረትና ይቅርታ መሻት

. መንግሥተ ሰማያት የመግባት ዋስትናን መናፈቅ

. የሞትና የእግዚአብሔርን ፍርድ መፍራት

. በላያቸው ስለ ሰፈነው ፍርሃት የሰይጣን ኃይልና ወደ ክፋት የሚያደርሰውን የየግል ዝንባሌያቸውን መረዳት

. ለእርኩሳን መናፍስት፥ ለጥንቆላና ለባዕድ ርኩሳን ነገሮች አምልኮዎች መገዛት

. የእግዚአብሔርን የፍቅር ክብካቤ አለመረዳት፥ የሕይወትን ዓላማ በትክክል አለመገንዘብ ወይም እግዚአብሔር ጸሎታቸውን እንደሚመልስ እርግጠኛ አለመሆን ናቸው።

እኛ ግን ባለመሰልቸት፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱና ትንሣኤው እነዚህን ፍላጐቶቻቸውን እንደሚያሟላላቸው በትሕትና ከገለጽንላቸው ስሜታቸው ይቀሰቀሳል። እንዲህ ዓይነቱ አቀራረብ ለሙስሊሞች «መፍቴሔ እንደማግኘት» ያህል የሚቆጠር ስለሆነ፥ ስለ እስልምና ሊነሣ የሚችለውን አላግባብ የሆነ ውዝግብና ክርክር ከወዲሁ ያስወግደዋል። በዚህ ዓይነት የምስክርነት ስልት በመጠቀም ውጤታማ ለመሆን ከመቻሉም፥ በግል የሥነ እስልምና ጠበብት የመሆንን አስፈላጊነት ያስቀረዋል።

እኔም ብሆን፥ ወንጌልን ለሙስሊሞች ማካፈል የተማርኩት፥ በመካከላቸው በመሰማራትና በተግባር በማሳየት፥ ቀስ በቀስ የበለጠ መረዳትን በመጨበጥ ነው። ብቃት ይኑርህም አይኑርህ አንተም ይህንኑ መንገድ መማር ትችላለህ። የኬሚካል መሐንዲስ እንደመሆኔ የሥራ ሕይወቴን ያሳለፍኩት በድርጅት ሥራ ነው። ዳሩ ግን ለመጽሐፍ ቅዱስ እውቀቴ ምንጭ የሆነው፥ በመላው የሕይወቴ ዘመን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ከማንበብ ያገኘሁት ጥበብ የተሞላው ተጨባጭ ልምድ ነው። የቤት ክርስቲያኔ ንቁ ተሳታፊ ብሆንም፥ ከዚህ በተጨማሪ በሌላ የወንጌል ስርጭት ሥራ የመሳተፍ ብርቱ ፍላጐት ነበረኝ።

ከቡድኔ ጋር ሁኜ በየአደባባዩ በመንሰብከበት በአንድ ወቅት እንዴት ከአንድ ሙስሊም ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ለመገጣጠም እንደ በቃሁ ከቶ አልዘነጋውም። ያም አጋጣሚ በሕይወቴ ዘለቄታነት ያለው ተጽዕኖ አሳድሮብኛል። ሰውዬው በስብሰባው ለጥቂት ጊዜ ያህል ቆሞ ሲያዳምጥ ቆየ። ሊሄድ ሲነሣ አስቆምኩትና በወንድማዊ መንፈስ የዮሐንስ ወንጌልን አበረከትኩለት። ወዲያው አርእስቱን አነበበና መልሶ ወደ እጄ ገፋ በማድረግ «የለም አልፈልግም። እኔ ሙስሊም ነኝ» አለ። ደነገጥኩኝ። የአነጋገሩና የድሪጊቱ አፈጻጸም ፍጹም ከሆነ የተሸናፊነት ስሜት አደረብኝ። ምን መልስ እንደምሰጠው ፍንጭ አጣሁ። ትቶኝ መሄዱን በዓይኔ በተከታተልሁ መጠን ተስፋ መቁረጤም ጨመረ። እኔም በዚያች አጋጣሚ የተነሣ ረጅሙን ትምህርታዊ ጉዞዬን ተያያዝኩት። በዚህችም መጽሐፍ አማካይነት ለማስተላለፍ የሞከርኩት ወንጌልን ለሙስሊሞች ለማድረስ ባደረግሁት ጥረት ያገኘኋቸውን ትምህርቶች ነው።

አንድ ቶቅርብ ወዳጂ የሆነ ሰው ለብዙ ዓመታት ያህል ወንጌልን በሙስሊሞች መካከል ለማሰራጨት በንቃት ሠርቷል። በመጀመሪያ ላይ የነበረው አቀራረብ፥ በምክንያታዊ የክርክር ዘዴ ስሕተታቸውን ፊት ለፊት ማጋለጥ ነበረ። ዳሩ ግን ከዓመታት አገልግሎቱ በኋላ ይህ ዘዴው ትክክለኛ አለመሆኑ ተሰምቶት አቀራረቡን ቀየረ። እንደ መሰለኝ ሙስሊሞች በክርክር ለክርስቶስ ሊማረኩ እንደማይችሉ ሳይገነዘብ አልቀረም።

ስለዚህ ሙስሊሞችን ለመድረስ የሚያስፈልገውን ዕቅድ ጠቅለል ባለ መልኩ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ። ይህች መጽሐፍ ወደ ፊት በገፋች መጠን ይህ አሳብ ተስፋፍቶና በጥልቀት ተዘርዝሮ ይቀርባል።

1. በሰብአዊነት መንፈስ በመመራት ወዳጅነትን፥ እምነትን፥ አመለካከትን፥ ወዘተ የሚያዳብር ውይይት በማካሄድ የጋራ መተማመን መሥርት። (ከበድ ያሉ ጥያቄዎችን ስለመመለስ ዘዴዎቹ በኋለኛዎቹ ክፍሎች ተካትተዋል)።

2. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለሌሎች መስክር።

3. እንዴት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታህና አዳኝህ አድርገህ እንዳመንክና አሁን የደኅንነት ዋስትና ያገኘህ ስለመሆኑ ተናገር።

4. ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ክፍሎችን የያዘ ጽሑፍ ለሙስሊም ጓደኛህ ስጠው።

5. በተለይ ላጋጠሙህ ሰዎች ጸልይላቸው።

## በጥልቀት የሚታሰብ

*** ክርስቲያን ከመሆንህ በፊት አንገብጋቢ ስለነበሩት አንዳንድ መንፈሳዊ ፍላጐቶችህ ወይም ችግሮችህ አስብ።

*** ይህ የሙስሊሙን የልብ ፍላጐት እንድትረዳ እንዴት ነው የሚረዳህ?

*** ለሙስሊም ለመመስከር ሞክረህ ታውቃለህ? አቀራረብህ ልባቸውን ነክቶታል?

## ምዕ. 4 እግዚአብሔር ለሙስሊሞች ያለው ርኅራኄ

ቤተ ክርስቲያን በሙስሊሞች መካከል ለወንጌል ስርጭት ያደረገችው ጥረት ያስመዘገበው ውጤት እጅግ ዝቅተኛ ነው። ሙስሊሞች «አይበገሬ» ተደርገው በመቆጠራቸው ክርስቲያኖች ፊታቸውን የመለሱትወደ ሌሎች ሕዝቦች ነው። ይህ አመለካከት የሚያሳዝንና ይቅር የማይባል ነው። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ የዓለም ሙስሊሞች ወንጌልን አንድም ጊዜ የመስማት ዕድል ሳይገጥማቸው ሌሎቹ ግን ወንጌልን ደጋግመው የሚሰሙት ለምን ይሆን? በመሠረቱ ወንጌልን በማወቃችንና ጌታ ኢየሱስን እንደ አዳኛችን አድርገን በማመናችን በእርግጥም የታደልን ነን። ታዲያ ግን ብዙ መታደል ብዙ ኃላፊነትን መቀበል መሆኑን ልንዘነጋው አይገባም። ጌታ ኢየሱስ «... ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው ...» (ማቴ 28፡18፥ 19) ብሏል።

ሆኖም ግን የአንተ ሰፍራ ቢለወጥና ሙስሊም ብትሆን ምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ልትሆን እንደምትችል ቆም ብለህ አስበህ ታውቃለህን? ደግሞስ አንድም ክርስቲያን የምሥራቹን ቃል ለማካፈል ከጐንህ ለመሆንና ጥረት ለማድረግ ደንታ ቢስ ቢሆን ምን ይሰማህ ነበረ? ስለዚህ ንስሐ እንግባና ጌታ ኢየሱስ እንዳዘዘን ወንጌሉን አንድ ቢሊዮን ሙስሊሞችን ጨምሮ ለሚገኘው ለሁሉም ሕዝብ ለማድረስ ቆርጠን እንነሣ።

የእግዚአብሔር ልብ ለሚጠፉት የሚደርስ ርኅሩኅ ልብ ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት በብዙ ስፍራዎች የሰው ልጆች ሁኔታ እንደሚያሳስበው ገልጧል።

አንዳንዶቹን ምሳሌዎች ከዚህ በታች ተመልከት። «... ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፉ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል» (2ኛ ጴጥ. 3፡9)። «እኔ ሕያው ነኝና ኃጢአተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ይኖር ዘንድ እንጂ ኃጢአተኛው ይሞት ዘንድ አልፈቅድም፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ተመለሱ፥ ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ፤ ስለምንስ ትሞታላችሁ? ...» (ሕዝ. 33፡11)። «እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል ...» (ሐዋ. 17፡30)።

መጽሐፍ ቅዱስ፥ «እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል?» በማለት ይጠይቃል (ሮሜ 10፡14)። ይህ ጥያቄ መልስ የሚያገኘው ክርስቲያኖች ሁሉ በአካባቢያቸውና ከአባቢያቸውም አልፈው ለሚኖሩ ወንጌልን የመንገር ኃላፊነታቸውን ሲገነዘቡ ነው።

እግዚአብሔር ለአገልጋዮቹ በጣም ቸር ነው። ለሌሎች በምንመሰክርበት ጊዜ የምንችለውን ያክል እንድንወጣ ብቻ ዝም ብሎ አይልከንም። በውስጣችን ሁኖ በኃይል እንዲሞላን፥ እንዲመራንና እንዲያነቃቃን ቅዱስ መንፈሱን ይሰጠናል። አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲገጥሙን በልዩ ጥልቅ መረዳቱ ሊያጽናናን ይችላል። ጳውሎስ በቆሮንቶስ በሚሰብክበት ጊዜ ከአይሁድ ተቃውሞና ስድብ የተነሣ ይፈራ ነበር። ምናልባት አካባቢውን ለቆ ለመሄድ ሳያስብ የቀረ አይመስልም። እግዚአብሔር ግን «እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፥ ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሣብህ የለምና አትፍራ፥ ነገር ግን ተናገር ዝምም አትበል፤ በዚህ ከተማ ብዙ ሕዝብ አሉኝና አለው» (የሐዋ. 18፡9፥ 10)። በከተማይቱ የሚኖሩ ብዙ ሰዎች በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚያምኑ እግዚአብሔር ለጳውሎስ ከገለጠለት በኋላ ተረጋጋ። ከዚህም የተነሣ ለአንድ ዓመት ተኩል በዚያው ስብከቱን ቀጠለ። በዚህ ወቅት ነበር ታላቋ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው።

መንፈስ ቅዱስ በልባቸው መሥራት የጀመረባቸውን ሙስሊም ጓደኞችህንና የምታውቃቸውን በወንጌል ለመድረስ ይመራህ ዘንድ ሁኔታዎችን እግዚአብሔር እንዲያስተካክልልህ ጠይቅ። ለምስክርነትህ ምላሹ በቁጣና በመቃወም ቢንቁህ እንኳ ተስፋ አትቁረጥ። ምናልባትም ለእንዲህ ዓይነቱ ሰው በእኛ ዘንድ የሚኖረው ግምት ለደኅንነት ተስፋ የሌለው ሊሆን ይችላል፤ ዳሩ ግን የልቡን ማወቅ አንችልም። ስለዚህ ይህን መሰሉን የተጣደፈና ጽናት የሌለው ሰብአዊ ፍርድ ከመስጠት ልንቆጠብ ይገባል። አንዳንድ ጊዜ ለወንጌል ምላሽ የሚሰጠው ፈጽሞ ያልታሰበ ሰው ነው። ለምሳሌ ተከታዩ ታሪክ አንድ አሊ በሚል ስም ልጠራው የፈለግሁት ሰው ያጫወተኝ ነው።

«እኔ በኢራን እስላማዊ ትምህርቶችን በመስጊድ የምሰብክ አክራሪ ሙስሊም ነበርኩኝ። አብዮት ተደርጐ አያቶላ ኾሚኒ ሥልጣን ላይ ሲወጣ የተሳሳተ የፖለቲካ መስመር በመያዜ በወኅኒ ተጣልኩኝ። ታምራዊ በሆነ መንገድ ከወኅኒ

አመለጥኩኝና ጠመዝማዛዎቹን ተራሮች አቋራርጬ ቱርክ ገባሁ። በዚያ ያልታወቅሁ ስደተኛ ሆኜ የድህረ ምረቃ ትምህርቴን ለመከታተል በቃሁ።

«አንድ ቀን ጓደኛዬን ልጠይቀው እቤቱ ሂጄ ሳለሁ በቋንቋዬ በፋርሲ የተጻፈ አዲስ ኪዳን (ኢንጂል) አየሁኝና እንዲያውሰኝ ጠይቄ ወሰድኩት። ማንበብ በጀመርኩ ጊዜ በአዲስ ኪዳን ያነበብኩትን በቁርዓን ከተጻፈው ጋር አነጻጽር ነበር። ይህን ያደረግሁት ከማምነው ጋር ተመሣሣይነት እንዳለው ለማየት ነበር። ዳሩ ግን እየጠለቅሁ በሄድኩ ቁጥር ስለ እስልምና እምነቴ ማሰቤ እየመነመነ ሄደ። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት፥ በአስደናቂ ትምህርቱና ሕይወቱ ተማረክሁኝ። ለአራት ወራት ያክል አዲስ ኪዳንን ከአጠናሁ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ በትክክል አምላክ እንደሆነ ከዚህም የተነሣ ሊመለክበትና ሊታዘዙት የተገባ እንደሆነ አመንሁ።

«ቆየት ብሎ ባለቤቴንና ልጆቼን ከኢራን ማውጣት ቻልሁና ቱርክ መጥተው ተቀላቀሉኝ። አንድ ሳምንት ያህል አብረውኝ ከሰነበቱ በኋላ ባለቤቴ «አሊ፥ ልዩ ሆነሃል። የለወጠህ ነገር አለ?» አለችኝ። በእኔ ላይ በሆነው ለውጥ እጅግ ስለተሳበች አዲስ ኪዳንን ሳነብላት ለማዳመጥ ፈቃደኛ ሆነች። ትምህርቶቹን አስረዳኋት፥ ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘሁትን አዲሱን እምነቴን አካፈልኋት። ቀስ በቀስ ጌታ በውስጧ ሠራና እርሷም ክርስቶስን እንደ ጌታዋና አዳኟ አድርጋ ተቀበለች። በቱርክ በምንኖርበት ከተማ ካለው አነስተኛ የአማኞች ኅብረት አብረን ተቀላቀልን። እነርሱም ክርስቲያን ደቀ መዛሙርትና ምስክሮች ሆነን እንድናድግ ረድተውናል።

«እግዚአብሕር ዕድሉን ስላዘጋጀልን ወደ ምዕራብ አገር ሄደን ለመኖር በቃን። በዚህ ስፍራ ቤተሰባችን በአካባቢው ካለው ቤተ ክርስቲያን ጋር ሙሉ ኅብረት ከመመሥረቱም ለኢራናውያንና ቱርክ ጐረቤቶቻችን ስለ አዳኛችን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደልብ ለመመስከር ነፃነት በማግኘታችን ደስተኞች ነን።»

እግዚአብሔር በገዛ ዓለሙ ውስጥ የሚጠቀምበትን የአሠራር ስልት በተመለከተ ሉዓላዊ ነው። አንዳንዴ ለጠፉት ለመናገር ያልተለመዱ መንገዶችን ሲጠቀም ብዙውን ጊዜ ግን የዳኑ ኃጢአተኞችን መልእክተኞቹ ያደርጋቸዋል። ተግባራችን «የምሥራቹን ቃል» ማወጅ ነው። በምድር ላይ ፈቃዱን ለመፈጸም የሕያው እግዚአብሔር አገልጋይ መሆን ታላቅ ዕድል ነው። «የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ፤ የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ፤ ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና» (1ኛ ቆሮ. 3:9)።

## በጥልቀት የሚታሰብ

*** «በወንጌል ለመድረስ ሙስሊሞች እጅግ የማይበገሩ ናቸው?» ስለሚለው አባባል ምን ታስባለህ?

*** እግዚአብሔር ስለ ጠፉት ያለው አመለካከት ምንድን ነው? (ከመጽሐፍ ቅዱስ በመጥቀስ አመሳክር።)

*** እግዚአብሔር ለሙስሊሞች ርኅራኄን እንዲሰጥህ አሁኑኑ ጊዜ ወስደህ ጸልይ።

# ምዕ. 5 እስልምና የበላይነትን በያዘበት አካባቢ የክርስቲያን ምስክርነት።

ሙስሊሞች በመላው ዓለም በሚገኙት የእስልምና ተከታዮች ዘንድ ፍጹም መግባባትና መቻቻል እንዳለ በማስመሰል ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሌሎችን ለማሳመን ሲሞክሩ ይታያል፤ ዳሩ ግን ማንኛውም የማሰብ ችሎታ ያለው ሰው፣ ለስምንት ዓመታት የዘለቀውንና ሙስሊም ሙስሊሙን የወጋበትን በኢራንና በኢራቅ መካከል የተካሄደውን የጭካኔ ጦርነት ሲያስታውስ በዚህ ሊታለል አይችልም። በሙስሊም አገሮች ውስጥ ባሉ ክርስቲያኖች ላይ የሚደርስ ውርደትና ሥቃይ በየጊዜው በሰብአዊ መብት ተከላካይ ድርጅቶች ይጋለጣል። የአንዳንድ አገር ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በረቀቀ መንገድ ይረሸናሉ፣ ይገደላሉ። አንዳንድ ደራሲዎች በመጽሐፎቻቸው ጥቂቶቹን የሙስሊም መሪዎች በማስኮረፋቸው ብቻ ለሕይወታቸው በመፍራት የፖሊስ ጥበቃን ለመጠየቅ ተገደዋል። የእስላምና ድብቅ መርሐ - ግብር (ዓላማ) አገሮችን ሁሉ በፖለቲካ ኃይል መቆጣጠር ነው።

በተለያዩ አገሮች ያለው ሁኔታ እንደ ሙስሊሙ ሕዝብ ተጽዕና ደረጃ ይለያያል። ከየአገሩ ሕገ መንግሥታዊ ገደብ የተነሣ የሙስሊሞቹ ኃይል ውስን ከሆነበት አገር አንሥቶ፥ እስላማዊው ሕግ ፍጹም እስከሚቆጣጠርበት ደረጃ ድረስ ይለያያል። ሙስሊሞች ያለ ምንም ተቃውሞ በሚገዙበት አካባቢ፣ ክርስቲያኖችንና ወንጌልን ለማጥፋት የሚወሰደው ማንኛውም እርምጃ ትክክል ተደርጐ ይቆጠራል። ተጽዕኖአቸውን ለማስፋፋት የሚጠቀሙበት ስልት በቀጥታ በገንዘብ በመደለል ወይም በኃይል በማስገደድ ላይ ያተኰረ ነው። በተዘዋዋሪም መንገድ «የነዳጅ ገንዘብ» ሕዝቦችን ወደ እስልምና ለመለወጥና የፖለቲካ የበላይነትን ለመጨበጥ በገፍ ይፈስሳል። ይህ ካልተሳካላቸው ደግሞ ሚዛናዊነት በጐደለው ቁጣ በወንጌል ላይ በመነሣሣት ቤተ ክርስቲያንንና መኖሪያ ቤቶችን

ያፈርሳሉ፤ ብሎም ክርስቲያኖችን እንኳ ይገድላሉ። ከተጽዕኖአቸው መንጋጋ ውስጥ ለማስገባት የሚወስዷቸው ተጨማሪ እርምጃዎች ክርስቲያኖችን ከትምህርት ቤት፥ ከዩኒቨርስቲዎች፥ ከመንግሥት ሥራ ቦታ ማባረርና የክርስቲያን ሆስፒታሎችንና ተቋማትን መዝጋት የመሳሰሉት ናቸው።

በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ለሚገኙት ሙስሊሞች ወንጌልን ማድረስ ከፍተኛ ዋጋን የሚያስከፍል ነው። ምንም እንኳ ታላቅ ፍቅርን የሚጠይቅ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ለሙስሊሞች ወንጌልን እንድናካፍል ያዝዘናል። ጉዳዩ ለእኛ በአማራጭነት የቀረበ አይደለም። ደግሞም የሰው ፍራቻ ከዓላማችን ሊያዘናጋን አይገባም። «... የሚሞተውን ሰው እንደ ሣርም የሚጠወልገውን የሰው ልጅ ትፈራ ዘንድ አንተ ማነህ? ሰማያትንም የዘረጋውን ምድርንም የመሠረተውን ፈጣሪህን እግዚአብሔርን ረስተሃል፤ ...» (ኢሳ. 51፡12፥ 13)። ስለ ጌታችን መናገር ከፈራን የእግዚአብሔርን ኃያልነት ዘንግተናል ማለት ነው።

ሁላችንም በተወሰነ ደረጃ ስንመዘን ዮናስ ለነነዌ ሕዝብ የነበረውን ዓይነት አመለካከት ይዘን መገኘታችን የሚያሳዝን ነው። እግዚአብሔር ነቢዩን ያዘዘው ንስሐ እንዲገቡ እንዲያስጠነቅቃቸውና ከሚመጣው ፍርድ እንዲያመልጡ እንዲነግራቸው ነበር። ሆኖም ነቢዩ የምሕረትንና የይቅርታን ቃል ወደ ኋላ አዘገየባቸው። የዮናስ መንገድ የመስቀል መንገድ አይደለም።

በሚያሳዩት የጭካኔ ፍርደ ገምድልነት ወይም ተጽዕኖ የተነሣ በሙስሊሞች ላይ የልብ ጥላቻ ወይም ድብቅ የበቀል ስሜት አይደርብህ። እግዚአብሔር «ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤ ... ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ። ... ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፤ በቀል የእኔ ነው፥ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ...» (ሮሜ 12፡17-19)። በእስልምና ሥርዓት ላይ ያለ አመለካከት በሙስሊም ሕዝቦች ላይ ካለን አመለካከት ጋር መምታታት የለበትም። ምንም እንኳ ሕዝቡን ለእስር ያበቃቸውን ሥርዓት ብንጠላውም፥ ሕዝቡን ግን መውደድ አለብን። ስለ እስራታቸው ማዘንና መራራት ይገባናል። «ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ (ሰይጣን) የማያምኑትን (ሙስሊሞች) አሳብ አሳወረ») 2ኛ ቆሮ. 4፡4)። ሙስሊሞች ከኃጢአት የመመለስንና በክርስቶስ የማመንን መልእክት ሊሰሙ ይገባቸዋል። መልእክቱም በአንድ በሆነ ሰው አማካይነት ሊነገራቸው ይገባል።

እርግጥ አንዳንዶቹን የሙስሊሞች ግፍና በደሎች ስናሰላስል የፍቅር ዝንባሌን ማሳየቱ በግል ጥረታችን የማይቻል ነው። እንደ እውነቱም ራስን በጤናማ አካባቢ ማቆየቱ ሁልጊዜም ቢሆን ተመራጭነት ያለው ነው። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር

ጠላቶቹ ሳለን እኛን እንደፈለገን ከቶውንም መዘንጋት የለብንም። «ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ...» (ሮሜ 5፡10)፥ እንደዚሁ ሁሉ እኛም እንደ ጠላቶቻቸው የሚቆጥሩንን ሁሉ መፈለግ አለብን። ይህ የሚቻለው እግዚአብሔር ጸጋውን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሲያፈስልን ብቻ ነው። «... በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ...» (ሮሜ 5:5)። «ይህን ስለ ቈረጥን የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና፤ ...» (2ኛ ቆሮ. 5፡14)። «እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን» (2ኛ ቆሮ. 5፡20)። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት እግዚአብሔር ሕይወታችንን ለሁሉም ሰዎች የፍቅሩ ቧንቧ እንዲሆን ይፈልጋል። በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የእርቅ መልእክትን ማስተላለፍ በተለይ ለቤተ ክርስቲያን የተለለፈ የዘመቻ አዋጅ ነው።

በሚያገለግሉን ላይ ጤናማ አመለካከት እንዲኖረን መጽሐፍ ቅዱስ አንድ አስደሳች በሆነ ታሪክ አማካኝነት ያበረታታናል። ከብዙ ዘመናት በፊት አንዲት ልጃገረድ በሶሪያውያን ወራሪዎች ተማርካ ወደ ጦር አበጋዙ ቤት በባርነት እንድታገለግል ተወሰደች። እንደ እውነቱ ከሆነ ለዚህ በባርነት ለሚገዛት ሰው በጐ ፈቃድ ሊኖራት ምንም ምክንያት ባልኖራትም ነበረ። እርሷን በማረኳት ሰዎች ወላጆችዋ ሲገደሉ፥ ቤቷና መንደሯ ሲጋይባት ተመልክታ ሊሆን ይችላል። አሁን ደግሞ በጦር አዝማቹ ሰው ቤት ባሪያ ናት። ሆኖም ጌታዋ ለምጽ እንደነበረበት ባወቀች ጊዜ ያሳየችው የቸርነት መንፈስ ምንኛ ታላቅ ነበር። በሆዷ ደስ ከመሰኘትና በበሽታው ሥቃይ እየማቀቀ እንዲሞት ከመመኘት ይልቅ መልካም ዜና አበሠረችለት። «(... ጌታዬ በሰማርያ ካለው ከነቢዩ ፊት ቢደርስ ኖሮ ከለምጹ በፈወሰው ነበር ...» (2ኛ ነገ. 5፡3) አለች። በ2ኛ ነገሥት 5 ላይ ያለውን ሙሉ ታሪክና አስደሳች ድምዳሜ አንብብ። ጌታ ኢየሱስ በሉቃስ 4፡27 ላይ እንደ ተናገረው በዚያን ዘመን የተፈወሰ ለምጻም ቢኖር ንዕማን ብቻ ነው። ስለዚህ ይህች ታናሽ ብላቴና በእግዚአብሔር ላይ በነበራት እምነት ካልሆነ በቀር እርሱ ሊፈውሰው እንደሚችል የምታውቅበት መንገድ አልነበረም። በጭካኔ በሚያገለግሉን ላይ በእንዲህ ዓይነቱ መንፈስ እርምጃችንን እንድናስተካከል እግዚአብሔር ይርዳን። ያች ታናሽ ብላቴና የነበራት መተማመን ዓይነት እኛም በቸሩ አምላካችን ላይ ይኑረን። በሥቃይና በስደት ላሉ ክርስቲያኖች ስላለው የእግዚአብሔር ጸጋ በአባሪ ሐ ተገልጿል።

## በጥልቀት የሚታሰብ

*** በአካባቢህ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች እርስ በርስ ለመግባባት ያላቸው ዝንባሌ ምን ይመስላል?

*** ሙስሊሞች ባህላዊ ጠላቶችህ ከሆኑ፥ ይህን ዝንባሌህን እንዴት ልትቀይረው ትችላለህ?

*** ስደትና ግፍ እየተፈጸመብህ ሳለ፥ እንደምን ክርስቲያናዊ ፍቅርን ለማሳየት ይቻልሃል?

# ምዕ. 6. ሙስሊሞችን ለመረዳት የሚጠቅም መሠረታዊ መረጃ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ እስልምና እምነትና ስያሜዎች አንዳንድ መሠረታዊ መረጃዎችን ለመስጠት እፈልጋለሁ። እነዚህም የሙስሊሞችን የአስተሳሰብ ዘይቤ ለመረዳት ጠቃሚ ናቸው። ይሁን እንጂ ማስታወስ የሚኖርብህ እምነትህን ለሙስሊሞች ማካፈል ከመጀመርህ በፊት እነዚህን መረጃዎች በሙሉ በቃል የመያዝ ግዴታ እንደሌለብህ ነው።

አላህ:- ማለት ሙስሊሞች እግዚአብሔር ለማለት የሚጠቀሙበት ቃል ነው፤ አላሁ አክበር (እግዚአብሔር ገናናው) ማለት ነው። ሙስሊሞች ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ያላቸው መረዳት የተወሰነ ነው። የፈጣሪነት ሚናውን፥ፈራጅነቱን እና ከሁሉም በላይ የሆነ ኃይል እንዳለው ይቀበላሉ፤ነገር ግን ከሰው ልጅ ምንም ግንኙነት እንደሌለው አድርገው ይቆጥራሉ። ስለ እግዚአብሔር ፍቅር የሚያውቁት ነገር የላቸውም። እንዲያውም ለሕያው እግዚአብሔር ፍጹም ተጻራሪ የሆኑ ሌሎች ባሕርያትንም ያላብሱታል። አላህ በመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለጠው ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ጋር አንድ ተደርጎ መወሰድ የለበትም።

እስላም:- ማለት በመሐመድ ለተመሠረተ ሃይማኖት የተሰጠ ስም ሲሆን በዓረብኛ ትርጉሙ መገዛት ወይም ራስን መስጠት ማለት ነው። ይህ አላህ የሚመለከበት ሃይማኖት ሲሆን፥ በዚህም አምልኮ ሙስሊሞች ሃይማኖታዊ ግዳጆችንና ሥነ ሥርዓቶችን እንዲሁም ሌሎች መልካም ተግባራትን በመፈጸም በእግዚአብሔር ተቀባይነትን ለማግኘት የሚሹበት ነው።

ሙስሊም:- ማለት የእስልምናን ሃይማኖት የሚከተል ሰው ማለት ሲሆን፥ ራሱን ለአላህ ፈቃድ አገልጋይ ወይም ባሪያ አድርጐ የሰጠ መሆኑንም የሚናገር ነው። ይህም ነው ለአንድ ሙስሊም ሕይወቱ አስቀድሞ የተወሰነና የተደነገገ ስለመሆኑ ለማመን የጸና መሠረት የሚሆነው። ወደፊት የሚደርስበት ማናቸውም ነገር፥ መልካምም ሆነ ክፉ የአላህ ፈቃድ ስለሆነ አሜን ብሎ የመቀበል ግዴታ

አለበት። ይህ እምነት የሚያመራው ሕይወትን የማይለወጥ አድርጎ ወደ መውሰድ እና ከዚህም የተነሣ ወደ ደንታቢስነት ዝንባሌ ነው።

መሐመድ፡- የእስልምና መሥራች ነው። በሙስሊሞች የመጨረሻና ታላቁ ነቢይ ተደርጎ ይከበር እንጂ አይመለከም። ይህ ሰው በዘመኑ የነበረው የጣኦት አምልኮ በጣም ስላንገፈገፈው፥ በአንድ አምላክ እምነት ላይ የተመሠረተ ሃይማኖት ለማምጣት ይጥር ነበር።

ቁርዓን፡- ሙስሊሞች እግዚአብሔር በመልአኩ ገብርኤል በኩል ለመሐመድ የሰጠው መገለጥ ነው ብለው የሚያምኑበት ቅዱስ መጽሐፋቸው ነው። በ7ኛው ምዕተ ዓመት ስለተሰጠ ሙስሊሞች ከእግዚአብሔር የተሰጠ የመጨረሻ መገለጥ እንደሆነና ትምህርቱም መጽሐፍ ቅዱስን የሚልቅ እንደሆነ ይናገራሉ። ትውፊቶች ደግሞ የመሐመድን ትምህርት የሚያንጸባርቁ ገለጻዎች ወይም ታሪኮች ናቸው።

የእስልምና አዓምዶች፡- እነዚህ አምስት ነጥቦች ማንኛውም ሙስሊም በታማኝነት ሊፈጽማቸው የተገቡ ሃይማኖታዊ ተግባሮች ናቸው።

1. (የሽሃዳ) የእምነት መግለጫ እንደሚከተለው ነው፡- «ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፤ እንዲሁም መሐመድ ደግሞ የአላህ መልእክተኛ ነው»። ይህንን የእምነት መግለጫ ደጋግሞ በመናገር ሙስሊም ያልሆነ ሰው ሙስሊም ሊሆን ይችላል።

2. (ሳላት) ከሥርዓታዊ መንጻት በኋላ በየቀኑ አምስት ጊዜ የሚደረግ ሥርዓታዊ ጸሎት ነው። በየሳምንቱ የሙስሊሞች የበዓል ቀናት በሆነው በዕለተ-ዓርብ በመስጊድ እየተገኙ መጸለይ የተለየ ዋጋ ያሰጣል።

3. (ዛካት እና ሰደቃ) በፍቃደኝነትና በሕጋዊነት የሚሰጥ ምጽዋት ነው።

4. (ረመዳን) ከፀሐይ መውጣት ጀምሮ እስከ ፀሐይ መጥለቅ ድረስ ምንም ምግብና ውኃ የማይወሰድበት የጾም ወር ነው። ሙስሊሞች የጾሙ ሥነ -ሥርዓት ከፍ ያለ ዋጋ ወይም ሽልማት እንዳለው ያምናሉ፤ ይሁን እንጂ በምሽት ከፍተኛ ድግስ ያደርጋሉ።

5. (ሐጅ) በሃይማኖታዊ ጉዞ ወደ መካ በመሄድ በተወሰኑ ሥነ -ሥርዓታዊ ሂደቶች ውስጥ ማለፍ ነው። በባህል እንደሚታመነው ለሃይማኖታዊው ተጓዥ የሚሰጠው ሽልማት ገነት ነው።

# የክርስቲያንና የሙስሊም ሃይማኖታዊ ጽንሰ አሳቦች ንጽጽር

ተመሣሣይ ቃላትን ስለምንጠቀም አንዱ ቃል ለሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ሊሰጥ የሚችለውን የተለያየ ትርጉም መገንዘብ ያስፈልጋል። (ከዚህ በታች ያለው ሠንጠረዥ ፊል ፓርሻል በሴሚናር ላይ ካቀረበው መረጃ በማስፈቀድ የተወሰደ ነው። ስለ ስያሜዎቹ የበለጠ ዝርዝር በአባሪ መ ተሰጥቷል። «ቃላትን በጥንቃቄ ተጠቀም»።)

| ቃል | ሙስሊም | ክርስቲያን |
|---|---|---|
| እግዚአብሔር | የራቀ፥ ወላዋይ፥ መሐሪ፥ ሁሉን ቻይ | የግል፥ አፍቃሪ፥ ጻድቅና ፈራጅ |
| ኢየሱስ ክርስቶስ | ነቢይ | መለኮት፥ እግዚአብሔር |
| መጽሐፍ ቅዱስ | ከእግዚአብሔር የተሰጠ መገለጥ፥ የተለወጠና የተበረዘ | ሙሉ ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ቃል |
| ሥላሴ | እግዚአብሔር፥ ማርያም፥ ኢየሱስ | አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ |
| እምነት | በእግዚአብሔርና በመሐመድ | በኢየሱስ እንደ አምላክነቱና እንደ አዳኝነቱ |
| ኃጢአት | ውርደት፥ ደካማነት፥ መጥፎ ተግባራት | በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ፥ ኃጢአተኛ ባሕርይ |
| ደኅንነት | በእምነትና በሥራ፥ ዋስትና የለም | በክርስቶስ በማመን፥ ዋስትና አለው |
| ቅድስና | በሥርአታዊ ነገሮችና በታዛዥነት ላይ ማተኮር | በመታዘዝና በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ትኩረትን በመስጠት |
| ልዕለ–ተፈጥሯዊ ኃይላት | የመናፍስት ዓለም ፍራቻ | በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ የተመሠረተ እምነት |

ለአንድ ዓይነት ሥነ መለኮታዊ ቃላት የሚሰጡትን የተለያዩ ትርጉሞች ነቅቶ ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። ሙስሊሞች ሊያስፋፉ ከሚጥሯቸው አሳቦች አንዱ በሁለቱም ሥርዓቶች የሚመለከው አንድ አምላክ ስለሆነ ክርስትናና እስልምና አንድ ናቸው የሚል ነው። ይህ ትምህርት ሊፈተን የሚችለው እንዴት ነው? ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ሙሉ ሥልጣን ወዳለው መጽሐፍ ቅዱስ መመልከት ያሻናል።

አንድ ገንዘብ የሐሰት መሆኑ ከተጠረጠረ ከእውነተኛው ጋር በማስተያየት ይጣራል! አጣሪውም ከእውነተኛው ገንዘብ የሚለይባቸውን ሁኔታዎች አንድ በአንድ ይመለከታል። አንድም ልዩነት ከታየ የሐሰት መሆኑ ይጋለጣል። ይህን መርህ በመከተል ለምሳሌ ስለ እግዚአብሔር ባሕርያት ሙስሊም ያለው መረዳት በሚመዘንበት ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱሱን እግዚአብሔር የማያመልኩ መሆናቸው በገሃድ ይታወቃል። ከላይ በሠንጠረዡ የተጠቀሱትን ሌሎች ሥነ መለኮታዊ ቃላት በተመሣሣይ መንገድ በመፈተን እስልምና መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው መሠረታዊ የእምነት ፍንገጣዎች እንደሚታዩበት ለማረጋገጥ ይቻላል።

## «ልማዳዊ» እስልምና

በዚህ ምዕራፍ እስካሁን ድረስ የተሰጠው መረጃ የትክክለኛውን እስልምና መሠረታዊ እምነቶች ያጠቃለለ ነው። ይሁን እንጂ ራሱን ሙስሊም ነኝ ብሎ የሚጠራው ሰው ሁሉ እነዚህን ትምህርቶች ሊረዳ ወይም የእምነቱ መግለጫ አድርጎ ሊናገር አይችልም። በእስልምና በደንብ የተካኑ ስለ እምነታቸው ምስክርነት መስጠት ቢችሉም፥ አብዛኛዎቹ ግን ስለ ትክክለኞቹ የእምነት ትምህርቶች ያላቸው እውቀት በጣም አነስተኛ ነው። የሚከተሉት ልማዳዊ እስልምናን ሲሆን ይህ በመሠረቱ በባዕድ አምልኮ ላይ ያተኮረ ሆኖ፥ ዳሩ ግን ውጪአዊ ገጽታው በእስልምና ተግባራት የተለበጠ ነው። ሌሎቹ ደግሞ በስም ክርስቲያኖች እንዳሉ ሁሉ፥ በስም ሙስሊም የሆኑ ብቻ ናቸው። በእነዚህ የተለያየ የእምነት ደረጃ ባላቸው ቡድኖች ውስጥ ወንጌልን በምታደርስበት ጊዜ የውስጥ ጉድለታቸውን (ፍላጐታቸውን) በተለያዩ መንገዶች ይገልጹልህ ይሆን ይሆናል። ይሁን እንጂ ለእነዚህ ችግሮቻቸው መፍትሔ ለመሻት ማተኮር ያለብህ በክርስቶስ ላይ እንጂ በሥነ መለኮታዊ እምነቶቻቸው ላይ መሆን የለበትም።

የምታውቃቸው ተራ ሙስሊሞች ምናልባት «ልማዳዊ» እስልምና የሚለማመዱ ሊሆኑ ይችላሉ። የእምነት አቋማቸውን በቃል ሊደግሙ፥ ሥርዓታዊ ጸሎቶችን ሊጸልዩ፥ የረመዳንን ጾም ሊጾሙ፥ ወዘተ. ይችላሉ። ግን በዚህ ሁሉ

ውስጥ የርኩሳን መናፍስት (ጂኒ) እና የሰይጣን ኃይል ፍራቻ ሰፍኖባቸዋል። የርኩሳን መናፍስትን ኃይል እንዲከላከልላቸው ከቁርዓን የተወሰነ ክፍል የተጻፈበትን ኪታብ በሰውነታቸው ሊያስሩ ይችላሉ። ለሕመም፥ ምቀኛን ለማራቅ፥ እንዲሁም ለሌሎች በሽታዎች «ቅዱስ ሰው» ወይም ጠንቋይ (ሻማን) ያማክራሉ። ስለዚህ የሚኖሩት በአስማት ወይም በአምልኮተ- ባዕድ እስራት ውስጥ ነው።

በሁሉም አገር ያሉ እስላሞች ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ ቁርዓንን በዓረብኛ በቃል እንዲያጠኑ ይገፋፋሉ። የዓረብኛ ቋንቋን ወይም የቁርዓንን ትምህርት ላይረዱት ቢችሉም በቃላቸው ግን ይሸመድዱታል። ቁርዓን ለመሐመድ ቃል በቃል ከእግዚአብሔር እንደ ተሰጠ ስለሚያምኑ፥ እያንዳንዱን ቃል በፍርሃት ያከብሩታል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ስለ ትክክለኛው እስልምና ያለው መረዳት አነስተኛ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም አንዳንዶቹ ለሕልሞችና ራእዮች የተለየ ስፍራ ይሰጣሉ። በክርስቶስ የተለወጡ ሙስሊሞች በሚሰጡት ምስክርነት፥ አንዳንዴ «ነጭ አንጸባራቂ ልብስ የለበሰ ሰው» በራእይ እንደሚገለጥላቸው ይገልጻሉ። እርሱም ስለ ክርስቶስ የበለጠ ለመረዳት የሚያስችሉአቸውን መመሪያዎች እንደ ሰጣቸው ይህም በመጨረሻ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ማመን እንደመራቸው ይመሰክራሉ። እግዚአብሔር ራሱን ለሙስሊሞች በዚህ ልዩ መንገድ እንዲገልጥላቸውና ይህ መንገድ ክርስቶስን ከልብ እንዲፈልጉት ምሪት እንዲሆናቸው እኛም እንጸልይላቸዋለን።

## እስልምና የሕይወትን ሁለንተናዊ ገጽታ ያጠቃልላል

እስልምና ጥርት ያለ የአኗኗር ዘይቤ መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው። ሙስሊሞች የእነርሱ ማኅበረሰብ (ኡማ) «ለሰዎች ከተለየች ሕዝብ ሁሉ በላጭ ኾናችሁ፤...» (ቁርዓን 3፡110) እንደተባለለት እንደሆነ ያምናሉ። የዚህ ማኅበረሰብ ፍሬዎች የሚገለጡት በትክክለኛ ባሕርይ፥ አቀራረብ፥ አለባበሶች፥ መስተንግዶና ቤተሰባዊ ትስስር ነው። እስልምና ሁሉንም የሕይወት ገጽታዎች ማለትም ሃይማኖታዊ፥ ሥነ-ምግባራዊ፥ ማኅበራዊ፥ ባህላዊ፥ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ዘርፎችን የሚያጠቃልል ነው። በሕይወታቸው ባለው በማንኛውም ጊዜ፥ ማለትም በቀን 24ቱን ሰዓት ከመወለዳቸው እስከ መሞታቸው ድረስ በሙሉ፥ እስልምና በተከታዮቹ ላይ የባሕርይ ጫና ያሳድርባቸዋል ለማለት ይቻላል። አንድ

ሙስሊም እንዲሁ ራሱን የቻለ ግለሰብ ብቻ ሳይሆን፥ በጥብቅ የተዋቀረው ማኅበረሰብ አባል፥ በዚያም ውስጥ እንደገና እጅግ የጠበቀ የቤተሰብ አባል ነው።

አንድ ክርስቲያን የሆነ ዓረብ ስለ እስልምና በማናቸውም የሕይወት ዘርፎች ጣልቃ ገብነት የሚከተለውን ጽፏል።

«አንድ ሙስሊም ሙስሊም የሆነው ከሙስሊም ቤተሰብ ስለ ተወለደ ነው። ራሱን ከኅብረተሰቡ፥ ከባህሉ እና ከፖለቲካው ሥርዓት ጋር በማመሳሰል የሙስሊምነት መለያውን ይቀዳጃል። «እስልምና» ሲባል ራሱን ለአላህ ፈቃድ ማስገዛቱን የሚያረጋግጥበት ሲሆን፥ በተግባር ግን ራሱን ለአጠቃላዩ የእስልምና ሥርዓት የሚያስገዛበት ነው። ይህም እስላማዊ ሕግን፥ ባህላዊ ልማዶችን፥ ማኅበራዊ እና ቤተሰባዊ ምኞቶችን፥ እንዲሁም ሃይማኖታዊ እምነቶችንና ተግባሮችን ያጠቃልላል። ይህም ማለት በእስላማዊ አገዛዝ ሥር ማንኛውም ሙስሊም በጊዜው ለሚሠለጥኑት ኃይላት ሙሉ ለሙሉና ያለ ጥያቄ ራሱን ማስገዛት አለበት። እስላማዊ ሕግ ጥብቅ ስለሆነ ለግላዊ ምርጫዎች ምንም ስፍራ አይሰጥም።»*

* የሙስሊም አመለካከት፥ በጆርጅ ሆስኔ፥ ወንጌል ስርጭት፥ ቅጽ 4 ቁ. 3፥ 4፥ 1990. (A Muslim's World View, by George Houssney, REACHOUT, Vol. 4 No. 3, 1990.)

## የቤተሰብ ክብር አስፈላጊነት

ሙስሊሞች ስለ «ክብራቸው» ወይም ስለ ቤተሰባቸው ከፍተኛ ግምት ስለሚሰጡ መጠንቀቅ አለብህ። የጠበቀ የቤተሰብ አቋም ስላላቸው አንዱ አባል የተሳሳቱ ተግባራት ቢፈጽም፥ ለመላው ቤተሰቡ ታላቅ የእፍረት ምንጭ ይሆናል። ትዳሯ ስላልተስማማት ባሏን ጥላ በምትኮበልል ሚስት፥ አርግዛ የምትገኝ ወጣት ልጃገረድ፥ በትምህርታቸው የሚወድቁ ልጆች እንኳ ሳይቀሩ የቤተሰቡን ክብር እንደሚያጎድፉ ተቆጥረው ጠበቅ ያለ እርምጃ ከሚወሰድባቸው ነገሮች መካከል ዋነኞቹ ናቸው። በአንዳንድ አገሮች ጋጠወጥ የሆነውን የቤተሰብ አባል መግደል በሕግ ፊት የቤተሰቡን ክብር ለመመለስ እንደ ተወሰደ ሕጋዊ እርምጃ ተቆጥሮ ሙሉ ተቀባይነት አለው። በሕዝብ ፊት መዋረድ በጣም የሚያሸማቅቃቸው ነገር ነው። ይህ ማለት የአንድ ቤተሰብ ወይም የአንድ ሰው፥ በተለይም የአባወራው ኃጢአት በምንም መንገድ በሕዝብ ፊት መነገር የለበትም። ከሁሉም በላይ ደግሞ በእነርሱ ዘንድ አንድ ሰው እስልምናን ተወ ማለት የመጨረሻ ውርደት እና የክብር መጉደፍ ነው። በመላው ቤተሰብ ላይ ገሃድ እፍረት ስለሚያስከትል ሁሉም ለዚህ

ምክንያት የሆነውን ሰው ማጥፋት ወይም መግደል ኃላፊነታቸው እንደሆነ ይሰማቸዋል።

ይህ ከላይ የቀረበው መረጃ አንድ ሙስሊም ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲመለስ ጥሪ በሚቀርብለት ጊዜ በውስጡ ስለሚፈጠሩ በርካታ ግጭቶች እንድንረዳ እገዛ ያደርጋል። ለቤተሰብ፥ ለኅብረተሰብ እና ለእስላማዊ ሕግ ባለው ታማኝነት መካከል በመወጠር ይፍረከረካል። ሙስሊሞች ወደ ክርስቶስ እንዳይመጡ እና የተለወጡትም እምነታቸውን ግልጽ እንዳያወጡ ለምን እንደሚቸገሩ ይህ ዝግ ሥርዓት በሚገባ ያብራራዋል። እነዚህ ሁሉ ውጊያዎች በሥጋ በኩል ሲሆኑ አንድ ሙስሊም በክርስቶስ ሲያምን የሚነሡ መንፈሳዊ ውጊያዎችም አሉ። ይህ ርዕስ በምዕራፍ 13 በሚገኘው በመንፈሳዊ ውጊያ ሥር በበለጠ ይብራራል።

## በጥልቀት የሚታሰብ

*** ስለ አንድ ተመሣሣይ ቃል ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ያላቸውን የጽንሰ አሳቦች ልዩነት በተመለከተ ጥናት አድርግ። ለምሳሌ «እግዚአብሔር»፥ «ኃጢአት»፥ ወዘተ (ሠንጠረዡን ተመልከት።)

*** «እስልምና ጥሩ ሃይማኖት ነው። ሥነ ምግባራዊ ሕጐችንና ሠናይ ምግባሮችን ያራምዳል» ስለተሰኘው አባባል ምን ምላሽ ትሰጣለህ?

*** አንድ ሰው፥ «ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች በመሠረቱ አንድ ናቸው፤ ምክንያቱም የሚያመልኩት አንድ አምላክ ነው» ቢልህ ምን ትመልስለታለህ?

# ክፍል 2
# ለሙስሊሞች መመስከር

## ምዕ. 7 ድንገት ለሚያጋጥሙን መመስከር

ድንገት ለሚያጋጥሙን ሙስሊሞች ቀላሉ የመመስከር ዘዴ የመጽሐፍ ቅዱስን የተወሰነ ክፍል የያዘ ጽሑፍ መስጠት ነው። ይህ ፈቃደኛ በሆነ በማንኛውም ሰው ያለ ብዙ ድካም ሊከናወን ይችላል። በወዳጅነት መንፈስ በመመራት ድንገት ከሚገጥምህ ሰው ጋር የውይይት ዕድል ክፈት። እንዲህ ዓይነቶችን ሰዎች በአውቶቡስ ወይም በታክሲ ስትሄድ፥ ወይም አስቤዛ በምትሸምትበት ገበያ ስፍራ ልታገኛቸው ትችላለህ። ወይም ከሙስሊም ቤተሰብ ተጐራብተህ ልትኖር፥ በሥራ ቦታ ወይም በትምህርት ቤት ልትገናኛቸው ትችል ይሆናል። በዚህ ዓይነቱ አጋጣሚ የሚፈጠረው ጭውውት የወዳጅነት መንፈስ የሰፈነበት ከሆነ ውይይቱን ወደ መንፈሳዊ ጉዳዮች ለመምራት መሞከሩ ይጠቅማል።

ለድንገተኛ ሰው ስለሚደረግ ምስክርነት የግሌን ምሳሌ ላቅርብልህ። በአንድ ወቅት እኔና ባለቤቴ በሕንድ አገር በምትገኝ ከተማ በአየር ማረፊያ የእንግዶች መቀበያ ውስጥ ተገኝተን ነበር። አጋጣሚውም ባለቤቴ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደምታገለግልበት ሆስፒታል ለመብረር አውሮፕላን የምንጠባበቅበት ነበር። በአለባበሳቸው ሙስሊም መሆናቸው በቀላሉ የሚታወቅባቸው በርከት ያሉ ሰዎች አብረውን ይጠባበቁ ነበር። እኔም ስለ ክርስቶስ ልመሰክርላቸው ስለፈለግሁ ከመካከላቸው አንዱን ባናግረውም፥ እርሱ ግን የቡድናቸው መሪ ወደሆነው አንድ መልከ መልካም ወጣት አመለከተኝ። ወዳጃዊ ሰላምታ ከተለዋወጥንና የእርስ በርስ ትውውቅ ካደረግን በኋላ፥ በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ለመነጋገር ፈቃደኛነቱን ገለጸ። ይህ ዝንባሌ ደግሞ የሙስሊሞች ዓይነተኛ መለያ ነው። እኔም በግል ሆነን ለመነጋገር እንዲያመቸን ወደ ዳር ፈንጠር እንድንል አደረግሁት። ከዚህ ወረድ ብሎ የተመለከተውን ውይይት አደረግን፡-

«ክርስቲያን ነህ?» ብሎ ጠየቀኝ።

«አዎን ነኝ» ብዬ መለስኩለት። «አንተስ ሙስሊም ነህ?»

«አዎን ነኝ።»

«ጥያቄ ልጠይቅህ?» ስል ተዳፈርኩት።

«ደስ ይለኛል» አለና መለሰልኝ።

«እግዚአብሔርን ታውቃለህ?»

«አዎን አውቃለሁ፣» በማለት ፈጠን አለና አረጋገጠልኝ።

«ታዲያ ይኼ ታላቅ መታደል አይደለም?» አልኩት። «እኔ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ሰው መገናኘት በጣም ደስ ይለኛል። እስኪ ንገረኝ፣ እግዚአብሔርን የምታውቀው እንዴት ነው?»

መልስ ሊሰጠኝ በሚታገልበት ጊዜ ሁሉ በፊቱ ላይ ግራ የመጋባት እና የመደናገጥ ስሜት ወርሮት እንደ ነበረ በቀላሉ ተመልክቻለሁ። እግዚአብሔርን በግሉ በትክክል አለማወቁን ለመረዳት የተገደደበት የመጀመሪያው ጊዜ አሁኑ መሆን አለበት ስል ተገረምኩኝ። ምናልባት፣ የሚያውቀው ቢኖር እስልምና ስለ እግዚአብሔር የሚያስተምረውን ብቻ ለመሆኑ በልቡ ብልጭ ብሎ ሳይታየው አልቀረም ይሆናል። ዳሩ ግን ከሕያው እግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት እንዳልነበረውና የፍቅሩና የእንክብካቤው አስተማማኝነት አንድም ጊዜ ተሰምቶት እንደማያውቅ ግልጽ ነው።

ውይይታችን ቀጥሎ ፍሬያማ መቋጫ እንዳስገኘ መናገሩን በወደድኩኝ ነበረ። ግን እኔ እንደተመኘሁት ጭውውታችን አልቀጠለም። ሆኖም በዚያ ግንኙነታችን እንኳ ሰውዬው ስለ እግዚአብሔር በበለጠ ለመረዳት ምኞት እንዳደረበት አልጠራጠርም። ምክንያቱም ወደ ኢትዮጵያ ለመብረር ተሳፈሩ የሚለው ማስታወቂያ የተነገረው ላቀረብኩለት ጥያቄ አንድም መልስ ሳይሰጠኝ በመሆኑ ነው። ወዲያውኑ ተጨባብጠን ተሰናብቼው ተለየሁት። ይሁን እንጂ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ለዚያ ወጣት ሰው እንድጸልይ በልቤ ውስጥ ሸክም አኑሮአል። እግዚአብሔር በእስልምና ሊታወቅ ያለመቻሉ ግንዛቤ እውነትን እንዲፈልግ እንዲያደርገውና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእውነት እግዚአብሔርን እንዲያውቅ ጸሎቴ ነው።

ይህ ግንኙነት የተደረገው ፍጹም እንግዳ ከሆነ ሰው ጋር ወዳጅነት በሰፈነበት መንፈስ መሆኑን እንደምትረዳ አልጠራጠርም። ሁኔታው የተጠናቀቀው ምንም ዓይነት አለመግባባት ሳይፈጠር ነው። ርዕሰ ጉዳዩ ሰውየው እግዚአብሔርን በግሉ ለማወቅ ባለው ውስጣዊ ፍላጐት ላይ ያተኮረ ነበር። የውይይቱን አቅጣጫ እኔ

ስለመራሁት ስለ እስልምና የተጠቀሰ ምንም ነገር አልነበረም። ዳሩ ግን ከጊዜው መጣበብ የተነሣ ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባብ ሳልሰጠው በመቅረቴ ቅር መሰኘቴ አልቀረም።

የሚቀጥለው ታሪክ ፍሬቢስ በሚመስል ግንኙነት ተጀምሮ አስደናቂ ውጤት ስላስገኘው የደብሊዩ ኤም ሚለር ስሜት የሚነካ ልምምድ የቀረበ ዘገባ ነው።

«ወጣት ሚስዮናዊ በነበርሁ ጊዜ በኢራን በምትገኘው የሴይስታን ከተማ ውስጥ ቅዱሳት መጻሕፍትን ላልተማሩና ግትር ለሆኑ ሙስሊሞች ለመሸጥ በቆሻሻማው የገበያ ስፍራ እየተዟዟርኩ ጥቂት ወራትን አሳልፌ ነበር። በዚህ ጊዜ ፍላጐት ያደረባቸውን ገገሮች እንዳገኝ ብጸልይና ተስፋ ባደርግም አንድም ሰው ከቶ አልቀረበኝም። ያ ጊዜ በሕይወቴ ከገጠመኝ ተስፋ መቁረጥ ሁሉ መራራውና እጅግ አስቸጋሪው ጊዜ ነበር።»

ከብዙ ዓመታት በኋላ ዶክተር ሚለር ወደዚሁ ስፍራ ተመልሶ ኖሮ፣ አንድ ወጣት መጻሕፍት ሻጭ «የምነግርህ የምስራች አለኝ! በሴይስታን ክርስቲያን የሆነ ሰው አግኝቼአለሁ። እርሱም በአፍጋኒስታን ወሰን ላይ የአንድ ጐሣ አለቃ የሆነ የተከበረ ሰው ነው» በማለት አወጋው።

ዶክተር ሚለር ይህንን የጐሣ አለቃ (ሳርደር) ባገኘው ጊዜ፣ «ስለ ድፍረቴ ይቅርታ ይደረግልኝና ክርስቲያን መሆንህን ሰምቼአለሁ። ስለ ክርስቶስ ማን እንደነገርህ መልካም ፈቃድህ ሆኖ ልትነግረኝ ትችላለህ?» ሲል ጠየቀው።

«አዎን» በማለት መለሰ የጐሣ አለቃው። በመቀጠልም፣ «ለሃያ ዓመታት ክርስቲያን ነበርሁኝ። ዳሩ ግን ስለ ክርስቶስ የነገረኝ ማንም ሰው አልነበረም» ሲል አከለበት።

«ታዲያ እንዴት ክርስቲያን ለመሆን በቃህ?» በማለት ዶክተር ሚለር በመገረም ጠየቀው።

«መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ» አለና መለሰለት።

«ግን መጽሐፍ ቅዱስን ከየት አገኘህ?» ሲል ጠየቀው ዶክተር ሚለር።

የጐሣ አለቃው (ሳርደሩ) ፈገግ ካለ በኋላ ዝግ ብሎ «ከአንተ ነው ያገኘሁት» አለው።

«የምትለው በሴይስታን ከሃያ ዓመታት በፊት በነበርኩበት ጊዜ ከእኔ ጋር ተገናኝተህ መጽሐፍ ቅዱስ ገዝቼሃለሁ ነው?»፥ በማለት ዶክተር ሚለር አሁንም በአድናቆት ጠየቀው።

«አዎን» ሲል መለሰ። «የአስራ ስድስት ዓመት ልጅ ሳለሁ ወደ ክፍልህ መጣሁኝና ትልቅ የፋርሲ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስ እንድትሸጥልኝ ጠየቅሁህ። አንተም አንዱን ቅጂ ከሸጥህልኝ በኋላ የእግዚአብሔር ቃል ስለመሆኑና በአክብሮት መያዝ እንዳለበት ነገርኸኝ። ቤቴ ወደሚገኝበት መንደር ወስጄ በግሌ አነበብኩትና በክርስቶስ አመንሁ። ከሰባት ዓመታት በኋላ እዚህ ከነበሩት የእንግሊዝ ሚሲዮናውያን መካከል አንዱ አጠመቀኝና ቅዱስ ቁርባንም ሰጠኝ። በዚህ ጊዜ በቤቴ ግብዣ አዘጋጀሁና ሌሎች የጐሣ አለቆችን ጠራሁ። ክርስቲያን መሆኔን ለማሳየት ብዬ በግድግዳው ላይ መስቀል ሰቀልሁ።»*

* ለእስልምና የክርስቲያን ምላሽ፥ በዊልያም ኤም ሚለር፥ ዊተን፥ ኤናውዎይ አይ ኤል ቲዶል ሃውስ አሳታሚዎች፥ 1976 ገጽ 112-114። (A Christian's Response to Islam, by William M. Miller, Wheaton, IL.: Tyndale House Publishers, 1976, pp. 112-114)

ይህ ታሪክ፥ በታማኝነትና በጸሎት መንፈስ ዘርን ስለ መዝራት እንዴት ያለ ማበረታቻ ነው! «ወይም ይህ ወይም ያ ማናቸው እንደሚበቅል ወይም ሁለቱም መልካም እንደሚሆኑ አታውቅምና በማለዳ ዘርህን ዝራ፥ በማታም እጅህን አትተው» (መጽሐፈ መክብብ 11፡6)። ስለ ዘሪው በተሰጠው ምሳሌ ላይ ጌታ ኢየሱስ «ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል ነው» (ሉቃስ 8፡11) አለ ። ዘር ፍሬን ሊሰጥ የሚችለው በተዘራ ጊዜ ስለሆነ ማንኛውም ክርስቲያን መዝራት ይገባዋል።

## እንገብጋቢ መንፈሳዊ ፍላጐቶችን መጠቀም

መንፈሳዊ ፍላጐቶችን በማሟላት ረገድ እስልምና የቱን ያህል ደካማ ስለመሆኑ የሚከተለው ታሪክ ቁልጭ አድርጐ ያሳያል። ታሪኩም «የእስልምና ተገዳርት» በሚል ርዕስ ሲ. አር ማርሽ* በጻፈው አስደናቂ መጽሐፍ ውስጥ ተዘግቦ የሚገኝ ነው። ማርሽ እና ባለቤቱ በአልጄሪያ ለብዙ ዓመታት ሚሲዮናውያን ነበሩ። ማርሽ በየመንደሮቹ በመዘዋወር ስለ ጌታ ኢየሱስ ከወንዶች ጋር ይነጋገር ነበር።

«የሚቀጥለው መንደር አምስት ኪሎ ሜትር ይርቅ ነበር፤ እናም በዚያ እውሩ ሐሚድን ጥቂት ሰዎች ከብበውት አገኘሁ። እርሱም በዘንጉ እንቅስቃሴ

ጭምር ለንግግሩ ትኩረት በመስጠት የቁርዓንን አስተምህሮት ያብራራላቸው ነበር። ከመወለዱ ጀምሮ በእውርነት የተጠቃ በመሆኑና መሥራት ባለመቻሉ በቁርዓን ትምህርት ቤት ብዙ ዓመታት አሳልፏል። በመሆኑም ሌሎች የቅዱስ መጽሐፋቸውን ቃል መስመር በመስመር ሲደግሙት ስለሰማ እርሱም በቃሉ እስከሚወጣው ድረስ ለማጥናት ቻለ።

ከዚህ በተጨማሪም በአካባቢው ሼኮች ዘንድ ተወዳጅ የሆነውን ክርክርና የእስልምናን አስተምህሮት ያውቅ ነበር። እኔም ከሰዎቹ ጋር አብሬ ተቀመጥኩኝ። ይህ ዓይነ ስውር ሰው ንግግሩን አቆመና ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል የወንጌልን መልእክት በአጽንኦት አዳመጠ። ከዚያም እንደ እሳት በሚጋረፍ አንደበቱ የጥያቄ መዓት ያወርድብኝ ጀመር። አንዳቸውንም እንኳ እንድመልስ ፋታ አልሰጠኝም። የእኔን መልስ ለማዳመጥ አልፈለገም ነበር። ዓላማውም እርሱ እንኳ ዕውሩ ሰው ሃይማኖቱን የቱን ያህል ጠንቅቆ እንደሚያውቅ ለማሳየት ነበር። ደግሞም በዚህም ብሎ በዚያ እነዚያ ሰዎች እኔ ያመጣሁትን የሕይወት መልእክት ከመስማት እንዲገቱ ማድረግ ነበረበት። ርኅራኄንና ፍቅር ለማሳየት ብዬ ጥያቄዎቹን ለመመለስ የተቻለኝን አደረግሁ። እርሱ ግን ስሜቱ ይብስ እየጋለበት ሄደ፤ ስብሰባውም ዋጋ ወደሌለው ንትርክ አሽቆለቆለ። በዚያን ጊዜ ግን ተደጋጋሚ ስኬት ባስገኘልኝ አንድ ዘዴ ለመጠቀም ወሰንሁ።

«ወዳጄ፥ እስኪ መሐመድ ፈጽሞልኛል ስለምትለው ነገር ንገረን። ይህንንም ለማድረግ እስከ አሥር ደቂቃ ድረስ ምንም ሳልናገር በትዕግሥት እጠብቅሃለሁ። ከዚያ በኋላ ደግሞ ክርስቶስ ለእኔ ያደረገውን ስለምነግርህ በተራህ ለአሥር ደቂቃ ታዳምጠኛለህ» በሚል ከስምምነት ላይ ደረስን።

«ሐሚድ አንተ ቀድመህ ተናገር» ስል ጋበዝሁት።

እርሱም ንግግሩን ጀመረ፤ «መሐመድ ስለ እርሱ እንድንመሰክር፥ በቀን አምስት ጊዜ እንድንጸልይ፥ እንድንጾም፥ ምጽዋት እንድንሰጥ፥ ቁርዓንን እንድናነብ ነግሮናል። ለእኛ ለሙስሊሞች ያደረገው ይኸንን ነው።»

«በተለይ ለአንተ፥ ያደረገልህን ንገረን እንጂ!» በማለት በጥሞና ጠየቅሁት።

ሙሉ ደቂቃ አለፈ፤ ይሁን እንጂ ሐሚድ ምንም ተጨማሪ የማሰላሰያ ጊዜ አላስፈለገውም ነበር። ስለምን መሐመድ እንዲያደርግ ቃል በቃል የነገረው ይህንኑ ያክል ብቻ በመሆኑ ነው። እኔ ግን ዝምታውን እንዳጤንኩኝ፥ በልቤ ለአዳኜና ለእነዚያ ሰዎች ከተቀጣጠለው ፍቅር በመነሣት ያደረገልኝን ሁሉ በቀላል መንገድ

ነገርኳቸው። «ጌታ ኢየሱስ አድኖኛል። ሕይወቴን ለውጧል። የዘወትር ወዳጄና ጓደኛዬ ነው። ምልአት ያለውና ደስተኛ ሕይወት ሰጥቶኛል። እንደዚሁም የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እንድከተል ብርታታ የሚሰጠኝ ከመሆኑም፥ ለውድቀቴም የይቅርታ ዋስትና አስገኝቶልኛል። ጠላቶቼን እንድወድድ አስተምሮኛል። ለአርባ ዓመታት ብቻ ሳይሆን ለዘላለም ለመግዛት ወደ ምድር በቶሎ ይመጣል። ከእርሱ ጋር እንድሆን ሊወስደኝ ይመጣል።» በዚህ ወቅት ምስኪኑና ዕውሩ ሐሚድ ራሱን መቆጣጠር ተስኖት ነበር። በስድብ ላይ ስድብ በማውረድ ረገመኝ፤ ተፋብኝ። እኔም ንግግሬን መቀጠሉ ፋይዳ ቢስ መሆኑን በመረዳት በዚሁ ገታሁት።

የመንደሪቱን ጕዳና አቋርጬ በምጓዝበት ጊዜ ሁሉ የሚታወሰኝ፥ ያ የሐሚድ የጥላቻ አመለካከት፥ ንግግሩን ተከትሎ የሚወራጨው በትሩ፥ ምሬት በተሞላው ሁኔታ የረገመኝ እርግማንና ምራቁን የተፋብኝ ሁኔታ ነበር። ያ እራሱ ከመሃይም የማይሻለው ሐሚድ፥ ብጤዎቹን ሙስሊሞች ለማስተማር ያደርግ የነበረው ጥረት፥ ዕውርን ዕውር ከሚመራበት ሁኔታ ያልተለየ ነበር። በጥልመት በተሰወሩት በእነኛ ዓይኖቹም ላይ የሚነበበውን የጥላቻና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ለመግለጽ ያስቸግራል። ምናልባትም በዚህ መንደር በአንድ ዓይነ ስውር መሪነት የገጠመኝ ተቃውሞ በሌላኛው መንደር ደግሞ ጥልቅ የልብ ጥማት ባላቸው አድማጮች እንደሚካካስ ተስፋ በማድረግ ወደ ቀጣዩ መንደር ተጓዝሁ። የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ በሐዋርያት ሥራም ተመሣሣይ መልክ ነበረው።

* የእስልምና ተግዳሮት፥ በሲ. አር ማርሽ፥ ሎንዶን፡ ቃለ እግዚአብሔር ማኅበር፥ 1980፥ ገጽ 31-33። (The Challenge of Islam, by C R Marsh, London: Scripture Union, 1980, pp. 31-33.)

የዚህ ዓይነቱ የምስክርነት ዘዴ፥ ለሙስሊሞች አንገብጋቢ መንፈሳዊ ፍላጐቶቻቸው ሃይማኖታቸው መልስ እንደማያስገኝላቸው የማሳያው አንደኛው መንገድ ነው። በርግጥ ማድረግ ስለሚገባቸው ነገሮች ተነግሯቸዋል፤ ግን ለመታዘዝ የሚያስችላቸው ኃይልና ለችግሮቻቸው አስተማማኝ መፍትሔ አልተሰጣቸውም። አንድ ገጣሚ በሚከተለው መንገድ ገልጾታል።

አድርግና ኑር ነው የሕጉ ግዳጅ፥

ታዲያ ምን ያረጋል አልሰጠኝም እንጂ እግር ወይም እጅ።

የላቀ ነው ቃሉ ወንጌል የሚሰጠኝ፥

ከንፍን አቀዳጅቶ መብረር የሚያስችለኝ።

ከላይ ከተጠቀሰው ገጠመኝ የምንማረው ፍሬ ነገር፣ አንድ ውይይት ወደ ንትርክ ከተለወጠ መቀጠሉ ፋይዳ እንደሌለው ነው። በወዳጅነትህ መጀመሪያ ላይ ለሙስሊሙ ማረጋገጥ ያለብህ ተከራክረህ ልትረታው ከመሞከር ይልቅ ወዳጅነቱን ማትረፍ እንደሚበልጥብህ ነው። ይህ ሽንፈትን መቀበል አይደለም። በወዳጅነት መንፈስ እንዳላችሁ መለያየቱ ለአንተም ሆነ ለሌላው ክርስቲያን ወደፊት ሊመሰክርለት እንዲችል መንገዱን ከፍት ያደርጋል።

የዚህ ዓይነቱ በግል የሚካሄድ ቃሉን የማካፈልና የምስክርነት ውጤት ገሃድ የሚወጣው በዘላለማዊው ፍርድ ዕለት ብቻ ነው። ሆኖም ግን ያ ቀን እስከሚደርስ፣ ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ ለዓለም ሁሉ የሚጠቅም መልካም አገልግሎት የማቅረብ ድንቅ ዕድል አለን! ይህም ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ የሚያመጣውን አንድ የተያያዘ ሰንሰለት በመዘርጋት ተሳታፊ መሆን ነው። ዳሩ ግን ወንጌልን ለሙስሊሞች በምናደርስበት ወቅት እራሳችንን የሰንሰለቱ የመጨረሻ አያያዦች በማድረግ ቅጥ ያጣ ጉጉት እንዳያድርብን መጠንቀቅ ይገባናል። የ1ኛ ቆሮ. 3:6 «እኔ ተከልሁ አጵሎስም አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር» የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሕ ማስታወስ ያስፈልገናል።

## በጥልቀት የሚታሰብ፡-

*** በአካባቢህ ከሚገኙት ሙስሊሞች ጋር ግንኙነት መፍጠር የምትችለው የት ነው?

*** ንግግር እንዴት ትጀምራለህ? መንፈሳዊ ጉዳዮችን እንዴት ታነሣለህ?

# ምዕ. 8 ፍቅር - የሙስሊሞችን ልብ የመማረኪያ መንገድ

ከዚህ ቀደም ባለው ምዕራፍ ድንገት ለሚያጋጥሙን ሰዎች መመስከር ስለምንችልበት ዘዴ አንዳንድ ምሳሌዎችን አቅርቤአለሁ። በመቀጠል ደግሞ ሙስሊሞችን ጠበቅ ባለ መልኩ ለመቅረብ ስለሚያስችሉን አንዳንድ መመሪያዎች ዘርዘር ባለመልኩ ለመግለጽ እሞክራለሁ። በመካከለኛው ምሥራቅ ለሰላሳ ሰባት ዓመታት ያህል የሠራ አንድ ሚሲዮናዊ፣ መውደድ፣ መንገር፣ መጸለይ በሚሉት ሦስት ቃላት በመጠቀም ሙስሊሞችን ስለሚቀርብበት ዕቅድ ተናግሯል።

ክርስቶስ እኛን እንደሚወደን አንተም ሙስሊሞችን ውደድ።

ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ንገራቸው።

ከግንኙነትህ መጀመሪያ አንስቶ እስከ መጨረሻው ጸልይላቸው።

በዚህ ምዕራፍ ሙስሊሙን ለመድረስ ስለሚያስፈልገው የክርስቲያን ፍቅር እናጠናለን። የሚቀጥሉት ሦስት ምዕራፎች ለሙስሊሞች ወንጌልን ስለ መንገርና ተቃውሞአቸውን ስለ ማስተናገድ የሚያስረዱን ይሆናሉ። እንደዚሁም በዚሁ ክፍል ውስጥ ቆየት ብለን ወንጌልን ለሙስሊሞች በምናሰራጭበት ወቅት ስለሚያስፈልገው ጸሎትና መንፈሳዊ ውጊያ እናነሣለን።

እውነተኛ ክርስቲያናዊ ፍቅር የእንቢተኝነትን በሮች ለመክፈት ግሩም ቁልፍ ነው፤ ይህ ፍቅር ነው ለሙስሊሞች ብርቱ ምስክርነት የሚሆነው። የእንግሊዝኛ፥ የእጅ ሥራና ወዘተ ትምህርት የሚሰጥበትን የዓረብ ወጣቶች መገናኛ ማዕከልን በኃላፊነት የሚመሩትን ባልና ሚስት አውቃለሁ። አንድ ቀን ተማሪዎቹን «በመስጊድም ውስጥ ቢሆን ተመሳሳይ ትምህርት እየተሰጠ ወደዚህ ለመምጣት የመረጣችሁት ለምንድን ነው?» በማለት ጠየቁአቸው። የሁሉም ተማሪዎች መልስ «እውነት በዚያም ቢሆን የሚያስተምሩት ተመሳሳይ ነው፤ ነገር ግን እዚህ ፍቅርን እናገኛለን» የሚል ነበር።

ቀደም ሲል ሙስሊሞችን ይጠላ ለነበረው ለዚያ ለማዕከሉ ዲሬክተር ይህ ሕይወቱን ለመለወጥ ያስቻለው የእግዚአብሔር ፍቅር ምስክርነት ነበር። በተወለደበት አገሩ ክርስቲያኖች በሙስሊሞች በጣም ይጨቆኑ ነበር። ወደ ምዕራቡ ዓለም በደረሰ ጊዜ አንድም ሙስሊም እንኳ ላለማየት ዕቅዶ ነበር። ቢሆንም ቅሉ እግዚአብሔር በዲሬክተሩ ልብ ውስጥ ሥራውን ሠራና ፍቅሩንና ርኅራኄውን ሰጠው። አሁን በየቀኑ ወንጌልን እየነገራቸው አብሯቸው ይውላል።

በሙስሊሞች የጭካኔ አቀባበልና ግፍ ለተከበበ ሰው «ጠላታችሁን ውደዱ» የሚለውን የጌታ ኢየሱስን ትእዛዝ ለመፈጸም በጣም ከባድ ነው። እዚህ ላይ ልንዘነጋው የማይገባው በስም ሙስሊሞች የሆኑትን ሁሉ ከእስልምና ሥርዓት ጋር ማምታታት እንደማይኖርብን ነው፤ የደኅንነትን ተስፋ በማይሰጣቸው ሃይማኖታዊ ሥርዓት ሥር በመታሰራቸው በጣም እናዝናለን። ነገር ግን ሕዝቡ ልክ እንደ እኛው ናቸው። ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ፥ ለኃጢአታቸው ይቅርታ ለማግኘትና ከሞት ፍርሃት እንዲሁም ከእግዚአብሔር ፍርድ ነፃ ለመውጣት በልባቸው እንደኛው ተመሳሳይ መቃተት አለ። አንተም ጌታ ኢየሱስን ከማመንህ በፊት የነበረህን ልምምድ በማስታወስ ምን እንደሚሰማቸው ልትገነዘብ ትችላለህ።

መሐሪው አምላካችን እንድንወድ የሚነግረን ብቻ ሳይሆን ትእዛዙን ለመፈጸም ኃይልን የሚሰጠንም ነው። ጌታ ኢየሱስን ለሚያምን ሁሉ መንፈስ ቅዱሱን ይሰጣል። በውስጥ በሚያድር የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አካሄዳችን እርሱን የሚያስደስት እንዲሆን ያደርጋል። «... በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም» (ሮሜ 5፡5)። በውስጣችን በሚሠራው መንፈስ ቅዱስ ለሁሉም ሰው የፍቅሩ መተላለፊያ እንድንሆን እግዚአብሔር ይፈልጋል።

የአንድን ሙስሊም ልብ በክርስቲያናዊ ፍቅር እንዴት ለመማረክ እንደሚቻል ከዚህ በመቀጠል የምንመለከተው የደብሊዩ ኤም ሚለርና የአንድ ወደ ክርስትና የመጣ ኢራናዊ ሙስሊም ውይይት በግሩም ሁኔታ ያሳየናል።

«ወንድሜ ወደ ክርስቶስ የመራህ ምንድን ነው?»

«የሚስተር ዊልሰን ዕንባ ነው ወደ ክርስቶስ የመራኝ» አለና ሙስሊሙ አባስ መለሰ።

«እንዴት ተደርጐ?» ስል በመገረም ጠየቅሁት። «አንድም ሰው በዕንባ ክርስቲያን ሲሆን ሰምቼ አላውቅም።»

«ነገሩ እንዲህ ነው» በማለት ይህ ወንድም እንደሚከተለው አጫወተኝ።

«ሚስተር ዊልሰን እዚህ መጥቶ ከእኔ ጋር ተነጋገረ፤ እንደዚሁም ተከራከረኝ። እኔም በክርክራችን የረታሁት መስሎ ስለተሰማኝ በጣም ተኩራራሁ። ዳሩ ግን አለማመኔንና ትዕቢቴን በመመልከት ይህ የእግዚአብሔር ሰው በጣም አዘኖ አለቀሰ። ክርክሩ ያላደረገልኝን ነገር ዕንባው አደረገልኝ። ልቤን አቀለጠው፤ እኔም አምኜ ክርስቲያን ሆንኩኝ። ቆየት ብዬ ደግሞ ተጠመቅሁኝ።»*

* ዊልያም ኤም ሚለር፥ ለእስልምና የክርስቲያን ምላሽ፥ ዊተን፥ ኢልናይስ ቲንዴል ሃውስ፥ 1976 ገጽ 126። (William H Miller, A Christian's Response to Islam, Wheaton, IL.: Tyndale House, 1976, p. 126.)

ይህ ምስክርነት የመዝሙረ ዳዊት (126፡6) ምሳሌ ነው። «በሄዱ ጊዜ፥ ዘራቸውን ተሸክመው እያለቀሱ ተሰማሩ፤ በተመለሱ ጊዜ ግን ነዶአቸውን ተሸክመው ደስ እያላቸው ይመጣሉ።»

ሙስሊሞች እንዴት በፍቅር እንደሚነኩ የምጠቅሰው ሌላው ምሳሌ ደግሞ ባለቤቱ ያጫወተችኝ ታሪክ ነው። በሕይወት መቆየት የሚችለው ብልጣ ብልጡ

ነው የሚለው አባባል፥ በእውነትም ትክክል ነው ለማለት የምንደፍረው፥ እንደ ሱማሊያ ባለው ምድረ በዳ ውስጥ ሰዎች በዘላንነት ኑሮአቸውን መምራታቸውን ስናይ ነው። ታማሚዎችና ደካሞች ብዙውን ጊዜ የተጣሉና የተናቁ ናቸው። ከእንደነዚህ ዓይነቶቹ ዩሱፍ (ትክክለኛ ስሙ አይደለም) አንዱ ነው። ይህ ሰው በአእምሮው ደካማ፥ ዕድገቱ የተገታ ወጣት ሲሆን፥ ቤተሰቡ ወደ ሚሲዮን ሆስፒታል ይዘውት መጡ። እናቱ «ውሰዱት፤ አንፈልገውም። ካልፈወሳችሁት እንቀብረዋለን» ብላ ተናገረች።

ሚሲዮናውያኑ በሽታውን መርምረው ካገኙ በኋላ ብዙ ወራት በፈጀው ሕክምና ውስጥ ፍቅርና እንክብካቤ ያልተለየው ርዳታ አደረጉለት። ቀስ በቀስ በአካሉ እየበረታና በአእምሮውም እየጐለመሰ ሄደ። ሚሲዮናውያኑና ክርስቲያን ሱማሌዎች ክርስቶስ ለእርሱ ያለውን ፍቅር በመሰከሩለት ጊዜ የወንጌልን መልእክት በጉጉት አዳመጠ። ዩሱፍ ብሩህ የሆነ ክርስቲያን ሆነና የክሊኒኩ ጸሐፊ ሆኖ መሥራት ጀመረ። ክርስቲያን እንዲሆን የገፋፋው ምን እንደሆነ ሲጠየቅ፥ ለመወደድ በመብቃቱ መሆኑን በመግለጽ፥ «ተወዳጁ መዝሙሬ ኢየሱስ ይወደኛል፤ ይህንን አውቃለሁ፤ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልኛል» ሲል በደስታ መለሰ።

ከፍቅር በተጨማሪም ከመንፈስ ፍሬዎች አንዱ የሆነውና በገላ. 5:22 የተጠቀሰው ትዕግሥት ነው። ለሙስሊሞች ወንጌልን ለማድረስ ይህ በጣም አስፈላጊ ባሕርይ ነው። እስቲ አንተም ብትሆን አንድ ሙስሊም ለመጀመሪያ ጊዜ የክርስቶስን ወንጌል በሚሰማበት ወቅት በአእምሮው ውስጥ የሚመላለሰውን ነገር ለመገመት ሞክር። ሕይወቱን በሙሉ የተማረው እግዚአብሔር በፈለገው መንገድ እንደሚሠራ፥ ልዩና ሊታወቅ የማይችል መሆኑንም ጭምር ነው። በዳኝነቱ ደግሞ ፍርደ ገምድል እንደሆነ፥ የወደደውን ይቅር የሚል እና የወደደውን የሚኮንን ነው። በሙስሊሞች ማኅበረሰብ አንድ ሰው በሚኖርበት አካባቢ ያለው ቤተሰቡ፥ ቤተዘመዱ፥ ሁሉም ሰው፥ የሚያምኑትና የሚለማመዱት ተመሣሣይ ነገርን ነው። እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ያለው ያ ሙስሊም ወንጌልን ሰማ እንበል፤ ፈጣሪ የሰውን ሥጋ ለብሶ ስለ መምጣቱ፥ በሰዎች መካከል ስለ መኖሩ፥ ለፍጥረቱ ኃጢአት በመስቀል ላይ አሰቃቂ ሞት መሞቱንና ከሞት ስለ መነሣቱም ሰማ እንበል። እንዲህ ዓይነቱ ዜና ለእርሱ የሚታመን አይደለም። መጀመሪያ ወንጌልን በሚሰማበት ጊዜ ስድብና አስቀያሚ ነገር ሆኖ ይሰማዋል። ስለዚህ አደራህን፥ በሙስሊሙ ምላሽ የማትቆጣና ለምስክርነትህ በሚያሳየው አልረታ ባይነት ታጋሽ ሁን።

ሙስሊም ሴቶች የክርስቶስ ፍቅር እንዲገለጥላቸው ልዩ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ቡድኖች ናቸው። በእስልምና የተሰጣቸው ምድብ ስፍራ

ለወንዶች የማገልገልና በማንኛውም ሁኔታ ዝቅ ማለት ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በእርግጥ እንደሚወዳቸውና እንደሚያከብራቸው ለመቀበል በጣም ይከብዳቸዋል። በመሆኑም በተለይ ለሙስሊም ሴቶችም ስለሚሰጠው አገልግሎት በምዕራፍ 15 በስፋት ይቀርባል።

## በጥልቀት የሚታሰብ

*** ክርስቲያኖች ሙስሊሞችን በእርግጥ መወደድ የሚቻላቸው ይመስልሃልን? ከሆነስ እንዴት? (ከመጽሐፍ ቅዱስ አጣቅስ።)

*** እግዚአብሔር ፍቅሩን በልብህ እንዲያስቀምጥ አሁን ጸልይ።

# ምዕ. ፱ የክብሩን ወንጌል ለሙስሊሞች ንገራቸው

በዚህ ወንጌልን ለሙስሊሞች ከመመስከር የተነሣ ነው ክርስቲያኖች በበለጠ ብልሃት የሚያዳብሩትና እውቀትን የሚገበዩት። እምነትን በማካፈል ወንጌል ምን እንደሆነ፥ ጌታ ኢየሱስ ማን እንደሆነ፥ ለደኅንነት ምን እንዳደረገ፥ እና ምላሻችን ምን መሆን እንዳለበት፥ በግልጽና በቀላል መንገድ ማስረዳት ትችል ዘንድ የንግግር ዘዴን ተለማመድ። ደኅንነት ለአንተ ምን ትርጉም እንዳለው በመግለጽ የግል ምስክርነትህን የማብራራት ችሎታህን አዳብር።

እስልምና ለሰዎች ውስጣዊ የልብ ፍላጎት፥ ለምሳሌ ከእግዚአብሔር ጋር ስለ መታረቅ፥ ስለ ኃጢአት ይቅርታ፥ ከእግዚአብሔር ቁጣ ነፃ ስለ መሆን፥ ስለ ዘላለም ሕይወት ዋስትና፥ እግዚአብሔርን በግል ስለ ማወቅ፥ በፍቅሩ ስለ መደሰትና እርሱን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት ስለ መኖር መልስ እንደሌለው ተገንዘብ። በክርስቶስ ያለንን በረከት ሁሉ አስተውልና ሙስሊሞች ስለ እነዚህ ምንም እንደማያውቁ ተረዳ።

ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ በቂ የሆነ መረዳት የላቸውም ማለት ከእግዚአብሔር ጋር ስላላቸው ግንኙነት ከቶ እርግጠኞች ሊሆኑ አይችሉም ማለት ነው። ከሰዎች ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ተለዋዋጭ የሆነና በዘፈቀደነት የተሞላ ከአእምሮ በላይ የሆነ ኃይል አድርገው ይቆጥሩታል። መንግሥተ ሰማይ ይገቡ እንደሆነ ሲጠየቁ «ኢንሻ አላህ» (እግዚአብሔር ቢፈቅድ) በማለት ይመልሳሉ። እግዚአብሔር የሰዎችን በጎና ክፉ ሥራ በሚዛን ይመዝናል ብለው ያምናሉ። እናም ዕድሉ የሚወሰነው ሚዛኑ ወደደፋበት ነው ይላሉ። በላያቸው ሊመጣ ስላለው የእግዚአብሔር ፍርድ ጥልቅ ፍርሃት አላቸው። ስለዚህ በተደጋጋሚ የሚሰማው የሙስሊሞች አቤቱታ «የእግዚአብሔርን ምሕረት እሻለሁ» የሚል ነው።

ስለ እነዚህ ጥልቅ ውስጣዊ ፍላጐቶች በተናገርክ መጠን ከሙስሊሞቹም በኩል የምታገኘው ምላሽ ሞቅ ያለ ይሆናል። በዚህ አጋጣሚ ሰው ደኅንነትን የሚያገኘው በግል መሻቱ የተነሣ ሳይሆን እግዚአብሔር ሊያድነው የሚፈልግ ስለ መሆኑ አጠንክረህ ንገር። ይህን የሚያደርገው የጠፋውን ኃጢአተኛ ለማዳን እንጂ ሊፈርድበት አይደለም። እግዚአብሔር የጠፉትን የሚፈልጋቸው ስለሚወዳቸው ነው። ወንጌልን በግል ደረጃ ለማካፈል በምትነሣበት ወቅት ምንጊዜም ቢሆን የእስልምናን ፍጹም አጠቃላይ ብቃተ ቢስነት አስታውስ።

ሙስሊሞች ስለ ሃይማኖታቸው በደስታ ስለሚናገሩ ግልጽ ፍላጐት በማሳየትና በጸጥታ በማዳመጥ ማበረታታት ይገባሃል። ስለ መንፈሳዊው ዓለም በጣም የነቁ ስለሆነ፥ እንደዚህ ስላለው ጉዳይ ለመወያየት ዝግጁ ናቸው። መንፈሳዊ የውስጥ ፍላጐቶቻቸውን ለማውጣጣት ዘዴኛ በመሆን የፈለግኸውን ጥያቄ ልታቀርብላቸው ትችላለህ።

ለምሳሌ፥

«ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን መሥርተህ ታውቃለህ ወይ?»

«ለኃጢአትህ ይቅርታ አግኝተሃል?»

«እግዚአብሔር ጸሎትህን ይመልሳል?»

«ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደምትገባ እርግጠኛ ነህ?»

«ሕይወትህ እግዚአብሔርን ያስደስት እንደሆነ ታውቃለህ?»

«በሕይወትህ ሰይጣንንና ክፋውን እንዴት እንደምታሸንፍ ታውቃለህ?»

«የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ለመከተል ብርታት አለህ?»

ይህን የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ልታነሳባቸው ብትችልም፥ ዳሩ ግን በእያንዳንዱ ውይይት ወቅት እነዚህን ሁሉ ጥያቄዎች በአንድ ጊዜ እንደ ጥይት እንድታዘንብባቸው መምከሬ አይደለም። ጨርሶም ልታደርገው አይገባም! በውይይታችሁ ላይ በእንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች መቼ መጠቀም እንደሚገባህ መንፈስ ቅዱስ እንዲመራህ እስከ መጨረሻ ጸልይ። ስለምታነጋግረው ሰው የልብ ሁኔታ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። በተጨማሪም ለእነዚህ ጥያቄዎች ብዙዎቹ ሙስሊሞች የሚሰጡት መልስ አሉታዊ እንደሚሆን ከወዲሁ ማወቅ አለብህ። ምክንያቱም እንደእነርሱ እምነት እግዚአብሔር በሰው ልጅ ላይ ያለው

አቋም የማይታወቅ ወይም ተለዋዋጭ በመሆኑ፥ ስለነዚህ ነገሮች ማንም እርግጠኛ መሆን አይችልም የሚል አቋም ስላላቸው ነው።

የዚህ ዓይነቱ ትህትና ያለበት አጠያየቅ ዓላማ፥ እስልምና በልቡ ውስጥ ለሚብላሉት ፍላጎቶቹ ወይም ጥያቄዎቹ ምንም ምላሽ እንደማያስገኝለት ገና ከመጀመሪያው ወደ መገንዘቡ እንዲያዘነብል ስለሚያደርገው ነው። ከዚህ ቀጥለህ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል እንዴት የውስጥ ፍላጎቶቹን ሁሉ ለማሟላት ዝግጅት እንዳደረገ ግለጽለት።

ይህንን የጥያቄ ዘዴ በመጠቀም ያነጋገርኩትን መልካም ሙስሊም የሆነ ዓረብ ወጣት አስታውሳለሁ። ይህ ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱስን ለራሱ እንዲመረምር አነሣሥቶታል። እኔም እየተከታተልሁትና መንፍስ ቅዱስም መጽሐፍ ቅዱስ እውነቱን እንዲገልጽለት እጸልይለት ነበር። የሚያሳዝነው ግን ይህ ወጣት ከጌታ ኢየሱስና ከእስልምና መካከል ክርስቶስን መምረጥ አቅቶት ወደ ቀድሞው መንገድ ተመለሰ።

በተቻለም መጠን አንድ ለአንድ ሰው በሆነ አቀራረብ ለሙስሊሙ ወንጌልን ለማካፈል ሞክር። ጠቅለል ባለ አነጋገር ሙስሊሞች በሌሎች ሙስሊሞች ፊት ለክርስትና ቀናነትን አያሳዩም። እርስ በርስ ስለሚፈራሩ ሌሎች ካሉ እስልምናን የመከላከል ግዴታ እንዳለባቸው ይሰማቸዋል። በአንድ ሙስሊም አገር ስለሚኖሩና በየግላቸው በጌታ ኢየሱስ ያምኑ ስለነበሩ ሁለት ወንድማማቾች የማውቀው ታሪክ አለ። አንዱ ለሌላው ክርስቲያን እንደሆነ ለመንገር ይፈራ ነበር። ዳሩ ግን ሁለቱ በድንገት በ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ ቢገናኙ የሚታይባቸውን የድንጋጤ ስሜት አስበው! ከበፊቱ ይልቅ አሁን በክርስቶስ ወንድማማች መሆናቸውን መገንዘቡ የቱን ያህል ባስደሰታቸው ነበር።

ከወንጌል ክፍል በምትጠቅስበት ጊዜ ለምሳሌ የዮሐንስ ወንጌል ከማለት ዮሐንስ የጻፈው ወንጌል በሚል አጠቃቀም ተጠቀም። ይህም የመጀመሪያው አገላለጽ ለሙስሊሞች አራት የተለያዩ ዓይነት ወንጌሎች እንዳሉ ስለሚያስመስል ነው። ወንጌል ስለ ክርስቶስ ሕይወት፥ ሞትና ትንሣኤ ነው። ይህም በአራቱ የዓይን ምስክሮች በሆኑት በማቴዎስ፥ በማርቆስ፥ በሉቃስና በዮሐንስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ ይገኛል።

ለሙስሊሞች ለመጀመሪያ ጊዜ ስትናገር «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለውን አባባል ላለመጠቀም ጥንቃቄ አድርግ። ስለ እውነተኛ ትርጉሙ የሚኖራቸው ግንዛቤ የተምታታ ስለሚሆን ብዙውን ጊዜ የውይይቱን ዘላቂነት ይገታዋል።

በጥልቀት የሚታሰብ፡-

*** ከሙስሊም ጋር ያለ ምንም ክርክር ስለ ሃይማኖት መወያየት የምትችለው እንዴት ነው?

*** የሙስሊሞችን የመከላከያ ቅጥሮች ለማለፍ ስለሚያስችሉህ ዘዴዎች ምን ታስባለህ?

## ምዕ. 10 ሙስሊም በወንጌል ላይ ያለውን ጥላቻ መረዳት

የሙስሊሞችን ጥላቻና በክርስትና ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በተመለከተ ማጤን የሚገቡን አንዳንድ አጠቃላይ መርሖዎች አሉ።

1. በክርስትና ስም በሚፈጸሙ አንዳንድ ድርጊቶች ላይ ሙስሊሞች የሚሰነዝሯቸውን ትክክለኛ ቅሬታዎች መነሻ መረዳት አለብን።

2. እንደ አንድ ሕዝብ በሙስሊሞች ላይ የሚኖረን አመለካከት እንደ ሥርዓትነቱ በእስልምና ላይ ከሚኖረን አመለካከት የተለየ መሆን ይገባዋል።

3. አንዳንድ ጊዜ ለተቃውሞአቸው ምላሽ መስጠት የማያስፈልግበት ወቅት መኖሩን ማጤን ይኖርብናል።

4. መጽሐፍ ቅዱስ እስልምናን አይቃወምም፤ በተገላቢጦሹ ግን እስልምና መጽሐፍ ቅዱስን ይቃወማል።

1. ብዙ ሙስሊሞች በመካከለኛው ዘመን በተካሄዱት ክርስቲያናዊ ዘመቻዎች (የመስቀል ዘመቻዎች) አማካኝነት የተፈጸሙትን ጥፋቶችና ጭካኔ የተሞላባቸውን ድርጊቶች በማስታወስ፥ አሁንም ቢሆን የጠላትነት ስሜት ይሰማቸዋል። እንደዚሁም በአለፈው 200 ዓመታት የሙስሊም አገሮች በምዕራቡ ዓለም ኢምፔሪያሊዝም አማካኝነት የደረሰባቸው የውርደት ቂም ከኀሊናቸው አለመፋቁ ሌላው ምክንያት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የ«ክርስቲያን» አገሮች ለእስራኤል መንግሥት የሚሰጡት ድጋፍ በሙስሊም መንግሥታት ላይ የተቃጣ ተደርጐ በመቆጠሩ፥ ለክርስቲያኖች ምስክርነት ዕንቅፋት ሆኗል። «የክርስቲያን» መንግሥት ብሎ ነገር እንደሌለ ለሙስሊሞች ገልጸን ማስረዳት አለብን። ክርስትና ከክርስቶስና ከተከታዮቹ ጋር ኅብረት የመፍጠር ጉዳይ ነውና ከዓለማዊ ተቋማት ጨርሶ ይለያል። በሌላ በኩል ግን በርግጥም እስላማዊ የሆኑ መንግሥታት አሉ።

የእነዚህ መንግሥታት እስላማዊ መስተዳድሮች የሕዝቦቻቸውን ፖለቲካዊ፥ ኤኮኖሚያዊና ሃይማኖታዊ ሕይወት ይቆጣጠራሉ።

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች በሙስሊሞች ላይ ስለሚያሳድሩት የጥላቻ ስሜት በጥልቀት ልንረዳ ይገባል። በተለይ የማያቋርጠውን የመካከለኛ ምሥራቅ ውጥረት አስመልክቶ ስለሚኖራቸው ስሜት ልንጠነቀቅ ይገባል። በርኅራኄ መንፈስና በለዘበ አንደበት እነዚህ ድርጊቶች የኃጢአተኛ ግለሰቦች ሥራዎች መሆናቸውንና እንደማንደግፋቸውም ልናስረዳቸው መሞከር አለብን። እነዚህ የክርስቲያን እርምጃዎች አልነበሩም። አዲስ ኪዳን (ኢንጂል) ግፍን፥ የድሃን መጨቆን፥ የክፋት ገጽታ ያላቸውን በሙሉ የሚቃወም ሲሆን፥ «ቅዱስ ጦርነት» (ጂሃድ)ንም አይደግፍም። በሙስሊሙ ዓለም ግን «ቅዱስ ጦርነት»፥ ማለትም ጠላትን በማንኛውም መንገድ ድል ማድረግ የተከበረና ትክክልም ነውና፥ እንደእነዚህ ስላሉ ጉዳዮች ጣልቃ ላለመግባት ሞክር። ምንም ፍሬ የሌለው ከመሆኑም በላይ ስለ ክርስቶስ ከምትሰጠው ምስክርነት መስመር ለቅቀህ እንድትሄድ ብቻ ነው የሚያደርገው። ክርስቲያኖችን «... ጠላታችሁን ውደዱ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ የሚረግሙአችሁን መርቁ፥ ስለሚበድሉአችሁ ጸልዩ» (ሉቃስ 6፡27) ብሎ በማዘዝ አዲስ ኪዳን ተቃራኒውን እንደሚያስተምር አሳያቸው። ይህ ትምህርት፥ ሙስሊሙ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ጽኑ ፍቅርንና ትዕግሥትን በሚያይበት ወቅት ይረጋገጣል። በተረፈ ግን በአስተምህሮትና በድርጊትህ መካከል ምንም ዓይነት አለመጣጣም ቢኖር ወዲያውኑ ይደርሱበታል።

2. ሙስሊሞችን እንደ አንድ ሕዝብ በምንወስድበት ጊዜ ለእነርሱ የሚኖረን ዝንባሌ መመሥረት ያለበት ዓላማቸውን ለማሳከት ተቃዋሚዎቻቸውን ሁሉ በሚገድሉና በሚደመስሱ ቀንደኛ አክራሪዎች አምሳል መሆን የለበትም። ከዚህ በተቃራኒ ብዙ ሙስሊሞች ቤተሰባዊነት የሚሰማቸውና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ናቸው። በወዳጅነት መንፈስ ወንጌልን ይዞ ለሚቀርብላቸው የጥላቻና የግጭት ምላሽ የሚሰጡ ሁሉም ሙስሊሞች አይደሉም። በመካከላቸው እውነተኛ መሻት ያለው ልብ ያላቸውና ያለማዳመጥ ዝግጁ የሆኑ አሉ።

ስለ እስልምና አክራሪዎች መስፋፋትና መጠናከር በየጊዜው በጋዜጦች እናነባለን። ለዚህም የሙስሊሞች ወንድማማችነት ግንባር አንዱና ዓይነተኛው ምሳሌ ነው። እንቅስቃሴው ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ እንደ መሆኑ፥ ሁሉንም መንግሥታት ከእስላማዊ ሕግ ሥር ለማድረግ የሚጥር ነው። የእስልምና ሃይማኖት በሥርዓትነቱ በግልጽና በኃይል ፀረ ክርስቲያናዊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልገናል። በዛሬው ጊዜ የእስልምና እንደገና ማንሠራራት በመላው ዓለም እየታየ ነው።

የእስላማዊ መንግሥታት «ፔትሮዶላር» (ነዳጅ በመሸጥ የሚገኝ ገንዘብ) ሃይማኖቱን ለማስፋፋት በሥራ ላይ ይውላል። ለኋላ ቀር አገሮች መንግሥታት በርዳታ ስም ከፍተኛ ገንዘብ ይሰጣሉ። ይህም እስላማዊ ማዕከሎችንና መስጊዶችን ለመሥራት መርጃ እንዲሆን ነው።

ከዚህ እንደምንረዳው የእስልምና ሃይማኖት በግልጽ በክርስትና እምነት ላይ ታላቅ ተቃውሞ እንዳለው ነው።

በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለ እምነትና እስልምና እርስ በርስ የሚቃረኑ ስለሆኑ፥ በመጨረሻ ላይ ፍጥጫ የማይቀር ነገር ነው። በምስክርነት ወቅት ለአንገብጋቢ መንፈሳዊ ችግሮች ቅድሚያ ትኩረት መስጠት እንጂ፥ ቁርዓን ወይስ መጽሐፍ ቅዱስ፥ መሐመድ ወይስ ኢየሱስ ክርስቶስ በማለት የሚፈጠሩ ክርክሮች በአጠቃላይ መወገድ ይኖርባቸዋል። ውይይቱን ከውዝግብ የራቀ አድርጎ መምራትና ሁልጊዜ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሆነው አዎንታዊ የእግዚአብሔር ምሕረት ላይ ማትኮር አስፈላጊ ነው። የመጨረሻ ፍጥጫ የሚሆነው እስልምና በሚያስተምረውና ኢየሱስ ክርስቶስ በቃሉ ውስጥ በሚናገረው መካከል ይሆናል። ሆኖም ለዚህ ወሳኝ ወቅት መፋጠን የአንተ አስተዋፅኦ አያሻውም። ይህ ሳይዘገይ በሰዓቱ የሚመጣ ከመሆኑም፥ ሁሉም ነገር በመንፈስ ቅዱስ በሚሆን ውስጣዊ ወቀሣ አማካኝነት እንደሚፈጸም መረዳት ያሻል።

3. ሙስሊሞች በክርስትና ላይ ለሚሰነዝሩት ተቃውሞ አንዳንድ ጊዜ መልስ መስጠት አስፈላጊ አይደለም። ወንጌልን እያካፈሉ እያሉ የአድማጭን የልብ ዝንባሌ መገምገም አስፈላጊ ነው። ተቃውሞም በትክክለኛ ጥያቄ ላይ የተመረኮዘ እስከሆነ፥ በተቻለ መጠን በተገቢው ሁኔታ መልስ ማግኘት ይኖርበታል። ርዕሰ ጉዳዩ ከችሎታህ በላይ ከሆነ ሁኔታውን ተቀብለህ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት እንደሚያስፈልግህ ለጓደኛህ ግልጽ አድርግለት። ይህ ሳይሆን ግን የሙስሊሙን ተቃውሞዎች በተድበሰበሰ መልስ ለማለፍ መሞከር እጅግ ብልግናና ራስን አጓጉል ማሞካሸት ነው።

ይሁንና ተጻራሪ ሙስሊም ቢገጥምህ የተጠናከረ አቋም ልትይዝ ይገባል። ለአንዱ ቅዋሚ መልስ ስትሰጥ ሌላ ይመጣብሃል ... አሁንም አሁንም በዚያው መልኩ እየተደጋገመ ይቀጥላል። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ከተፈጠረ ግን መቀጠሉ ፍሬቢስ ነው። ተቃዋሚው ምንም መልስ አይፈልግም፤ እናም ይህ የሚያመለክተው «አንዴ በአቋሜ ጸንቻለሁና፥ የቱንም ያህል በሐቅ ብታስረዳኝ አልቀበልህም» የማለት ያህል ነው። እኔን እንዲህ ዓይነቱ ሰው ቢያጋጥመኝ የምመልስለት፥ «ጥያቄዎችህ በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መልስ አላቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ ቢኖርህ አንብበህ ልትረዳ ትፈልጋለህን?» በማለት ብቻ ይሆናል። ከዚህ በኋላ ነገሩን ባለበት እተወዋለሁ። በወንጌል ላይ ሙስሊሞች ስለሚሰነዝሩአቸው ቅዋሚዎች መልስ ለመስጠት የሚረዱ አሳቦች በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ ይገኛሉ።

4. መጽሐፍ ቅዱስ እስልምናን ስለማይጻረር፥ እኛም መጻረር የለብንም። ይልቅ እስልምና ነው መጽሐፍ ቅዱስን የሚጻረረው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን በምንናገርበት ወቅት የተከላካይነት አቋም መያዝ አያስፈልገንም። እግዚአብሔር ራሱንና ዓላማውን ለመግለጽ ይስማማል ያለውን ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲዘገብ ፈቅዷል። መጽሐፍ ቅዱስ የተጠናቀረው እስልምና እንደ ሃይማኖት ከመመሥረቱ ስድስት መቶ ዓመታት በፊት ነው።

ጌታ ኢየሱስ ስለ ራሱ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፥ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» (ዮሐ. 14፡6) በማለት ተናግሯል። ስለ እግዚአብሔር ቃልም «... ቃልህ እውነት ነው» (ዮሐ. 17፡17) ብሏል። ለደቀ መዛሙርቱ «እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የወጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ» (ማቴ. 5፡17፥ 18) ብሎ ነግሯቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉና ፍጹም በሆነ ሥልጣን ይናገራል። የእግዚአብሔር ቃል የመጨረሻው እውነተኛ ዳኛ መሆኑን የሚደግፍ አቋም በመያዛችን በአቋማችን ልናፍር አይገባም።

ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን በሚቃወሙበት ጊዜ ለቅዋሚአቸው አዲስ ማረጋገጫ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው። እዚህ ላይ ነው የሙስሊሞች ክርክር ደካማ ጐን የሚታየው። የእስልምናን ታላቅነት በኃይል በሚያረጋግጡበት ወቅት ልበ ሙሉ ናቸው። ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛ አለመሆን የሚያሳይ ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ ባለመታከት በመጠየቅ ወደ ተከላካይነት ደረጃ ብታወርዳቸው ግራ የተጋቡና በራሳቸው የማይተማመኑ ደካሞች ሆነው ታገኛቸዋለህ። «ይህን ለምን ታምናለህ?»፥ «ለአባባልህ ምን ማረጋገጫ አለህ?» የመሳሰሉ ጥያቄዎችን ጠይቅ። በተግባር ላይ ከመዋላቸውም ጠቀሜታቸው ስለተረጋገጠ ተመሳሳይ የጥያቄ ዓይነቶች ቆየት ብሎ በሚቀጥለው ምዕራፍ ይቀርባሉ።

በግልጽ ፀረ ክርስቲያን የሆኑ ወይም መጽሐፍ ቅዱስን የሚቃወሙ ሥነ-ጽሑፎችን ከሙስሊሞች መቀበል እንደማያሻ በጥብቅ እመክራለሁ። ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል የአሕመድ ዲዳትን ስቅለት ወይስ ልብወለድ-ስቅለት

(Crucifixion or CRUCI-FICTION,) እና ሌሎች በእርሱ የተጻፉትን ጽሑፎች ልትቀበላቸው አይገባም። ከቅዱስ ቃሉ እንደምናውቀው እንዲህ ዓይነት ሰዎች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ለመጻፍ ምንም ሥልጣን የላቸውም። እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ቃሉን እንደማይረዱ፥ ሊረዱትም እንደማይችሉ በተለየ መልክ ገልጿል። «ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቀው አይችልም» (1ኛ ቆሮ. 2፡14)። በዚህ ምክንያት ዲዳትን ከመሳሰሉ ሙስሊሞች ጋር ግልጽ ክርክር እንዳይከፍቱ ክርስቲያኖችን በጥብቅ እመክራለሁ። ለሙስሊሞች ውሸትን የሚያሳምን የፕሮፖጋንዳ መድረክ ከመሆን በቀር የክርስቶስን እውነት በጥሞና እንዲገነዘቡ የሚያበረክተው እገዛ ትንሽ ነው።

ይህንን ጽሑፍ ለሙስሊሞች በማንበብ ወይም ከእነርሱ ጋር በመወያየት ተአማኒነት አታላብሰው። እርግጥ ነው ሙስሊሞች ክርስቲያናዊ ሥነ-ጽሑፎችን እንዲያነቡ እንጠይቃቸዋለን፤ ነገር ግን ክርስቶስን ከፍ የማድረግ ዓላማ ያላቸውን እንጂ እስልምናን ወይም መሐመድን ጥላሸት የሚቀቡትን አይደለም። ለሙስሊም ጓደኛህ «በበኩሌ እስልምናን ወይም ቁርዓንን በመጥፎ ሁኔታ የሚቃወም ማናቸውንም ነገር እንድታነብ አልጠይቅህም። ስለዚህ አንተም ክርስትናን የሚቃወሙ ነገሮችን እንዳነብ አትጠይቀኝ» ብለህ መናገር ትችላለህ።

### በጥልቀት የሚታሰብ

*** በክርስትና ላይ ጥላቻ ለማሳደር ሙስሊሞች ምን ምን ትክክለኛ ምክንያቶች ያሏቸው ይመስልሃል?

*** እንደ ሃይማኖትነቱ በእስልምና ላይ የሚኖርህ ዝንባሌ ምን ሊሆን ይገባል?

*** በሙስሊም ሕዝቦችስ ላይ የሚኖርህ ዝንባሌ ምን ቢሆን መልካም ነው?

## ምዕ. 11 ለዋነኞቹ የሙስሊሞች ተቃውሞዎች ምላሽ መስጠት

ሙስሊሞች እስላማዊ ትምህርትን በኃይል በማስፋፋት ላይ ሲሆኑ፥ ትክክለኛው ሃይማኖት እርሱ ብቻ እንደሆነ ያምናሉ። ይሁንና ብዙ ጊዜ በወንጌል ላይ የሚሰነዘሩት ተቃርኖ ክርስትናን መቃወም እንጂ የእስልምናን ብርታት ማጉላት አይደለም። ሙስሊሞች ቅደም ተከተላቸው ተጠብቆ በቃል በሚንበለበሉ ወጥ ተቃውሞዎቻቸው አድማጫቸውን ለማሳመን ይሞክራሉ። እስኪ ሙስሊሞች በክርስትና ላይ የሚሰነዝሯቸውን ዋነኛ ተቃውሞዎችና የምላሽ አሳቦችን ላካፍልህ።

## የሙስሊሞች ዋነኛ ተቃውሞዎች

1. «ክርስቲያኖች አንድ አምላክ ሳይሆን ሦስት አማልክትን ማለትም እግዚአብሔር፥ ማርያምንና ኢየሱስን ስለሚያመልኩ የአምላክን ስም ያስነውራሉ።» ከመፈጠሩ ጀምሮ እስልምና ካሉት ዓላማዎች አንዱ በዘመኑ በነበሩ ጐሣዎች ዘንድ የገነነውን አምልኮተ ጣዖት አስወግዶ አንድ አምላክ በማምለክ ላይ ያተኮረ ሃይማኖት መመሥረት ነበር። በዚህ ምክንያት ነው ጣዖት በመሰላቸው ላይ ሁሉ ተቃውሞ የሚሰነዝሩት።

2. «እግዚአብሔር ልጅ ሊወልድ አይችልም።» ለእነርሱ ይህ ማለት እግዚአብሔር ከማርያም ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አድርጎ ነበር ማለትን ያመለክታል።

3. «ኢየሱስ ሌላው ነቢይ እንጂ አምላክ አልነበረም።» እግዚአብሔር ከሁሉም ፍጥረት የላቀ ስለሆነ ሰው እስከ መሆን ራሱን ፈጽሞ ዝቅ አያደርግም የሚል እምነት አላቸው።

4. «ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም።» ሙስሊሞች የሚያምኑት አንድ ኢየሱስን የሚመስል ሰው በመስቀል ላይ እንደ ተተካ ነው። እግዚአብሔር የእርሱን ነቢይ እንዲህ ባለ ውርደት እንዲገደል አይፈቅድም ይላሉ። ይህ የክርስቶስን መሞት መካድ የሰው ልጅ አዳኝ የለውም ማለት ነው።

5. «መጽሐፍ ቅዱስ ከመጀመሪያው ጽሑፍ የተለወጠ ስለሆነ እውነተኛ አይደለም።» ቁርዓን ለመሐመድ በዓረብኛ ቋንቋ ስለ ተገለጠ የመጀመሪያውን ቅርፅ ይዞ ይገኛል ብለው ያምናሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች ቋንቋዎች ስለ ተተረጐመ ተአማኒነት የለውም ይላሉ።

## ለእነዚህ ተቃውሞዎች መልስ መስጠት

ቅራኔ የሚሰነዘርባቸው ጉዳዮች መሠረታዊ የክርስትና አስተምህሮት የሆኑት የሥላሴ ሦስትነት፥ የክርስቶስ መለኮትነት፥ የእርሱም ለኃጢአት ስርየት መሞቱና ከሙታን መነሣቱ እናም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ትክክል መሆኑን ናቸው። በእነዚህ ላይ የሚሰነዘረውን ጥቃት መከላከል በጣም አስፈላጊ ሲሆን፥ ዳሩ ግን መገንዘብ ያለብን እውነቶቹን ልናስተውል የምንችለው መንፈስ ቅዱስ መረዳትን ሲሰጠን ብቻ መሆኑን ነው። በመሆኑም ሙስሊሞች እነዚህን ጉዳዮች

በአእምሮአቸው ደረጃ ብቻ የመቀበል ብቃት ይኖራቸዋል ብለን ተስፋ ማድረግ የለብንም። «ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቀው አይችልም» (1ኛ ቆሮ. 2፡14)።

ይሁንና እንደእነዚህ ዓይነቶቹ ተቃውሞዎች እንዲሁ ሊታለፉ የማይችሉና ምላሻቸው በብልሃት መዘጋጀትን የሚጠይቅ ነው። በምላሾቹ ላይ የሚደረገው ክርክር የሙስሊም የወንጌል መልእክት ከመረዳት ችሎታ በላይ እጅግ የረቀቀና የተወሳሰበ መሆን የለበትም። መልስ የመስጠቱ ዓላማ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመመስከር ሲባል የተደረገ ሆኖ መወሰድ አለበት።

ማንኛውም የምታቀርበው መልስ ሙስሊሙን ስለ እውነት እንዲያምን ያደርጋል ማለት ብዙም የማይመስል ነው፤ ነገር ግን መንፈሳዊ ብርሃን ወደ ልቡና አእምሮው እንዲገባ የሂደቱ አንዱ ክፍል በመሆን ያገለግላል። ከላይ ለተዘረዘሩት ተቃውሞዎች ከዚህ በታች የሚቀርቡ ምላሾች እንደ መመሪያ የተሰጡ ናቸው። የበለጠ አጥጋቢ የሆኑ ሌሎች መንገዶችን ለራስህ ማግኘት ትችላለህ።

1. «ክርስቲያኖች አንድ ሳይሆን ሦስት አማልክትን ማለትም እግዚአብሔርን፥ ማርያምንና ኢየሱስን ስለሚያመልኩ የአምላክን ስም ያስነውራሉ።»

አንድ ሙስሊም ሦስት አማልክት ታመልካለህ ብሎ በሚከሰኝ ወቅት እንዲህ ላለው የጥቃት ውንጀላ መልስ የምሰጠው በኃይለኛና በቁርጠኛ ስሜት ነው። በተለይ ደግሞ ሦስቱ አማልክት እግዚአብሔር፥ ማርያምና ኢየሱስ ናቸው የሚለው ሐተታ ሲታከልበት! እንዲህም እለዋለሁ:- «የሆነ ሰው በተሳሳተ መንገድ ነግሮሃል። ያለ ምንም ጥርጥር ክርስቲያኖች ሦስት አማልክትን አያመልኩም። ማርያምን ማምለክና ለእርሷም መጸለይ ጨርሶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። እባክህን እንዲህ ያለውን ስድብ በፊቴ አትናገር። ጣዖት ማመልክ ለሕያው እግዚአብሔርና ለእኔም በደል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፥ «... አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ» (ዘዳ. 6፡4፥ 5)።

የሥላሴ ፅንሰ አሳብ በሙስሊሞች ዘወትር የሚነሣ ተቃውሞ ሲሆን፥ አጥጋቢ ማብራሪያ ማቅረብ ከቶውንም አይቻልም። ይሁንና አንዳንድ መልሶች ሊሰጡበት ያስፈልጋል። ችግሩ የእግዚአብሔርን ማንነት ለመግለጽ እየሞከርን መሆናችን ነው። ይህ ደግሞ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ከሰብዓዊ ልምምድ ለመግለጽ የሚያስችል አቻ ነገር ስለሌለ ፈጽሞ የማይቻል ነው። ክርስቲያኖች እንኳ ይህን

ፅንሰ አሳብ ለመረዳት ይታገላሉ። ምክንያቱም ውስን የሆነው ሰው ፍጹምና አጽናፍ አልባ የሆነውን መረዳት ስለማይቻለው ነው።

ሐቁ የእግዚአብሔር ባሕርይ እጅግ ድንቅ ከመሆኑ የተነሣ የትኛውም ሰብአዊ ምናብ ሊደርስበት የማይችል መሆኑ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ማለት እርሱ ሊታወቅ አይችልም ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስ «እኔን ያየ አብን አይቶአል (ዮሐ. 14:9) ብሏልና። ለሚያምኑት ጌታ ኢየሱስ እግዚአብሔርን ይገልጥላቸዋል። «ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው» (ዮሐ. 17:6)። የእግዚአብሔርን ማንነት ልናውቅ የምንችለው ጌታ ኢየሱስን በሕይወታችን ስንቀበለው ወይም ስናውቀው ነው። በመንፈስ ቅዱስ ራሱን ይገልጥልናል። ጌታ ኢየሱስ እንኳ የእግዚአብሔርን ሥላሳዊ ባሕርይ ለደቀ መዛሙርቱ ለመግለጽ ከቶ ጥረት አላደረገም። በጣም ጠቃሚ እውነቶችን በሚያስተምራቸው ወቅት እንዲሁ በውስጠ ታዋቂነት ነው የገለጸው (ዮሐ. 14)። የሥላሴ አስተምህሮት ከብሉይ ኪዳንና ከአዲስ ኪዳን ትምህርቶች የተገኘ ነው።

አንዳንድ ሰዎች ውኃ የሚገኝባቸውን ሦስት ደረጃዎች፥ በረዶ፥ ውኃ እና ተን (እንፋሎት) በመጠቀም በተነጻጻሪ ሊገልጹት ይፈልጋሉ። ወይም ደግሞ ፀሐይ ራሷን የምትገልጥባቸውን ሦስት መንገዶች፥ ብርሃን፥ ሙቀትና ኃይልን በመጠቀም ሊገልጹት ይሻሉ። እኔ ይህ አጥጋቢ ሆኖ አላገኘሁትም። በበኩሌ ቅድሚያ የምሰጠው ነገር ሙስሊም ወዳጆቼን ወደ መሠረታዊው ጉዳይ ማምጣትን ነው። «በእርግጥ እውነትን ለማወቅ ትፈልጋለህን? በዚህ ነገር እግዚአብሔር ራሱንና የእርሱን እውነት እንዲገልጥልህ እና ማመንም እንድትችል በመጸለይ መጽሐፍ ቅዱስን አንብብ» ስል እመክረዋለሁ።

መጽሐፍ ቅዱስ በሥላሴ መካከል ግንኙነቶች መኖራቸውን በግልጽ ያስተምራል። ዮሐንስ የጻፈው ወንጌል በመጀመሪያ ቁጥር «በመጀመሪያ ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» ይላል። በአሥራ አራተኛው ቁጥር ደግሞ «ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ ዘንድ አደረ» ይላል። በዚህ የእግዚአብሔር አንድነት ውስጥ የፍቅር ግንኙነት እንዳለ መቀበል አለብን። ነገር ግን ለዚህ ውስን ለሆነው የሰው አእምሮ እግዚአብሔር ይህን ግንኙነት ሊያስተላልፍ የሚችለው እንዴት ነው? በየትኛውም ስፍራ በማንኛውም ጊዜ በሁሉም የሰው ልጅ ዘንድ የታወቀ አንድ የፍቅር ግንኙነት አለ፥ይህም በአባትና ልጅ መካከል ያለ ግንኙነት ነው። ይህ እንግዳ ነገር አይደለም፤ ስለዚህም እግዚአብሔር የፍቅሩን ባሕርይ በዚህ መንገድ ገልጿል። «በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፥ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና» (1ኛ ዮሐ. 4:9)። ለዚህ የሚያገለግሉ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችም አሉ። አሁንም ይህን ዕድል ተጠቅሚ ሙስሊም ጓደኛዬ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነብ አበረታታዋለሁ።

2. ብዙውን ጊዜ የሚሰማው ሁለተኛ ተቃውሞ «እግዚአብሔር ልጅ ሊወልድ አይችልም» የሚል ነው። (በሙስሊም አስተሳሰብ ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ከሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳደረገ ነው።) እንደገና በዚህ ዓይነት ወራዳ አባባል ላይ በቁርጠኛ ስሜት እቃወማለሁ። ስለ ድንግል መውለድ በቀጥታ መንገድ ለመግለጽ አልሞክርም፥ ነገር ግን በዚህ ዓይነት መንገድ እመልስለታለሁ «እንዲህ ያለውን አስፀያፊ ታሪክ የሚናገረው ማነው? ኢየሱስ በተአምራዊ መንገድ ተፀንሶ ወደ ዓለም እንደሚመጣ መልአኩ ገብርኤል (ሙስሊሞች በጣም የሚያከብሩት) እንዳወጀ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። መልአኩ ገብርኤል ሐሰትን አልተናገረም። ይህ ታሪክ የተዘገበው በወቅቱ፥ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ለመናገር ሥልጣን በነበረው ሐኪም ነበር። ሉቃስ የጻፈውን ወንጌል ልስጥህ። እግዚአብሔር ለእኛ ስለገለጣቸው አስደናቂ ጥልቅ ነገሮች ራስህ ልታነበው ትችላለህ።» በዚህ መንገድ የኢየሱስን ሥጋ ለብሶ መወለድ አስፈላጊነት በመጽሐፍ ቅዱስ ፍጹም ሥልጣን ላይ ለማሳረፍ እጥራለሁ።

ይህን መሰሉ አጋጣሚ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ እንደሆነና ለእርሱ ምንም እንደማይሳነው ለማሳሰብ ምቹ ነው። ሙስሊሞች እንደሚናገሩት፥ በሥጋ ከመገለጥ በቀር እግዚአብሔር ምንም ነገር ማድረግ ይችላል ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምርም። ሁሉን ቻይ መሆኑን ካመኑ ምንም ሊያደርግ እንደሚችል፥ ሰው እንኳ መሆን እንደሚችል አስረዳቸው።

3. «ኢየሱስ ከነቢያት አንዱ ነበር እንጂ እግዚአብሔር አልነበረም።» ይህ ተቃውሞ በወንጌል ይዘት ላይ እና በክርስቶስ መለኮትነት ላይ የተነጣጠረ ነው። በመሆኑም አሁንም ለዚህ ለተሳሳተ አስተሳሰብ ቃል በቃል መልስ ከመስጠት ይልቅ በተዘዋዋሪ መንገድ አብራራዋለሁ። ምክንያቱም የምንወያይበት ጉዳይ የእግዚአብሔርን ባሕርይ የተመለከተ ስለሆነ ነው። ከኢየሱስ ክርስቶስ ሰብአዊነትና መለኮታዊነት ምሥጢር ጋር ተፋጥጠናል። ሰብአዊ ውስን አእምሮ በላለማዊና ወሰን አልባ እግዚአብሔርን በሙላት ሊረዳ አይችልም።

ሙስሊም ወዳጄን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ በእርግጥ ምን እንደሚል ለራሱ አንብቦ እንዲረዳ አበረታታዋለሁ። ሐቁ፥ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰብእና ውስጥ እግዚአብሔርንና ፍጹም ሰውን እናገኛለን። እርሱ ያለ ኃጢአት ነበረ! ጌታ ኢየሱስ እንዳደረገው ሁሉ ከእግዚአብሔር በስተቀር ማንስ ኃጢአትን ይቅር ሊል ይችላል? እግዚአብሔር ካልሆነ በቀር ሙታንን ሊያስነሣ የሚችል ማነው? ነፋሳትና ማዕበል ለቃሉ እንዲታዘዙ የሚያደርግ፥ በሰይጣንና በመናፍስት ዓለም ላይ ፍጹም ጌትነት ያለው እግዚአብሔር ካልሆነ በቀር ማን ነው? የወደፊቱን

የሚያውቅ፥ የሰዎችን አሳብ የሚያውቅ፥ ከእይታ በተሰወረ ርቀት ያሉትን ሰዎች የሚያይ ከእግዚአብሔር በቀር ማን ነው? በወንጌላት በሙሉ ጌታ ኢየሱስ ለመለኮት ብቻ የተወሰኑትን ባሕርያት በየቀኑ አሳይቷል።

ቁርዓንም ቢሆን ከእነዚህ ከጌታ ኢየሱስ ድርጊቶች አንዳንዶቹን ያምንባቸዋል። ግን በሰብአዊነቱ ላይ ያተኩራል እንጂ አምላክነቱን አይቀበልም። ታምራትን የሠራው በእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ እንደሆነና ከእርሱ በፊት እንደነበሩት ሌሎች ነቢያት ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል መሣሪያ ሆኖ እንዳገለገለ በመቁጠር ዘግቧል። ጊዜ ወስደህ የእንዲህ ዓይነቱን ትምህርት ውሸት አጋልጥ። ጌታ ኢየሱስ ታምራትን የሠራው በራሱ ኃይል መሆኑንም ግልጽ አድርግ። ታምራትን በፈጸመባቸው ወቅቶች ሁሉ ቃልን ይናገርና ወዲያውኑ ይከናወን ነበር። ይህ ከነቢያትና (1ኛ ነገ. 18:36 ተመልከት) ከሐዋርያት (ሐዋ. 3:6 ተመልከት) ሁኔታ ተቃራኒ ነበር፤ እነርሱ የእግዚአብሔር ኃይል መተላለፊያ ብቻ ነበሩ። ከክርስቶስ ውስጣዊ የፈውስ ዓይነተኛ ክንውኖች «... ኃይል ከእኔ እንደወጣ እኔ አውቃለሁና አለ» (ሉቃስ 8:46) እና «... ከእርሱም ኃይል ወጥቶ ሁሉን ይፈውስ ነበርና ...» (ሉቃስ 6:19) የሚሉ ይገኛሉ።

ሙስሊሞች የሚያከብሯቸው የብሉይ ኪዳን ነቢያት፥ መሲሑ ከነቢይ የላቀ እንደሚሆን የመተንበያቸውን እውነታ በዝርዝር ልታስረዳቸው ትችላለህ። ነቢዩ ኢሳይያስ «ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» (ኢሳ. 9:6) ሲል ጽፏል።

ይህንን ተቃውሞ ለመመለስ የሚያስችለው ሌላው ጠቃሚ ነጥብ ደግሞ እራሱ፥ እስልምናም ጌታ ኢየሱስ ታላቅ ነቢይ መሆኑን መቀበሉንና እውነተኛ ነቢይ ደግሞ እንደማይዋሽ በማሳየት ነው። ሆኖም ጌታ ኢየሱስ ታላቅ ነቢይ ነኝ አይልም፤ ነገር ግን እርሱ እግዚአብሔር ወልድ ነው፥ ማለትም የሰውን ሥጋ የለበሰ አምላክ ነው። ስለ ራሱ የሚናገረውን ለማረጋገጥ ልትጠቀም የምትችልባቸው አንዳንድ የንባብ ክፍሎች ዮሐንስ በጻፈው ወንጌል ውስጥ ይገኛሉ። እነዚህም ዮሐ. 17:5፥ 8:58፥ 5:16-27 ናቸው። እንደዚሁም «እኔ ነኝ» በማለት የተናገራቸው ሰባቱ ዐረፍተ ነገሮች በ(ዮሐ. 6:35፥ 8:12፥ 10:7፥ 10:11፥ 11:25፥ 14:6፥ 15:1) ይገኛሉ። እነዚህ ቃሎች ለራሳቸው ይመሰክራሉ።

4. አራተኛ የምናነሣው ተቃውሞ «ኢየሱስ በመስቀል አልሞተም» የሚለው የሙስሊሞች አባባል ነው። እግዚአብሔር ነቢዩ እንዲሰቀል ስለማይፈቅድ፥ ኢየሱስን የሚመስል ሌላ ሰው በእርሱ ቦታ በመስቀል ተተክቷል ይላሉ።

ከዚህ በመቀጠል ለመረዳት እንደሚቻለው፥ ይህን አባባላቸውን ለማስተባበል በጥያቄና መልስ አቀራረብ ተጠቅሚአለሁ።

ሙስሊም፡ «ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም።»

ክርስቲያን፡ «ለምን ይህን ትላለህ?»

ሙስሊም፡ «ቁርዓን እንዲህ ስለሚል ነው።»

ክርስቲያን፡ «ይህን አባባሉን ለመደገፍ የሚያቀርበው ምን አዲስ ማረጋገጫ አለ? የዓይን ምስክሮችን አዲስ ማረጋገጫ ይጠቅሳልን?»

ሙስሊም፡ «አይጠቅስም፤ ግን እግዚአብሔር የእርሱ ነቢይ በዚህ ዓይነት መንገድ እንዲሠቃይ አይፈቅድም ነበር። በእርሱ ምትክ የተተካው ሌላ ሰው ነበር።»

ክርስቲያን፡ «የኢየሱስ እናት ከመስቀሉ አጠገብ ቆማ ታለቅስ ነበር። ታዲያ በመስቀል ላይ የተቸከረው የወለደችው ልጇ መሆን አለመሆኑን አታውቅም ነበር ብለህ ታስባለህ? መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ የሚናገረውን አብረን እንመልከት።»

ስለ ክርስቶስ ሞት ለሙስሊም በምትነግርበት ወቅት «እግዚአብሔር የእርሱን ነቢይ እንዲገደል ይፈቅዳል ብዬ አላምንም?» ሊልህ ይችላል። ለዚህ ቀላሉ መልስ እግዚአብሔር ሁልጊዜ እኛ እንዲህ ያደርጋል ብለን በምናስብበት መንገድ እንደማያደርግ መስማማት ነው። በቃሉ ውስጥ «አሳቤ እንደ አሳባችሁ መንገዳችሁም እንደ መንገዴ አይደለምና፥ ይላል እግዚአብሔር። ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፥ እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ አሳቤም ከአሳባችሁ ከፍ ያለ ነው» (ኢሳ. 55፡8፥ 9) በማለት ያውጃል።

እንደዚሁ በኢሳይያስ 53 እና በመዝሙረ ዳዊት (22) ስለ ክርስቶስ ሞት በስፋት የተጠቀሰውን የብሉይ ኪዳን ነቢያት ገለጻም ተጠቀም። እነዚህን ክፍሎች አንብበው በወንጌል ከተብራራው የክርስቶስ ሞት ዝክረ ነገር ጋር እንዲያነጻጽሩት ሙስሊሞችን ምከራቸው።

በወቅቱ በሕይወት ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ያለ ጥርጥር የክርስቶስን ሞት ያውቁ እንደነበር በማሳየት ክርክሩን ማጠናከር ይቻላል። ስለ ድርጊቱ በኢየሩሳሌምና በዙሪያዋ ባሉ አካባቢዎች የነበሩ ሁሉ ያውቁ ነበር። ቀደምት የነበሩት ሐዋርያት የዚህን ታሪካዊ ክስተት እውነታ በማስመልከት ፈጽሞ ማረጋገጫ አላቀረቡም፤ እንዲሁ ድርጊቱን በግልጽ ተናገሩት። ሐዋርያት ጳውሎስ በአግሪጳ ፊት ራሱን እየተከላከለ በሚናገርበት ወቅት፥ «በእርሱ ፊት ደግሞ በግልጥ የምናገረው ንጉሥ

ይህን ነገር ያውቃል፤ ከዚህ ነገር አንዳች እንዳይሰወርበት (ለንጉሡ) ተረድቼአለሁና፤ ይህ በስውር የተደረገ አይደለምና» (ሐዋ. 26፡26) ሲል ተናግሯል።

ተቃውሞውን በዚህ መልክ ካስተናገድሁ በኋላ በመቀጠል ለምን እንደሞተና ከሞትም ለምን እንደተነሣ ለማስረዳት እሞክራለሁ። በሐዋርያት ስብከት ትልቁ ትኩረት ያረፈው በትንሣኤ ላይ ነው። ስለዚህ አንተም ሁልጊዜ ሞቱን ከትንሣኤው ጋር አያይዝ። ለእውነተኛ ክርስቲያኖች አሁንም ቢሆን ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንደተሰቀለ የሚያሳይ ሃይማኖታዊ መስቀል ማየት በእውነትም አሳዛኝ ድርጊት መሆኑን ግለጽ።

5. «መጽሐፍ ቅዱስ ከመጀመሪያው ጽሑፍ የተለወጠ በመሆኑ እውነተኛ አይደለም።» ለዚህ ተቃውሞ ምላሽ ለመስጠት በጣም ቀላል ዘዴ ሆኖ ያገኘሁት መጽሐፍ ቅዱስን ወይም አዲስ ኪዳንን በእጃቸው በማድረግ «እባክህን እስኪ የት ቦታ እንደተለወጠ አሳየኝ» ብሎ መጠየቁን ነው። ለዚህ መልስ ያለው አንድም ሙስሊም አላገኘሁም። ከዚያም በመቀጠል «የሆነ ሰው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አሳስቶሃል» በማለት እናገራለሁ። ይሁንና ቁርዓን መጽሐፍ ቅዱስ ተለውጧል አይልም፤ ደግሞም ቁርዓንም ቢሆን የተጻፈው እጅግ ዘግይቶ በሰባተኛው ምዕተ ዓመት ነው።

ሙስሊሞች የሚቀበሏቸው አራት ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ተውራት (ቶራ፣ አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት)፣ ዘቡር (መዝሙረ ዳዊት)፣ ኢንጅል (ወንጌላት) እና ቁርዓን ናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን እስልምና ከመጀመሩ ረጅም ጊዜ በፊት በደንብ መሠረት የያዙ ናቸው። ከሁለተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ዕድሜ ያስቆጠሩና በመጀመሪያው ቋንቋ የተጻፉ ቅጂዎች ዛሬም በቤተ መዘክሮች የሚገኙ ሲሆን በእጃችን ካለው ጋር አንድ ዓይነት ናቸው። ሙስሊም ጓደኛህ መጽሐፍ ቅዱስን በጸሎት መንፈስ እንዲያነብና እውነት ስለመሆን አለመሆኑ እግዚአብሔር እንዲገልጥለት እንዲለምን ገፋፋው። በየምሽቱ ለአስራ አምስት ደቂቃ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንዲያነብ በተለይ አበረታታው። መንፈስ ቅዱስ በመንፈስ ለታወረው ብርሃን ሊሰጥ የሚችለው በእግዚአብሔር ቃል በኩል መሆኑን አስተውል።

አንድ የተለወጠ ሙስሊም ለሌላ ሙስሊም በሚመሰክርበት ወቅት ለመጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደተከራከረ የሚገልጽ ምሳሌ መጋቢ ዋረን ሞድሪክር ቀርቧል። በጣም የዋህ የሆነና እውነትን በትጋት የሚሻ የሚመስል አንድ ሙስሊም ኢብራሂም የተባለውን ክርስቲያን «ስለ ቁርዓን ምን ትላለህ?» በማለት ይጠይቀዋል። ሰውየው ኢብራሂም ሙስሊም ከመሆኑ አስቀድሞ ቁርዓንን

እንዳነበበ ያውቅ ነበርና ቁርዓን የሚናገረውን አስቀድሞ በአእምሮው ውስጥ በማብሰልሰል ላይ ነበር። ጥያቄውን ለመመለስ ኢብራሂም ፊቱን ወደ እርሱ ዘንበል ባደረገ ጊዜ እንደ መልአክ ፊት ያበራ ነበር። ከዚያም «መጽሐፍ ቅዱስን አንብብ» በማለት በቀላሉ መለሰለት። በወቅቱ መስጠት የሚችለው ምርጥ መልስ ያ ነበር። ስለ ቁርዓን መጥፎ ቢናገር ኖሮ ዜናው ለሙስሊም ባለሥልጣናት በደረሳቸውና ሕይወቱም በሥጋት ላይ በወደቀ ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል ራሱ አንብቦ የእውነትን መገለጥ ራሱ እንዲያገኘው ሙስሊሙን ተማጸነው።

ሙስሊሙ ግን አሁንም ደገመና በመቀጠል «ስለ ቁርዓን ምን ትላለህ?» በማለት መጋቢ ሞድሪከርን ጠየቀ። እርሳቸውም መልስ ለመስጠት እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጣቸው ከጸለዩ በኋላ «ይህ እኮ የእኛ ችግር አይደለም፤ የአንተ ችግር ነው» አሉት። ማብራሪያቸውንም በመቀጠል፥ ቁርዓን የተሰጠው መጽሐፍ ቅዱስ ከተጠናቀቀ ከስድስት መቶ ዓመታት በኋላ ነው። ስለዚህ ቁርዓን ከመጽሐፍ ቅዱስ የት ላይ እንደሚለይ አይቶ እውነቱን መወሰን የሙስሊሙ ጉዳይ ነው በማለት ነገሩት።*

* «በእስላማዊ ሕዝቦች መካከል በግል ነፍሳትን የመማረክ ልምምድ»፥ በመጋቢ ኤች ዋረን ሞድሪከር። የግል ዕትም፥ በኤስ አይ ኤም ኢንተርናሽናል ፖ.ሣ.ቁ. 7900 ሊገኝ የሚችል። ('Personal Soul-Winning Experiences Among Islamic People', by Rev. H. Warren Modricker. A private publication available through SIM International, P O BOX 7900. Charlotte, NC 28241, USA.)

እውነተኛ ወንጌል ነው ስለሚሉት የበርናባስ ወንጌል ስለተሰኘው የሚጠቅሱ ሙስሊሞች ይገጥሙህ ይሆናል። ምሑራን ትክክለኛ አለመሆኑን ያረጋገጡ ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ ያለችግር የቅዋሚ አቋም ልትይዝ ትችላለህ። ስለ መጀመሪያ ምዕተ ዓመት መልክአ ምድርና ፖለቲካ እንደዚሁም ስለ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ ስሕተቶችን የያዘ ነው። በርናባስ ከሐዋርያ ጳውሎስ ጋር አብሮ ይሠራ የነበረና አንድ ዓይነት ወንጌል ይሰብክ የነበረ ነው። በእርሱ የተጻፈ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምንም የለም። የበርናባስ ወንጌል በይዘቱ መጽሐፍ ቅዱስንና ቁርዓንን የሚቃረን ነው። እንዳውም ምዕመናንን ለማወናበድ ሲባል በአሥራ አራተኛው ምዕተ ዓመት የተጻፈ የማጭበርበሪያ ጽሑፍ ነው።

## ክርስቲያኖችን ሊገጥሟቸው የሚችሉ ሌሎች ጉዳዮች

አንድ ሙስሊም «ክርስቲያኖች መጥፎ ሰዎች ናቸው፤ ምክንያቱም አልኮል መጠጦችን ይጠጣሉ፤ የአሳማ ሥጋም ይበላሉ» ሊልህ ይችል ይሆናል። አልኮል መጠጣት ለሙስሊሞች የተከለከለ ሲሆን፥ ክርስቲያኖችም ቢሆኑ አልኮልን ስለመጠቀም በቃሉ ውስጥ የተነገረውን መረዳት ይገባቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ለሰውነታችን እንክብካቤ እንድናደርግ በ1ኛ ቆሮንቶስ 6፡12-15 ይነግረናል። አልኮልን ያለአግባብ መጠቀም ለሰውነታችን ጉጂ እንደሆነ የታወቀ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስካርን በመቃወምም ይናገራል። ብዙ ክርስቲያኖች ራሳቸውን ከአልኮል የሚለዩት በግልና በማኅበራዊ ሕይወት ከሚያስከትለው አደገኛ ጠንቆች የተነሣ ነው።

ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስ ወይን መጠጣትን ያልከለከለባቸው በርካታ ስፍራዎች አሉ። ለዚህም ማብራሪያ አለው። ዛሬ እኛ ለስላሳ መጠጦችን እንደምንጠቀም ሁሉ በዚያን ዘመን በነበረው ባህል የወይን አጠማመቅ በጣም የቀጠነ ነበር። በዚህ መልኩ የሚዘጋጅ እስከሆነ ከጥቅም ላይ የማይውልበት ምንም ምክንያት አልነበረም። ሆኖም ግን በሙስሊሞች ዘንድ እጅግ የተወገዘ በመሆኑ፥ በተቻለ መጠን ክርስቲያኖች በግልጽ ባይጠጡት ይመረጣል። ሐዋርያው ጳውሎስ «ሥጋን አለመብላት ወይንንም አለመጠጣት ወንድምህም የሚሰናከልበትን አለማድረግ መልካም ነው» (ሮሜ 14፡21) በማለት እንደመከረው መፈጸም ተገቢ ነው።

ሙስሊም «እናንተ ክርስቲያኖች የማትጾሙት ለምንድን ነው?» ብሎ ሊጠይቅህ ይችላል። በእስልምና የረመዳንን ወር በሙሉ ቀኑን ሁሉ ከምግብና መጠጥ መለየት ግዴታ ነው። (ማታና ጀንበር ከመውጣቷ በፊት ግን ይፈስካሉ።) ይህ የሚደረገው ከእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን ለማግኘት ሲሆን፥ ሙስሊሞች በመጾማቸው ጽድቅን እንደሠሩ ይሰማቸዋል።

አንዳንድ የክርስትና ክፍሎች ሥርዓታዊ ጾምን የሚለማመዱ ቢሆንም ዳሩ ግን ቅዱስ ቃሉ ምግብን በተመለከተ በማያሻማ ሁኔታ የሚሰጠው መግለጫ አለ፡- «መብል ለሆድ ነው፥ ሆድም ለመብል ነው፤ እግዚአብሔር ግን ይህንም ያንም ያጠፋቸዋል» (1ኛ ቆሮ. 6፡13)። አንዳንድ ክርስቲያኖች የሚጾሙት በፈቃደኛነት ላይ በተመሠረተ አቋም ሲሆን፥ ይኸውም መመገብ ለየት ላለ ጸሎትና አገልግሎት ዕንቅፋት በሚሆንበት ጊዜ ነው። ለዚህ ተግባር ምንም ልዩ ወሮታ የሚያሰጥ ነገር የለውም።

እግዚአብሔር የበለጠ ጉዳይ ያለው ከልባችን ዝንባሌ እንጂ ከመጾማችን ወይም ካለመጾማችን አይደለም። «እኔስ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን? የበደልን እስራት ትፈቱ ዘንድ፥ የቀንበርንስ ጠፍር ትለቅቁ ዘንድ፥ የተገፉትንስ አርነት ትሰድዱ ዘንድ፥ ቀንበሩንስ ሁሉ ትሰብሩ ዘንድ አይደለምን? እንጀራህንስ ለተራበ ትቆርስ ዘንድ፥ስደተኞቹን ድሆች ወደ ቤትህ ታገባ ዘንድ፥ የተራቆተውንስ ብታይ ታለብሰው ዘንድ፥ ከሥጋ ዘመድህ እንዳትሸሸግ አይደለምን?» (ኢሳ. 58፥6፥ 7) ይላል።

ሌላው ሊቀርብልህ የሚችለው «ስለ ነቢዩ መሐመድ ምን ታስባለህ?» የሚል ጥያቄ ሊሆን ይችላል። ክርስቲያኖች ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ዝግጁ መሆን አለባቸው። መመለስ የሚገባን ቅያሜ በማይፈጥር መንገድ ቢሆንም ቅሉ፥ ዳሩ ግን ሙስሊሞች ለመሐመድ የሚሰጡትን ጥልቅ አክብሮት በሚያረጋግጥ መንገድ መሆን የለበትም። ኤል ፊትዝሰሞንስ «በቤት አይደለም» (Not At Home) በተሰኘው መጽሐፋቸው ያቀረቡት ጠቃሚ ምላሽ ወረድ ብሎ ተመልክቷል።*

«በመሐመድ ባምን ኖሮ ሙስሊም እሆን ነበር! አይደለም እንዴ? እዚህ ላይ አንድ ታሪክ ልንገርህ። አንድ ሰው በፍጥነት በሚውርድ ጅረት ውስጥ ወደቀ። መዋኘት አይችልም። ሁለት ሰዎች ደግሞ በዳሩ ቆመዋል። አንደኛው «ሕይወትህን አድን!» እያለ ይጮኻል፥ ወይም በዳር በኩል ዘሎ ይገባና እየዋኘ «ተመልከተኝ እንዲህ ነው ማድረግ ያለብህ!» በማለት ሊመክረው ይሞክራል። ሌላኛው ሰው ደግሞ ዘሎ ይገባና የሚሰምጠውን ሰው ትከሻዎቹን ይይዝና ወደ ዳር ያወጣዋል። መሐመድ የትኛው ነው? ጌታ ኢየሱስስ የትኛው ነው?»

* በግል የታተመ መጽሐፍ፥ የሚገኘው ከኤስ አይ ኤም ኢንተርናሽናል፥ ፖ.ሣ.ቁ. 7900፥ ቻርሎቴ፥ (A privately printed booklet available from SIM International, P O Box 7900, Charlotte, NC 28241, USA.)

«መሐመድ የመጨረሻው ነቢይ ስለሆነ ከሁሉ ታላቁ ነቢይ ነው።» ክርስቲያኖች ሊፋጠጡት የሚችሉት ሌላው ስሕተት ይህ ነው። ሙስሊሞች ኢየሱስ በዮሐንስ 14 ይመጣላችኋል ብሎ ቃል የገባው መንፈስ ቅዱስን ሳይሆን፥ መሐመድን እንደሆነ ያምናሉ። ይህን አሳብ መሠረት በማድረግ መሐመድ ከኢየሱስ የሚበልጥ ለመሆኑ ማረጋገጫ ይሰጣሉ። እንዲሁም ሁሉም ሙስሊሞች ሲባሉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር እንደሚመለስ በጥቅሉ ያምናሉ።

መሐመድ ከሁሉም በላይ ስለመሆኑ አንድ ሙስሊም በሚናገርበት ጊዜ በመጋቢ ሞድሪከር እንደሚከተለው በተገለጸው ቀጥተኛ ያልሆነ ምላሽ ተጠቀም። ምላሽህንም «ኢየሱስ እንደሚመለስ ታምናለህ?» በሚል ጥያቄ ጀምር። በዚህ ጊዜ

የሙስሊሙ መልስ በማያወላዳ ሁኔታ «አዎን! ወደ ምድር እንደሚመለስ እምናለሁ» የሚል ይሆናል። ረጋ ብለህ «በትክክል ይህን ታምናለህ ብዬ አላስብም» ትለዋለህ። መልስህ አስደንግጦትና አውኮት ኢየሱስ እንደሚመለስ እምነቱ መሆኑን በድጋሚ እንዲናገር ያደርገዋል። የአሳብ ልውውጡን አታጣድፍ! አባባሉን አለማመንህ በአእምሮው እስኪሠረፅ ድረስ ለጥቂት ጊዜ ታገሥ። ከዚያም «ኢየሱስ የሚመለስ ከሆነ እርሱ የመጨረሻ ነው ማለት ነዋ!» ስትል በመጨረሻ ላይ ልታፋጥጠው ትችላለህ። ሙስሊሙ ኢየሱስ እንደሚመለስ መቀበሉ እርሱ የመጨረሻው ነቢይ መሆኑን ስለሚያጸናበት፥ ኢየሱስ ከመሐመድ ይበልጣል ብሎ መናገሩ መሆኑን ወዲያውኑ ይገነዘባል።

## ወደ ቀና ምስክርነት ተሸጋገር

ከላይ የተገለጸው መረጃ ሙስሊሞች በክርስትና ላይ የሚሰነዝሩትን ተቃውሞ ለመቋቋም ጠቃሚ እንደሆነ እምናለሁ። ስለዚህ የራስህን መልሶች በወጥነት እስክታቀናብር ድረስ እንደ መመሪያ አድርገህ ተጠቀምበት። ሆኖም የሙስሊሞችን ጥያቄ መመለስ ለሙስሊም ወንጌል ስርጭት የትኩረት ነጥብ መሆን እንደሌለበት ማስታወስ ይኖርብሃል። ይህን የመሰለው ክርክር መቆጠር ያለበት ስለ ጌታ ኢየሱስ ለመመስከር እንደ መረማመጃ ድንጋይ ብቻ ሆኖ ነው። ጥያቄዎቻቸውን በሙሉና በሚገባ በመመለሳችን፥ ወደ ጌታ የተመለሱ ሙስሊሞች የሉም። ወደ ጌታ መመለስ የአእምሮ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፥ የልብና የፈቃድም ጉዳይ ነው። ሙስሊሞች ቁርዓንን፥ በማስተዋልና በምክንያት ላይ በተመሠረተ አጠናን ሳይሆን እንዲሁ ቃል በቃል ይሸመድዱታል። አብዛኛዎቻቸውም ለእምነታቸው ምክንያታዊ መሠረት ማቅረብ የሚችሉ አይደሉም።

ለአንዳንዶቹ ለተቃውሞዎቻቸው መልስ መስጠት አለመቻሌን በመቀበል ያለምንም ማቅማማት «አላውቅም» ብዬ በግልጽ እመልሳለሁ። እውነትን ፈላጊ ጠያቂ ከሆነ ጥያቄዎቹን ሊመልስለት የሚችል መጽሐፍ ለማግኘት እንደምትረዳው ልትነግረው ትችላለህ። ነገር ግን ሁሉን አውቃለሁ በሚል አቋም አትቅረብ! አንድ ሙስሊም ከአስመሳይ እውቀት ይልቅ በታማኝነት ይበልጥ ይነካል። «የማውቀው ይህን ብቻ ነው፥ በተረፈ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንዲሆንልኝና የኃጢአት ይቅርታን ለማግኘት ለነበረኝ የልብ ናፍቆት ጌታ ኢየሱስ መልስ ሰጥቶኛል! እናም ለአንተም ቢሆን ይህንኑ ሊያደርግልህ ይችላል» በማለት ንግግሬን ለመቋጨት እሞክራለሁ።

ይህን በተመለከተ በሐዋርያት ሥራ 22 እና 26 የተዘገበ እጅግ ጠቃሚና ልንከተለው የሚገባ የሐዋርያው ጳውሎስ ምሳሌ አለ። ከማያምኑና በጥላቻ ከተሞሉ

አድማጮች ጋር በተፋጠጠበት ወቅት፥ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያውቀውን፥ ከሙታን ከተነሣው ክርስቶስ ጋር ስላደረገው ግንኙነት እና እንዴት ሕይወቱን እንደለወጠለት ነገራቸው። ሌላው ተመሳሳይ ምሳሌ ዮሐንስ በጻፈው ወንጌል ምዕራፍ 9 ላይ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ዕውር ስለነበረ ሰው የተነገረው ታሪክ ነው። ፈሪሳውያን ያቀረቡአቸውን ከባድ ጥያቄዎች በሙሉ አልመለሰም፤ ግን በእርሱ ላይ ምን እንደተከናወነ ተናገረ። «ዕውር እንደነበርሁ አሁንም እንዳይ ይህን አንድ ነገር አውቃለሁ።» በማለት ያቀረበውን ቀላል ምስክርነት ሊያስተባብሉ አልቻሉም። ልክ እንደዚሁ ሁሉ፥ ለሙስሊሞች በምንመሰክርበት ጊዜ ስለ ጌታ ያለንን የግል መረዳት ልንክድ አይቻለንም።

## ጥያቄዎችን በሌላ ጥያቄ መልሳቸው

ብዙ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ የተጠቀመበትና ለመከተልም ጥሩ የሆነው ዘዴ አንድን ጥያቄ ወይም ዐረፍተ ነገር በሌላ ጥያቄ መመለስ ነው። በጠያቂው አእምሮ ያለው ምን እንደሆነ እስከምታውቅ ለመመለስ አትጣደፍ። እኔም ብሆን ብዙ ጊዜ «ይህን ጥያቄ ለምን ትጠይቃለህ?» እያልኩ እጠይቃለሁ። ይህን ማድረጌ አንዳንዴ የመጀመሪያው ጥያቄ ለምን እንደተሰነዘረ ስለሚያብራራልኝ ወይም በጠያቂው ውስጥ ያለውን ዋንኛ የተሳሳተ አመለካከት ስለሚያመለክተኝ ነው።

አንድ ጓደኛዬ «አንተ ክርስቲያን ነህ?» ተብሎ በአንድ ሙስሊም ተጠየቀ። ሆኖም ጥያቄን በጥያቄ በመመለስ ዘዴ ተጠቀመና «ክርስቲያን ምንድን ነው ስትል ነው የምታምነው?» በማለት መለሰለት። ሙስሊሙም ሲመልስ «ክርስቲያን በሦስት አማልክት የሚያመልክ፥ አልኮል የሚጠጣና የአሳማ ሥጋ የሚበላ ተሳዳቢ ነው።» አለ። እንግዲህ ጓደኛዬ ባለመጠራጠር፥ «አዎን ክርስቲያን ነኝ» ብሎ ቢመልስለት ኖሮ ነገሩ ምን ያክል የተምታታ እንደሚሆን ይህ ምሳሌ ያስረዳል።

ወንጌልን ለሙስሊሞች በማካፈል ላይ እያለህ ስለገዛ ሃይማኖታቸው ከማስተማር ልትቆጠብ ይገባል። ይህም ብዙውን ጊዜ የሚያጋጥመው አንድ ክርስቲያን ለማስረዳት ሲል «ሙስሊሞች ... ያምናሉ፤ ነገር ግን እኛ ክርስቲያኖች ... እናምናለን» በሚል አገላለጽ ሲጠቀም ነው። ሳታስብ ስለ እስልምና ታስተምራለህና ይህም እስልምና እውነተኛ እንደሆነ መደገፍህ ይመስላል።

እንደገና ደግሜ የማሳስብህ፥ ለሙስሊሞች ወንጌልን ከማድረስህ በፊት ሁሉንም ጥያቄዎች በመመለስ የተካንሁ ልሁን ብለህ ማሰብ እንደማይገባህ ነው። ዋናው ትኩረትህና የልብ እምነትህ ጌታ ኢየሱስን ለእነርሱ ማስተዋወቅ መሆኑን እስካልዘነጋህ ድረስ፥ ምላሽ መስጠቱን በድርጊት ትማረዋለህ። በአባሪ ሀ

የሙስሊሞችን ጥያቄዎች ለመመለስ ጠቃሚ የሆኑ በርካታ መጻሕፍት ተዘርዝረዋል። በሙስሊም ወንጌል ስርጭት ለምትሳተፉ ከእስልምና ጋር እና ከሙስሊም የአስተሳሰብ ዘይቤዎች ጋር የበለጠ ትውውቅ እንዲኖራችሁ በስፋት እንድታነቡት እመክራለሁ።

## የጠያቂዎችን የልብ ንጽሕና መመዘን

ለሙስሊም ይሁን ወይም እግዚአብሔር የለም ባይ ለሆነው፥ ወይም ለማናቸውም ሌላ ሰው ለልብ ንጽሕናው፥ የመጨረሻ መመዘኛ እውነትን ለማወቅ በእርግጥ ትፈልጋለህ? ቢገለጥልህስ ልትከተለው ፈቃደኛ ነህ? የሚሉትን ጥያቄዎች በማቅረብ የምታገኘው መልስ ነው።

ሰውየው በአዎንታ ከመለሰ ማብራሪያ መስጠትህን ቀጥል። «እንግዲያውስ እውነትን ልታውቅ የምትችልበት መንገድ ይኸውልህ። የአዲስ ኪዳን አንዱን ክፍል ለምሳሌ ወንጌልን ውሰድ። በምታነብበት ጊዜ ከልብህ ‹እግዚአብሔር ሆይ፥ በእውነት ካለህና ልትሰማኝ ከቻልክ፥ ይህም መጽሐፍ የአንተ ቃል ከሆነ፥ እባክህን በማነብበት ጊዜ ተናገረኝ፤ እኔም ደግሞ የምታሳየኝን ሁሉ አደርጋለሁ› » ብለህ ጸልይ።

ከዚህ በመቀጠል ስለ አንድ ጥገኛ ሙስሊም የተነገረ ታሪክ ይህንን አሳብ ያብራራዋል።

> «በተማሪነቴ ወራት በአንድ ምዕራባዊ ከተማ አንድ አነስተኛ የወንጌል ስርጭት ስብሰባ መከታተል ጀመርሁ። በዚህም ጊዜ ሦስት ነገሮች ልቤን ማረኩት። ምንም እንኳ አብዛኛዎቹ ሰዎች በዕድሜ ገፋ ያሉና እንደ እስልምና ስላሉ ሌሎች ሃይማኖቶች እውቀት ባይኖራቸውም እርስ በርስ ያላቸው ፍቅርና ለእኔም ያሳዩት ሰብአዊ ርኅራኄ በቅድሚያ ልቤን ነካው። ሁለተኛው ነገር ደግሞ አዲስ ኪዳንን ማንበብ ስጀምር ያደረብኝ ስሜት ነው። የበለጠ ባነበብሁ መጠን የበለጠ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ብሳብም፤ በዚያው መጠን ግን ያለመፈለግ ስሜትም ነበር። የተሳብሁት ለሰው ልጅ ባለው ርኅራኄና በፍቅሩ ሲሆን ያልፈለኩበት ምክንያት ደግሞ ስለራሱ ማንነት የሚናገራቸው ቃላት ነበሩ። ሦስተኛው ልቤን የማረከው እግዚአብሔር በብዙዎች ዘንድ እንደሚታመነው በርግጥም ካለ ራሱን እንዲገልጽልኝ በየዕለቱ መጸለይ ነበር። ከስድስት ወራት በኋላ አንድ ሰው «ለምን ክርስቲያን አይደለህም?» ብሎ ጠየቀኝ። እንደሚመስለኝ፥ የሰጠሁት መልስ «ነኝ» የሚል ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ በዚያን ጊዜ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ ለመሆን ከቁርጥ ውሳኔ ላይ ደርሼ ነበር።»

ሙስሊሙ ጓደኛህ በዚህ ዓይነቱ የእግዚአብሔር ቃል እንዲተማመን ምንም ሳታመነታ ምከረው። እግዚአብሔር በትህትና ለሚሻ ልብ ሊመልስ ቃል ገብቷል (ማቴ. 7:7)። ነገር ግን የሰውን ልጅ እውቀት መሻት ለማርካት፥ ወይም ለቃሉ ለመታዘዝ ፈቃደኝነት የሌለውን ሰው ጸሎት ለመመለስ ሲል ብቻ ምንም የሚያደርገው ነገር የለም። አንተም ብትሆን ድካምና ጥረትህ ተቀባይነት ባያገኝ አትደነቅ፤ ምክንያቱም ተፈጥሮአዊ ሰው ጨለማን የሚወድና ብርሃንን የማይፈልግ ስለሆነ ነው (ዮሐ. 3:19-21)።

## በጥልቀት የሚታሰብ

*** ሦስት አማልክት ታመልካለህ ብሎ የወነጀለህን ሙስሊም እንዴት አድርገህ መልስ ትሰጠዋለህ?

*** «እግዚአብሔር ልጅን አልወለደም» ለሚለውስ ሙስሊም እንዴት ትመልሳለህ?

*** ኢየሱስ ታላቅ ነቢይ ነው ማለቱ በቂ ነው? ክርስቶስ እግዚአብሔር ነኝ ስለማለቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በማስረጃነት ለሙስሊሙ የምታቀርበው የትኛውን ክፍል ነው?

*** ክርስቶስ ባይሞት ኖሮ ምን ልዩነት ያመጣብህ ነበር?

ሙስሊሞች ክርስቶስ በመስቀል እንደ ሞተ የመረዳታቸው አስፈላጊነት ለምንድን ነው?

*** ቁርዓን ከመጽሐፍ ቅዱስ በኋላ ስለተሰጠ መጽሐፍ ቅዱስን ይተካል ስለሚለው የሙስሊም አባባል ምን መልስ ትሰጣለህ?

# ምዕ. 12 ጸሎት - የአገልግሎት መሠረት

ለሙስሊሞች የታቀደ ማንኛውም የወንጌል ስርጭት ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ በጸሎት ላይ የተመሠረተና በጸሎት የተከበበ መሆን አለበት። ሙስሊሞችን በወንጌል መድረስ እውነተኛ መንፈሳዊ ውጊያ ስለሆነ፥ ዋንኛ መሣሪያችን በሆነው ጸሎት እንዴት መጠቀም እንደሚኖርብን መማር አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ እንድንጸልይ በርካታ ምክሮችን ይሰጣል። «. . . ሳታቋርጡ ጸልዩ . . .» (1ኛ ተሰ. 5:17)። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሁልጊዜ እንዲጸልዩ ነግሮአቸዋል (ሉቃስ 18:1)። ጌታ ኢየሱስ ራሱ በመጸለይ ብዙ ጊዜ አሳልፏል። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የጠለቀ ማብራሪያ የሚሰጠውን የጥቅስ ማውጫ በመጠቀም ስለ ጸሎት የተሰጡትን ማጣቀሻዎች ማየቱ ሊረዳህ ይችላል። ይህ ሁሉ ማብራሪያ

እንኳ ቢኖርም፥ የጸሎትን አሳብ ሙሉ ለሙሉ ለመረዳት አሁንም ጥረት እያደረግኩኝ ነው። በተጨማሪም እግዚአብሔር ያደረገልኝን ርዳታዎች ላካፍልህ እወዳለሁ።

በ1ኛ ዮሐ. 5፡14፥ 15 ውስጥ የሰፈረው ቃል ለውጤታማ ጸሎት መሠረት የሚጥል ይመስላል። «በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል። የምንለምነውም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደ ተቀበልን እናውቃለን።» ስለዚህ ለእኔ እንደሚመስለኝ ለጸሎታችን ቁልፉ በምንጸልይበት ጉዳይ ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቁ ነው።

የእግዚአብሔር ፈቃድ በኤፌሶንና በቈላስያስ የመጀመሪያ ምዕራፎች ውስጥ በግልጽ ተገልጧል። እነዚህ ክፍሎች የሚያብራሩልን፥ የእግዚአብሔር ዋና ፈቃዱ በሰማይም ሆነ በምድር ያለው ፍጥረት ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ ከፍ ለማድረግ ነው። እርሱ የእግዚአብሔር የክብሩ ነጸብራቅ፥ ፍጹማዊ አምሳሉም በመሆኑ፥ በሁሉ ሊከበርና ሊመለክ ይገባዋል። ይህ የላቀ የክብር ስፍራው በአሁኑም ጊዜ ቢሆን በሰይጣንና በርኩሳን መናፍስቱ ዕንቅፋት እየተደረገበት ነው። ስለዚህ በጌታ በመተማመን ለሙስሊሞች እንዲህ ብለን ልንጸልይ እንችላለን፡- «ሰይጣንን አሸንፈው፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዛ ዓለሙ የሚገባውን ክብርና ሁሉን የመጠቅለል ሥልጣን የሚቀናቀነውን የሰይጣን ክፉ ዓላማ ገሥጸው። በሙስሊሞች አእምሮ ሰይጣን የጋረደውን ዕውርነት ግፈፍ።»

ምሥጢሩ ከአእምሮአችን በላይ ቢሆንም፥ ጸሎት እግዚአብሔር በዚህ ዓለም በሚያከናውናቸው ዓላማዎቹ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው። እግዚአብሔር በጸሎት ሊያደፋፍረኝና ሊያበረታታኝ የተጠቀመባቸውን ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላካፍላችሁ።

በዘጸአት 17 እስራኤላውያን ከግብፅ ነፃ ከወጡ በኋላ ያካሄዱትን የመጀመሪያ ጦርነት ዝርዝር እናነባለን። ከአማሌቃውያን ጋር ባደረጉት ጦርነት ኢያሱ በሸለቆ ውስጥ የሚዋጋውን ሠራዊት መርቶ ለድል አበቃ። በኮረብታው ላይ ግን፥ ሙሴ የተራዘመው ጦርነት እስከሚያበቃ ድረስ አሮንና ሖር እጁን ደግፈውለት የእግዚአብሔርን በትር ከፍ አድርጎ እንደያዘ ነበር። እንደ ሰዎች ልማድ ቢሆን ኖሮ ከጦርነቱ በኋላ የድሉ ክብረ በዓል በሚከበርበት ሰዓት የሠራዊቱ መሪ የሆነውን ኢያሱን ባሞገሱት ነበር። ሆኖም ግን እግዚአብሔር ታሪኩን ሲዘግብ የድሉ ዋጋ የተሰጠው በጦር ሜዳ ላልነበሩትና ከሸለቆው በላይ ሆነው የእግዚአብሔርን በትር ይይዙ ለነበሩት ለሙሴ፥ ለአሮንና ለሖር ነው። ይህ ለወንዶችና ሴቶች ነፍስ

በሚደረገው ጦርነት ጸሎት ስላለው ድርሻ የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ነው። ድል የሚገኘው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመረዳት አእምሮአቸው በበራላቸውና ለእግዚአብሔር ክብር ሳያቋርጡ በሚጸልዩ ታማኝ ቅዱሳን አማካይነት ነው።

ሌላው ምሳሌ በሕዝቅኤል 22፡30፥ 31 ላይ የተመሠረተ ነው። «ቅጥርን የሚጠግንን፥ ምድሪቱንም እንዳላጠፋት በፈረሰበት በኩል በፊቴ የሚቆምላትን ሰው በመካከላቸው ፈለግሁ፥ ነገር ግን አላገኘሁም። ስለዚህ ቁጣዬን አፈሰስሁባቸው ...» ሙስሊሞችን ጨምሮ የማያምኑ ሁሉ ከኃጢአተኝነታቸው የተነሣ በአስፈሪው የእግዚአብሔር ቁጣ ፊት የተፈረደባቸው ሆነው ይቆማሉ። እኔ እና አንተ ለሙስሊሞች በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት በምንቆምበት ጊዜ፥ ጸሎታችን እግዚአብሔር ፍርዱን እንዲያዘገይ፥ ምሕረቱን እንዲያበዛና የንስሐ ዕድላቸውን እንዲያሰፋላቸው ያራራዋል። እርሱ ማንም እንዲጠፋ ፈቃዱ አይደለም (2ኛ ጴጥ. 3፡9፤ ሕዝ. 33፡11)። ነገሩ ታላቅ ምሥጢር ቢሆንም፥ ከእርሱ ጋር አብረው እንዲሠሩ እግዚአብሔር ጸሎተኞችን ይፈልጋል።

## የጸሎት ተባባሪዎች

በሙስሊም የወንጌል ስርጭት ሥራ ውስጥ ሳለህ ከአንተ ጋር እና ለአንተም የሚጸልዩ ክርስቲያኖች እጅግ በጣም ያስፈልጉሃል። በየዕለቱ ሊጸልይልህ ቃል የሚገባ ቢያንስ አንድ የጸሎት ጓደኛ አብጅ። እነዚህ የጸሎት ጓደኞች ውጤታማ ጸሎት እንዲጸልዩ ተዛማጅ መረጃዎችን ማግኘት አለባቸው። ነገር ግን የዚህ ዓይነቱ መረጃ «ምሥጢር - ለጸሎት ብቻ» የሚሉት ቃላት በላዩ ላይ ሊታተሙበት ይገባል። በማንም እጅ እንደ ልብ እንዳይገባ ወይም በድንገት የትም ወድቆ እንዳይገኝ ለማድረግ ሲባል ጽሑፉ በእትም መልክ መታተም የለበትም። አንድን ጠያቂ ወይም ወደ ጌታ የተመለሰን ሰው የኋላ ኋላ በግል ተጠያቂ እንዳያደርገው ለመጠንቀቅ ስትል ለማንም ሰው ዝርዝር መረጃዎችን አትስጥ። በጽሑፉም ላይ በስም የመጀመሪያ ፊደል፥ ወይም በፈጠራ ስም መጠቀሙ በጣም የተሻለ ነው። እንደዚሁ ሁሉ ጠበቅ ያለ መንፈሳዊ ክንውን የሚካሄድበትን አገር ወይም ክርስቲያን ሠራተኞች ስም አትጥቀስ።

## ለሙስሊም የወንጌል ስርጭት የሚረዳ ምልጃ፡-

በሙስሊሞች መካከል ለሚካሄደው አገልግሎት ስኬታማነት፥ የሚከተሉት በቅዱስ ቃሉ ላይ የተመሠረቱ የምልጃ ጸሎት መንደርደሪያ አሳቦች ሊጠቅሙህ ይችላሉ።

| የእግዚአብሔር ቃል... ይላል | ስለዚህ... እንጸልይ |
|---|---|
| አማኞች ከክርስቶስ ጋር ከሙታን ተነስተው፥ በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር ተቀምጠዋል። (ኤፌ.2:6) | በክርስቶስ ካለን የሥልጣን ስፍራ ለሙስሊሞች እንማልድ |
| ዓለም ሁሉ ለእርሱ ይሰግድ ዘንድ ጌታ ኢየሱስን ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው። (ፊልጵ.2:9-11) | ሙስሊሞ ከእስልምና ዞር ብለው ራሳቸውን ለክርስቶስ እንዲያስገዙና ጌታቸው አድርገው አሁኑኑ ያመልኩት ዘንድ ነው |
| በኃጢአት ላይ ፍርዱን ማምጣቱ የማይቀር ነው! ነገር ግን ማንም እንዳይጠፉ ምሕረትን ይወዳል። (2ኛ ጴጥ.3:9) | ሙስሊሞች ከኃጢአታቸው ንስሐ ገብተው፥ በክርስቶስ አምነው ይድኑ ዘንድ ነው። |
| ሰይጣን የማያምኑ ሰዎችን አእምሮ አሳውሮአል (2ኛ ቆሮ.4:4) | መንፈስ ቅዱስ ይህን ዕውርነት እንዲገፍና የክርስቶስ ክብር ብርሃን የሙስሊሞችን ልብ ያበራ ዘንድ ነው። |
| ቃሉ ሕያው ነው! የልብን ስሜትና አሳብ ይመረምራል (ዕብ.4:12) | የእግዚአብሔር ቃል ኃይል ሙስሊሞችን ይወቅስና እውነት መሆኑን ያሳምናቸው ዘንድ ነው። |
| እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውን ነገር የሚያስረዳ ነው (ዕብ. 11:1) | ከእስልምና ተመልሰው ጌታን ያገኙት በክርስቶስ እንዲያድጉና በዕለት ኑሮአቸው በእምነት ይራመዱ ዘንድ ነው። |
| የሰይጣን ምሽግ በጸሎት ይፈርሳል (2ኛ ቆሮ.10:4) | እግዚአብሔር የእስልምናን ምሽግ እንዲደረምስና ምርኮኞቹን ነፃ እንዲያወጣቸው፥ ይኸውም በወንጌል ያምኑ ዘንድ ነው። |

ደቀ መዛሙርት ለጌታ ኢየሱስ ያቀረቡት እጅግ ጠቃሚ ልመና «ጌታ ሆይ... እኛን መጸለይ አስተምረን» የሚል ነበር። ይህ ለእኛም የዘወትር ልመናችን ይሁን። ጸሎትን ለመማር ጠቃሚ ሆነው ያገኘሁዋቸው አንዳንድ መጻሕፍት:-

ለውጊያ የተወለደ፥ ቢ ኤ ማቴዎስ (ሰቨንኦክስ፡ ኦ ኤም ኤፍ መጻሕፍት፥ 1983) Born For Battle, by A Mathews (Sevenoaks: OMF Books, 1983).

ስለ ጸሎት በጸጥታ መናገር፥ በኤስ ዲ ጐርዶን (ግራንድ ራፒድስ፥ ኤም አይ፡ ቤከር ቡክ ሃውስ፥ 1980) Quiet Talks On Prayer, by S D Gordon (Grand Rapids, MI: Baker Book House, 1980).

ገደብ የለሹ የጸሎት ኃይል፥ በጄ ኦ ሳንደርስ (ቺካጐ፡ ሙዲ ማተሚያ ቤት፥ 1984)። (Prayer Power Unlimited, by J O Sanders (Chicago: Moody Press, 1984)

የምልጃ አገልግሎት፥ በኤ ሙሬ (ሉንዶን ማርሻል ፐከሪንግ፥ 1986) ናቸው። (The Ministry of Intercession, by A Murray (London :Marshall Pickering, 1996).

## በጥልቀት የሚታሰብ

*** የደቀ መዛሙርትን ጸሎት አስታውስ፡- «ጌታ ሆይ፥ እንድንጸልይ አስተምረን።» አንተም ይህን የዕለት ተዕለት ጸሎትህ አድርገው።

*** የጸሎትን መልስ ካላወቅህ ለመንፈስ ቅዱስ ሥራ ልብህ የተከፈተ እንዲሆን እግዚአብሔርን ጠይቀው።

- ያልተናዘዝከው ኃጢአት በሕይወትህ አለ?

- የማያምን ልብ አለህ?

- እርግጠኛ የሆነ የጸሎት መልስ በሌለበት ጊዜ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ መደገፍንና መተማመንን እያስተማረህ ነው?

*** «ለሙስሊሞች የወንጌል ስርጭት የሚረዳ ምልጃ»ን በአንድ ቅጠል ወረቀት ገልብጥ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አድርገውና ለሙስሊሞችና ለሙስሊም ወንጌል ስርጭት በምትጸልይበት ጊዜ በቃሉቹ ተጠቀም።